# የመንግሥት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ

# መመሪያ ቁጥር 12/2017

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በድሬዳዋ አስተዳደር የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር □27/2005 አንቀጽ 64/2 እና በድሬዳዋ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 16/2003 አንቀጽ 48/2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል::

## ክፍል ፩

## ጠ ቅ ላ ላ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ ''የድሬዳዋ አስተዳደር የመንግስት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 12/2017” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**2. ትርጓሜ**

2.1. የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ

ሀ/ ''የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ'' ማለት ዕቃው፣ አገልግሎቱ፣ የግንባታ ሥራው ወይም የምክር አገልግሎቱ ሊያሟላ የሚገባውን ጥራት፣ ዓይነትና ደረጃ የሚገልጽ ሰነድ ነው::

ለ/ ''አዋጅ'' ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 27/2005 እና የድሬዳዋ አስተዳደር የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 26/2005 ማለት ነው::

ሐ/ ''ጨረታ'' ማለት የጨረታ ማስታወቂያው ይፋ ከሆነበት ወይም የጨረታ ግብዣ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ የጨረታው አሸናፊ ተለይቶ ውል እስኪፈረም ድረስ ያለውን የግዥ አፈጻጸም ሂደት የሚገልጽ ነው::

መ/ ''መደበኛ የጨረታ ሠነድ'' ማለት የመንግስት መሥሪያ ቤቶች አጠቃላይ ይዘቱ አንድ ወጥ ወይም ተመሳሳይ የሆነ የጨረታ ሠነድ በቀላሉ ማዘጋጀት እንዲችሉ የሚረዳ በኤጀንሲው የተዘጋጀ ሠነድ ነው፡፡

ሠ/ ''የግዥ ሥራ ክፍል'' ማለት የመንግስት መስሪያ ቤቶች እንደስራ ባህሪያቸው የሚኖራቸው የውስጥ አደረጃጀት እንደተጠበቀ ሆኖ ግዥ ለመፈፀም ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው፡፡

ረ/ ''ጠቅላላ ዋጋ'' ማለት ለአንድ ግዥ አፈጻጸም ታክስን ጨምሮ ማናቸውም ሌሎች ወጪዎችን በማካተት በመንግስት መ/ቤቱ ለሚፈፀም ግዥ የሚከፈል ዋጋ ነው፡፡

ሰ/ ''የጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ'' ማለት ባለቤቱን ጨምሮ እስከ አምስት ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰራና የጠቅላላ ሀብቱ መጠን ህንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50 ሺህ፣ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ህንፃን ሳይጨመር ከብር 100 ሺህ ያለበለጠ ኢንተርፕራይዝ ማለት ነው፡፡

ሸ/ ''አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ'' ማለት ባለቤቱን ጨምሮ ከአምስት ሰዎች የበለጠ ስላሳና እና ከሰለሳ በታች ሠራተኞቸን ቀጥሮ የሚያሰራና የጠቅላላ ሀብቱ መጠን ህንፃን ሳይጨመር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 100ሺህ እስከ 5 መቶ ሺህ ውይም ህንፃን ሳይጨምር በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100 ሺህ እስከ 1ሚሊዮን 5 መቶ ሺህ ያለበለጠ ኢንተርፕራይዝ ማለት ነው፡፡

ቀ/ "የእድገት ደረጃ'' ማለት በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዥ የሚሰጥ የእድገት ደረጃ ነው፡፡

በ/ "የግል ኢንተርፕራይዥ'' ማለት በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ዘርፍ በግል ተደራጅቶ የሚንቀሳቀስ ነው፡፡

ተ/ "የንግድ ማህበር ኢንተርፕራይዝ'' ማለት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ህጋዊ አደረጃጀት እና በንግድ ህጉ አዋጅ መሠረት የተደራጀ ኢንተርፕራዝይ ነው፡፡

## ፫. <u>የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የሚሆነው በማናቸውም በአስተዳደሩ የመንግስት መሰሪያ ቤቶች ግዥ ላይ ይሆናል፡፡

## ፬. <u>መርሆዎች</u>

ማናቸውም ግዥን ለማስፈፀም የተሰጠ ሥልጣን እና የግዥ አፈፃፀም ተግባር የሚከተሉትን መርሆዎች ከግብ ማድረስ ይኖርበታል፡፡

ሀ/ በግዥ አፈፃፀም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት፣ ይህም ማለት ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ፣

ለ/ በአዋጁ በተፈቀደው ልዩ አስተያየት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ በዜግነት ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች በመንግስት ግዥ እንዳይሳተፍ አለመከልከልን ወይም አድልዎ አለማድረግን፣

ሐ/ የመንግስት ግዥ አፈፃፀምን ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ እድገት መደገፍ፣

መ/ ማናቸውም የግዥ ውሣኔ የሚሰጥበት መስፈርት እና በእያንዳንዱ ግዥ ላይ የሚሰጠውን ውሣኔ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ግልፅ ማድረግ፣

ሠ/ ከግዥ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የሚሰጡ ውሣኔዎች እና የሚወሰዱ እርምጃዎች የሚያስከትሉት ተጠያቂነት መኖሩን ማረጋገጥ፣

ረ/ በአዋጁና በዚህ መመሪያ በተፈቀደው ልዩ አስተያየት መሰረት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የሚደግፉ የሀገር ውስጥ አምራቾችን፣ ኩባንያዎችን እና አነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎችን ማበረታታት፡፡

# ክፍል ፪

# <u>ተግባርና ኃላፊነት</u>

## ፭. <u>የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ የሚከተሉት ተጨማሪ ዝርዝር ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

፭.፩. የግዥ ስራን እንዲያከናውኑ የሚመደቡ ሰራተኞች እና ኃላፊዎች በዘርፉ በቂ የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

፯÷፪. የግዥ ስራን እንዲያከናውኑ የሚመደቡ ሰራተኞች እና ኃላፊዎች ጥሩ ሥነ-ምግባር ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣

፯÷፫.የግዥ ስራን እንዲፈፅም የሚደራጀው የስራ ክፍል ስራውን በቡድን ለማከናወን የሚያስችል በቂ ስልጣን ያለውና ግልፅ የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋለት መሆኑን ማረጋገጥ፣

፯÷፬.የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉና ከ፫ ያላነሱ አባላት ያሉት የመ/ቤቱን ከፍተኛ ግዥዎች መርምሮ የሚያፀድቅ፣ እና ከሦስት ዓመታት የማይበልጥ የአገልግሎት ዘመን የሚኖረው የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ማቋቋም፣

ሀ/ በመ/ቤቱ ውስጥ በከፍተኛ ኃላፊነት ደረጃ ላይ የሚገኙ፣

ለ/ በተቻለ መጠን ከተለያየ የሙያ ዘርፍ የተውጣጡ እና በመ/ቤቱ ስራ የተሻለ እውቀት እና ልምድ ያላቸው፣

፯÷፭. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 ድንጋጌ ቢኖርም ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ አባላትን የአገልግሎት ዘመን ለአንድ ተጨማሪ የአገልግሎት ዘመን ማራዘም፣

፯÷፮.የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ አባላት ስራቸውን ለማከናወን የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ እና የቢሮ መገልገያ መሳሪያዎች የተሟሉላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣

፯÷፯.በግዥ አፅዳቂነት የሚመደቡ ሠራተኞች ለስራው የሚያውሉት ጊዜ የመደበኛ ስራቸው አካል ሆኖ በስራ ፕሮግራሞቻቸው እና ውጤት ላይ መመዝገቡን ማረጋገጥ፣

5.8. በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀሙ ግዥዎችን ለመቆጣጠርና ለመከታተል አስፈላጊውን የማስፈፀሚያ ስልት በማውጣት ተግባራዊ ያደርጋል

፯÷፱.በግዥ ስራ እና በግዥ አፅዳቂነት ለተመደቡ ሠራተኞች እና የስራ ኃላፊዎች መንግስት ያወጣውን የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ፣ ይህንን የአፈፃፀም መመሪያ፣ መደበኛ የግዥ ሰነዶች እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች እንዲደርሷቸው እና የመንግስት የግዥ ስርዓትን በሚገባ እንዲያውቁ የሚያስችል ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ

፯÷፩፲. ለግዥ ስራ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የስራ ክፍሉም ሆነ አፅዳቂ ኮሚቴው ስራቸውን በተገቢው ለመወጣታቸው ክትትል ማድረግ፣ እንደአስፈላጊነቱም የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣

5.11. ውስብስብ ለሆኑ እና ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ ለሚፈልጉ ግዥዎች የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ባለሙያዎችን በመምረጥ ጊዜያዊ ገምጋሚ ኮሚቴ ማቋቋም፣

ሀ. ከሚፈፀመው ግዥ ጋር በተያያዘ የዳበረ እወቀት እና ልምድ ያላቸውን

ለ. በሚቋቋመው ጊዚያዊ ገምገሚ ኮሚቴ ውስጥ የግዥ ሥራ ክፍል እንደ አስፈላጊነተ የጠያቂው ክፍል በአባልነት በማሳተፍ

ሐ. በመስሪያ ቤቱ ግምገማን ለማድረግ የሚችል ባለሙያ ካልተገኘ ከሌላ የመንገስት መ/ቤት አባል ሊሁን የሚችል ወይም የሚያማክሩ ባለሙያዎች በትውስት በኮሚቴው ውስጥ በማሳተፍ

፭፡፩፪፡ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የመ/ቤቱን የግዥ እቅድ መርምሮ ማፅደቅ፡-

ሀ/ የግዥ እቅዱ ከመ/ቤቱ የስራ ፕሮግራሞች ጋር መጣጣሙን፣

ለ/ ተሰባስበው ሊፈፀሙ የሚችሉ ግዥዎች አንድ ላይ መሰባሰባቸውን፣

ሐ/ ኤጀንሲው በሚወስነው መሠረት ከሌሎች መ/ቤቶች ግዥዎች ጋር ተጣምረው በማዕቀፍ ስምምነት ሊፈጸሙ የሚችሉ ግዥዎች መለየታቸውን፣

መ/ እቅዱ የመ/ቤቱን የግዥ ፍላጎቶች በሙሉ ያካተተ እና ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ቀርቦ የኮሚቴውን ይሁንታ ማግኘቱን፣

፭፡፩፫፡ ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር ተጠቃለው በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀሙ የመ/ቤቱ ግዥዎች የሚፈለጉ መረጃዎች ተሟልተው ግዥውን እንዲፈፅም ስልጣን ለተሰጠው አካል በወቅቱ እንዲላኩ ማድረግ፣

፭፡፩፬፡ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 22 ን/አንቀጽ 22.2 መሰረት በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ መፅደቅ የማያስፈልጋቸውን አነስተኛ የገንዘብ መጠን ያላቸው ግዥዎችን በሚመለከት፡-

ሀ/ በግዥ የስራ ክፍሉ ደረጃ እንዲፀድቁ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፣ ወይም

ለ/ ከስራው ጋር በቀጥታ ግንኙነት የሚኖረው የበላይ ኃላፊ እንዲያፀድቅ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፣

ሐ/ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚሰጠው ውክልና በገንዘብ መጠን ተገድቦ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ የስራ ኃላፊዎች ሊሰጥ ይችላል፣

፭፥፲፭፥ በዚህ መመሪያ በክፍል 10 ከአንቀጽ ፵፯፡-፭፭ መሠረት በግዥ አፈጻጸም ሂደት የሚደረጉ የዋጋ ማስተካከያዎችን አግባብነት የማረጋገጥ፣

፭፥፲፮፥ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 69 መሠረት እና በመ/ቤቱ የተከናወነውን የግዥ አፈጻጸም አስመልክቶ የቀረበ የመረጃ ፍላጎት ጥያቄ በግዥ ሥራ ክፍሉ ተቀባይነት በማጣቱ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ውሳኔ ይሠጣል፣

፭፥፲፯፥ የውል ሰነድ ይፈርማል፣ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ውል የመፈረም ውክልና ሊሰጥ ይችላል፣ በውሉ መሰረትም ግዥው መፈፀሙን ይከታተላል፣

5.18. በአዋጁ አንቀፅ 7 መሠረት ከግዥው ውስብስብነት ወይም መ/ቤቱ ካለው የግዥ አቅም በላይ በመሆኑ ምክንያት የመ/ቤቱ ግዥ የሚከተሉትን ተመርኩዞ በሶስተኛ ወገን እንዲፈፀም ሊያደርግ ይችላል፡-

ሀ/ ከሶስተኛ ወገን የሚያገኘው የግዥ አገልግሎት አዋጁን እና ይህንን መመሪያ ተከትሎ እንዲፈፀም ያደርጋል፣

ለ/ ለመ/ቤቱ ግዥ በሚፈፅመው ሶስተኛ ወገን እና በመ/ቤቱ መካከል ግልፅ የሆነ የስራ ክፍፍል እንዲኖር ያደርጋል፣

ሐ/ በዚህ ንዑስ አንቀፅ መሰረት በሶስተኛ ወገን ለሚፈፀሙ ግዥዎች የሚወሰኑ ውሳኔዎች በሙሉ በቅድሚያ ለመ/ቤቱ ቀርበው የተፈቀዱ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፭፥፲፱፥ በመስሪያ ቤቱ የተከናወኑ ግዥዎችን የሚገልጽ የግዥ አፈጻጸም ሪፖርት በኤጀንሲው በሚዘጋጁ ቅጾችና በሚወሰነው መሠረት የመላኪያ ጊዜውን ጠብቆ እንዲላክ ያደርጋል፣

፭፥፳፥ የሚከተሉትን ጨምሮ የመ/ቤቱን የግዥ አፈፃፀም በሚመለከት ኤጀንሲው ለሚያደርገው የግዥ ኦዲት ወይም ምርመራ ሥራ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡-

ሀ/ ለኦዲት ሥራው የሚያስፈልጉ ሰነዶች በሚፈለገው ጊዜ እንዲቀርቡ ማድረግ፣

ለ/ ለተመደቡት ኦዲተሮች አገልግሎት የሚሆን የስራ ቦታ እንዲመቻች ማድረግ፣

ሐ/ ስለተፈፀሙት ግዥዎች አካሔድ ሊያስረዳ የሚችል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ እንዲመደብ ማድረግ፣

፭፥፪፩፥ በግዥ ኦዲት ግኝቶች ላይ ከኤጀንሲው በተሰጡ አስተያየቶች መሰረት ተገቢ ማስተካከያ የማድረግ እና የተደረጉ ማስተካከያዎችንም ለኤጀንሲው ማሳወቅ፣

፭፥፪፪፥ ከመ/ቤቱ ግዥ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ለአቅራቢዎች የተፈጸሙ ክፍያዎችን በሚመለከት መረጃው ለሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት እንዲደርስ ያደርጋል፣

## ፮. የፅዴ ሥራ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት

በአዋጁ የተሰጡት ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው የግዥ የስራ ክፍል ቀጥሎ የተገለጹት ተጨማሪ ዝርዝር ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-

6.1. የመ/ቤቱን ፍላጎት በማሰባሰብ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 12/1 በተገለፀው መሠረት የግዥ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ከሌሎች መ/ቤቶች ፍላጎት ጋር በጋራ ግዥ እንዲፈጸምላቸው በኤጀንሲው የተወሰኑትን ይለያል፣

6.2. በአዋጁ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 "ሰ"፣ "ሸ" እና በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 24 ከተፈቀደው በስተቀር ማንኛውም የመንግስት ግዥ በኤጀንሲው ከተመዘገቡ እና የባንክ ሂሳብ ካላቸው አቅራቢዎች የተፈጸመ መሆኑን ያረጋግጣል፣

6.3. ከጠያቂ የስራ ክፍል ጋር በመተባበር የጨረታ ሰነድ አዘጋጅቶ ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ያቀርባል፣

6.4. በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ በሚሰጡ አስተያየቶች መሠረት የጨረታ ሰነዶችን ያስተካክላል፣

6.5. በአዋጁ አንቀጽ ፪፬ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ዘዴ የሚፈጸመውን ግዥ ጨምሮ የግዥው የገንዘብ መጠን በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከተገለጸው እና ከዚያ በላይ የሆነን ግዥ፣ የጨረታ ማስታወቂያው በጋዜጣ በወጣበት ተመሳሳይ ጊዜ በኤጀንሲው የመረጃ መረብ (ድረ - ገጽ) ላይ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል:-

| | | |
|---|---|---|
| ሀ/ | ለግንባታ ዘርፍ ሥራ ከብር | 10, 000,000.00 |
| ለ/ | ለዕቃ ግዥ | 3,000,000.00 |
| ሐ/ | ለምክር አገልግሎት | 2,000,000.00 |
| መ/ | ለሌሎች አገልግሎቶች | 1,000,000.00 |

6.6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፮፥፭ ከተገለጸው የገንዘብ መጠን በላይ ለሆኑ ግዥዎች የጨረታ አሸናፊው ከተመረጠና የግዥ ውል ከተፈረመ በኋላ ባሉት አምስት ቀናት ውስጥ በኤጀንሲው የመረጃ መረብ (ድረ-ገጽ) በተዘጋጀው ፎርም ላይ

አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመሙላት መረጃው ለሕዝብ ይፋ እንዲሆን ያደርጋል፣

6.7. የጨረታ ሰነድ ይሸጣል፣ በጨረታ ሰነዱ ላይ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ማብራሪያ ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፣

6.8. የመጫረቻ ሰነድ መቀበያ ሳጥን ያዘጋጃል፣ ያስተዳድራል፣

6.9. ጨረታ ይከፍታል፣ እስከተቻለ ድረስ የግዥ ጠያቂው ክፍል እና የውስጥ ኦዲት ተወካይ በጨረታ አከፋፈት ስነ-ስርዓቱ ላይ እንዲገኙ ይጋብዛል፣

6.10. በቀረቡ የመጫረቻ ሰነዶች ዋና ዋና ገፆች ላይ ማህተም እየተደረገ መፈረሙን ያረጋግጣል፤ የጨረታ መክፈቻ ቃለ-ጉባኤ እንዲያዝ ያደርጋል፣

6.11. የጨረታ ማስከበሪያ ይቀበላል፣ እንዲጠበቅ ያደርጋል፣ በጨረታ ሰነዱ በተገለጹት ሁኔታዎች መሠረት የጨረታ ማስከበሪያውን ለመንግሥት ገቢ ያደርጋል ወይም ተመላሽ ያደርጋል፣

6.12. የመጫረቻ ሰነዶች ኮፒዎች ጨረታውን እንዲገመግሙ ለተወከሉ ኮሚቴ አባላት መሰጠታቸውን እና ኦርጅናል ሰነዶቹ ለማጣቀሻነት በጥንቃቄ ተነጥለው መያዛቸውን ያረጋግጣል፣

6.13. የመጫረቻ ሰነዶችን በቡድን በመሆን ይገመግማል ወይም እንዲገመገሙ ያደርጋል፣ የግዥው መጠን በዚህ መመሪያ በአንቀጽ ፪፪ በን/አንቀጽ 2 ላይ ከተጠቀሰው በላይ በመሆኑ ምክንያት የግምገማ ውጤቱ ለግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ቀርቦ መፅደቅ ያለበት ከሆነ ለኮሚቴው ያቀርባል፣

6.14. የመጫረቻ ሰነድ በግዥ የሥራ ክፍል ሲገመገም መረጃዎች በትክክል መገልበጣቸውን፣ የሂሳብ ስሌት በትክክል መሰራቱን ወይም አንድን ተጫራች ሊጠቅም ወይም ሊጎዳ የሚችል ማንኛውም ተግባር አለመፈፀሙን ያረጋግጣል፣

6.15. በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ የሚፀድቁ ግዥዎችን በሚመለከት ከኮሚቴው ለሚቀርቡ የማብራሪያ ጥያቄዎች ማብራሪያ ይሰጣል ወይም ማብራሪያ እንዲሰጥ ያደርጋል፣

6.16. በሦስተኛ ወገን የሚከናወኑ ግዥዎችን በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሰረት የተፈፀሙ መሆኑን ይከታተላል፣ እንዲፈፀሙም ያስተባበራል

6.17. ከመንግስት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በሚሰጠው ውክልና መሰረት በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 22 በን/አንቀጽ 22.፪ ላይ ከተጠቀሱት የገንዘብ ገደቦች በታች የሆኑ ግዥዎችን ያፀድቃል፣

6.18. ለአሸናፊ እና ተሸናፊ ተጫራቾች የጨረታውን ውጤት ያሳውቃል፣

6.19. በውል ረቂቅ ላይ ከአቅራቢዎች ጋር ይደራደራል፣ በተሰጠው የውክልና ስልጣን መሰረት ይፈርማል ወይም በሚመለከተው የበላይ ኃላፊ እንዲፈረም ያደርጋል፣

6.20. የመንግስት መ/ቤቱ በውል ስምምነቱ መሰረት ግዴታውን መወጣቱን እና የውል መብቱ መከበሩን ያረጋግጣል፣

6.21. በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀሙ ግዥዎች ተሳታፊ የሚሆኑ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ይመርጣል፣ የዋጋ ማቅረቢያም ይሰበስባል፣

6.22. በተለይ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀሙ ግዥዎችን በሚመለከት በአሸናፊነት የሚመረጡት አቅራቢዎች ዋጋ የገበያ ዋጋ መሆኑን ያረጋግጣል፣

6.23. የግዥ ሰነዶችን ይይዛል፣ ይጠብቃል፣ ከሚመለከታቸው ሕጋዊ አካላት ማብራሪያ ሲጠየቅ ተገቢውን ማብራሪያ ይሰጣል፣

6.24. በአዋጁ አንቀጽ ፩፪(፪) በተገለጸው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመ/ቤቱን የግዥ አፈጻጸም ሂደት አስመልክቶ መረጃ እንዲሰጠው ጥያቄ ለሚያቀርብ አካል የተጠየቀውን መረጃ በተቻለ ፍጥነት ይሰጣል፡፡ ሆኖም መረጃውን የመስጠት ሂደት መ/ቤቱን ለተጨማሪ ወጪ የሚዳርገው ከሆነ መረጃ ፈላጊው ወጪውን እንዲሸፍን መደረግ ይኖርበታል፡፡

## ፯. የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

በአዋጁ የተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

7.1. በግዥ ስራ ክፍል የሚዘጋጀው ዓመታዊ ዕቅድ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ባስገባ መንገድ መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፣

ሀ/ የተለዩት የግዥ ፍላጎቶች ከመ/ቤቱ ፕሮግራሞች ጋር የሚጣጣሙ መሆኑን፣

ለ/ እያንዳንዱን ፍላጎት ለማሟላት ከግዥ የተሻለ ሌላ አማራጭ አለመኖሩን፣

ሐ/ እቅዱ ግዥን በጥቅል ለመፈፀም በሚያስችል መልኩ መዘጋጀቱን፣

መ/ ከመሥሪያ ቤቱ ልዩ ባህርይ አንፃር ሊሟሉ የሚገባቸው ሌሎች ሁኔታዎች መሟላታቸውን፣

7.2. በግዥ የስራ ክፍል የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላቱን ያረጋግጣል፦

ሀ/ በኤጀንሲው ለየግዥው አይነት የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ የተከተለ መሆኑን፣

ለ/ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ የተገለፁትን ሁኔታዎች ያሟላ መሆኑን፣

ሐ/ የመወዳደሪያ መስፈርቶቹ አድሏዊ ያልሆኑ፣ ግልፅ እና ተደራሽ መሆናቸውን፣

መ/ ተገቢ ቅፆችን፣በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሠረት እንደግዥው ዓይነት ሊገለጹ የሚገባቸውን ሁኔታዎች እና ሌሎችንም መሠረታዊ ጉዳዮች ማሟላቱን፣

7.3. የሚከተሉትን የማጣራት ሥራዎች በማከናወን በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 22/2/ ላይ እንደግዥው ዓይነት ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ የሆኑ ግዥዎች የግምገማ ሪፖርቶችን መርምሮ ያፀድቃል፣

ሀ/ ግምገማው በወጣው የጨረታ ሰነድ መሰረት መሰራቱን፣

ለ/ የአዋጁን እና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የጠበቀ መሆኑን፣

ሐ/ በግዥ ውሳኔ ሀሳቡ ላይ ለመድረስ የተከናወኑት ዝርዝር ግምገማዎችና አጠ ቃላይ የግዥ ሂደቱ መ/ቤቱ ለሚከፍለው ክፍያ ተመጣጣኙን ለማስገኘት የሚያስችሉ መሆኑን ማረጋገጥ፣

፯፥፬፥ በዚህ መመሪያ በንዑስ አንቀጽ ፳፫፥፯ ላይ የተገለጸውን ተግባራዊ ያደርጋል

7.፭. በቀረበው የግዥ ግምገማ ሪፖርት ላይ የሚሰጥ ማንኛውም አይነት የኮሚቴው ውሳኔ ምክንያታዊ መሆን ይኖርበታል፣

፯፥፯. አዋጁን፣ የአፈፃፀም መመሪያውን እና ሌሎች በኤጀንሲው የሚወጡ የአፈጻጸም ሥርዓቶች በተሻለ ሁኔታ ሊፈጸሙ የሚችሉበትን አሰራር ለኃላፊው ያማክራል፣

፯፥፯. በኮሚቴው ስለተከናወኑ የግዥ ተግባራት፣ ስላጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሔ ሀሳቦች የሚገልጽ ሪፖርት ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፣

፯፥፰፥ በመ/ቤቱ የግዥ አፈጻጸም ሂደት ውስጥ በኮሚቴው ስለተወሰኑ ውሳኔዎች በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ፣በኤጀንሲው ወይም በሌላ ሥልጣን ባለው አካል ሲጠየቅ ማብራሪያ ይሰጣል፣

7.9. የአፅዳቂ ኮሚቴው ሰብሳቢ እና ፀሐፊ የሚኖራቸው ዝርዝር የስራ ድርሻ እና ኃላፊነት እንዲሁም የስብሰባ ስነ-ስርዓት በዚህ መመሪያ አባሪ ቁጥር ፪ ላይ ተመልክቷል።

## 8. <u>ተጠያቂነት</u>

በአዋጅ አንቀጽ 10 እንደተደነገገው በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሥራ የተመደቡ ሠራተኞች ወይም የመንግሥት ግዥን እና ንብረትን ለማስተዳደር የተሾሙ ኃላፊዎች፣ የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ አባሎች በአዋጅ እና በዚህ መመሪያ መሠረት ስለሚወስዷቸው እርምጃዎች ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

# ክፍል 3

# <u>የግዥ ዕቅድ</u>

## 9. የግዥ ዕቅድ ስለማዘጋጀት

፱÷፩. ማንኛውም የመንግስት መሥሪያ ቤትና በሥሩ የተደራጁ አካላት የታቀዱ የሥራ ፕሮግራሞቻቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸውን ግዥ በወቅቱ ለመፈፀም የሚያስችል በመርሐ ግብር የተደገፈ የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት አለባቸው::

፱÷፪. የመንግስት መ/ቤቶች የሚፈጽሙት ግዥ ዕቅድን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት:: የሚዘጋጀው የግዥ ዕቅድ የሚከተሉትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚያስችል መሆን አለበት::

ሀ/ በአዋጁ አንቀፅ ፬ ላይ የተመለከቱትን የመንግስት ግዥ መርሆዎች ተግባራዊ ለማድረግ፣

ለ/ የመሥሪያ ቤቱን የሥራ ፕሮግራም ለማሳካት፣

ሐ/ የቁጥቁጥ ግዥን በመከላከል የመሥሪያ በቱን አሰራር ጊዜና ወጪ ቆጣቢ ለማድረግ፣

መ/ በግዥ አፈጻጸም ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶችን በቅድሚያ በመገንዘብ ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ፣

## 10. የግዥ ፍላጎትን መለየት፣ ማሰባሰብና ማደራጀት

፩፲÷፩. ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት የግዥ ፍላጎት በሚያዘጋጅበት ጊዜ የሚከተሉትን ማገናዘብ ይኖርበታል:-

ሀ/ ፍላጎቱ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ባለ እና ጥቅም ላይ ባልዋለ ሌላ ሐብት ወይም ንብረት ሊሟላ የማይችል መሆኑን ማረጋገጥ፣

ለ/ ፍላጎቱ ገበያ ላይ በሚገኝ ምርት ወይንም አገልግሎት ሊሟላ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሐ/ የግዥ ፍላጎቱ ጥቅም ላይ የማይውሉ እሴቶችን ያላካተተና መሥሪያ ቤቱን ለአላስፈላጊ ወጪ የማይዳርግ መሆኑን ማረጋገጥ፣

መ/ በተለይ ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግሉ ታስበው የሚከናወኑ ግዥዎች በሚሆኑበት ጊዜ የግዥ ፍላጎቱ ወደፊት የሚፈጠርን የፍላጎት ዕድገት ያገናዘበ መሆኑን፣

ሠ/ አስገዳጅ ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ ፍላጎቱ ገበያ ላይ በሚገኝ መደበኛ አቅርቦት ወይም ስታንዳርድ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ረ/ የግዥ ፍላጎቱ የማህበረሰቡን የአካባቢ ደህንነት እና ጥበቃ የማይጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ፤

፩፲÷፪. ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት በሥሩ ከሚገኙ የሥራ ክፍሎች የግዥ ፍላጎቶች በማሰባሰብ ዓመታዊ የግዥ ፍላጎታቸውን ለማወቅ የሚከተሉትን መፈጸም አለበት::

ሀ/ በመ/ቤቱ የሚገኙ ተጠቃሚዎች ዓመታዊ የግዥ ፍላጎታቸውን እንዲያቀርቡ መጠየቅ፣

ለ/ ከተጠቃሚዎች የቀረበውን ፍላጎት በግዥ ዓይነት፣ ብዛት፣ የጥራት ደረጃ እና በሚገኝበት ቦታ መለየት፣

ሐ/ መ/ቤቱ ልዩ ትኩረትና ቅድሚያ የሚሠጣቸውን ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራና አገልግሎቶችን መለየት፣

መ/ የቀረበው ፍላጎት በቂ አቅራቢ ያለው ወይም የሌለው መሆኑን ማጣራት፣

ሠ/ በመ/ቤቱ በተደረገ ጥናት ወይም ከሌሎች ምንጮች በተገኘ የገበያ መረጃ ለየግዥው የሚያስፈልገውን የዋጋ ግምት ማወቅ፣

ረ/ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በተጠቃሚዎቹ መዘጋጀቱን ወይም ወደፊት የሚዘጋጅ መሆኑን ማረጋገጥ፣

፩፲÷፫. የመንግስት መ/ቤቶች ከተጠቃሚዎች የተሰባሰበውን ፍላጎት፣ ከገበያ ጥናት የሚገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ እና የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የግዥ ፍላጎታቸውን ማደራጀት አለባቸው:-

ሀ/ በአዋጁ አንቀጽ ፬፪ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃ፣አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ግዥ በአንድ ላይ የሚፈጸምበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከ፭፲% (ከሃምሳ በመቶ) በላይ ድርሻ ያለውን የግዥ ዓይነት መሠረት በማድረግ መፈፀም፣

ለ/ እስከተቻለ ድረስ ተቀራራቢ እና ተመሳሳይ ፍላጎቶችን በአንድ ላይ ማሰባሰብ፣

ሐ/ በአንድ ላይ ለሚፈፀሙ ግዥዎች በቂ አቅራቢ በገበያ ላይ መኖሩን ወይም ግዥው በሚኖረው የአቅራቢ አይነት በተለያየ ምድብ /ሎት/ በመከፋፈል በቂ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል መሆኑን ማረጋገጥ፣

መ/ ግዥው ለአፈጻጸም አመቺ እና አደናቃፊ ሁኔታዎች የሌሉበት መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሠ/ እስከተቻለ ድረስ የአገር ውስጥ አምራቾች የመወዳደር እድልን በሚያሰፋ መልኩ ግዥው እንዲደራጅ ማድረግ ::

## 11. <u>የግዥ ዘዴ መምረጥ</u>

፩፩÷፩. የመንግስት መ/ቤቶች በግዥ ዕቅድ ዝግጅት ወቅት በአዋጁና በዚህ መመሪያ ለእያንዳንዱ የግዥ አይነት ከተፈቀዱት የግዥ ዘዴዎች ውስጥ አግባብነት ያለውን በመምረጥ በዕቅዱ ላይ ማመልከት አለባቸው::

፩፩÷፪. የመንግስት መ/ቤቱ የግዥ ዕቅዱን በሚያዘጋጅበት ወቅት የሚታወቁ የግዥ ፍላጎቶች ሁሉ በግዥ ዕቅዱ ውስጥ መካተታቸውን እና ለእያንዳንዱም ግዥ ተስማሚ የሆነ የግዥ ዘዴ መመረጡን ማረጋገጥ አለበት::

## 12. <u>የግዥ መፈፀሚያ ጊዜን መወሰን</u>

፩፪÷፩. የመንግስት መ/ቤቶች ለግዥ እቅድ ማዘጋጃ በኤጀንሲው የሚዘጋጀውን ቅፅ በመጠቀም በግዥ ሂደቱ ወስጥ ዋና ዋና ተግባራት የሚከናወኑበትን ጊዜ መወሰን አለባቸው፡፡ ለዚህም የሚከተሉትን እና እንደሚፈፀመው የግዥ ዓይነት ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ሊያስገቡ ይገባል፡፡

ሀ/ ግዥው በሚከናወንበት ጊዜ ከመስሪያ ቤቱ የሥራ ፕሮግራም ጋር የተጣጣመ መሆኑን፣

ለ/ በገበያ ላይ ሰፊ አቅርቦት የሚኖርበትን ጊዜ ታሳቢ ያደረገ መሆኑን፣

ሐ/ በግዥ መመሪያው አባሪ ፫ ላይ በተገለፀው መሠረት ዝቅተኛ የጨረታ መቆያ ጊዜን የጠበቀ እና እስከተቻለ ድረስ ሰፊ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል የመጫረቻ ሰነድ ማዘጋጃ ተጨማሪ ጊዜ የሰጠ መሆኑን፣

መ/ በተለይ ውስብስብ ለሆኑ እና ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ላላቸው ግዥዎች በቂ የሰነድ ማዘጋጃ፣ መገምገሚያ እና ማፅደቂያ ጊዜ የተሰጣቸው መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

፩፪÷፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩፪÷፩ ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ለየግዥ ዓይነቱ የሚወሰነው ጊዜ የግዥ አፈጻጸም ዋና ዋና ተግባራትን ለማከናወን ከሚያስፈልገው ጊዜ የረዘመ እንዳይሆን ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡

## 13. <u>የግዥ ዕቅድ ይዘት</u>

፩፫÷፩. የመንግስት መ/ቤቶች በዚህ መመሪያ ክፍል ፫ ላይ የሠፈሩትን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ እና ኤጀንሲው ለዚሁ ባዘጋጀውና በአባሪ ፩ ላይ በተመለከተው የግዥ ዕቅድ ማዘጋጃ ቅፅ በመታገዝ የግዥ ዕቅዳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ በዚህ መሰረት የሚዘጋጀው ዕቅድ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

ሀ/ የግዥውን ምድብ ፣ ቁጥር፣

ለ/ የግዥውን መግለጫ፣

ሐ/ የግዥውን መጠን፣

መ/ የግዥው ዝርዝር አፈጻጸም የሚከተላቸው አሠራሮች፣

ሠ/ ግዥውን ለማጠናቀቅ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት የሚፈፀሙበትን ጊዜ፣

ረ/ ለግዥው የሚያስፈልገውን በጀት መጠንና የፋይናንስ ምንጭ፣

ሰ/ ለግዥው ተስማሚ የሆነ ውል ዓይነት፣

ሸ/ በግዥ አፈጻጸም ሂደቱ የሚሳተፉ ዋና ዋና አካላትን የተሳትፎ ሁኔታ፣

ቀ/ ሌሎች እንደ መ/ቤቱ ባህርይ ትኩረትን የሚሹ ጉዳዮችን፣

፲፫፥፪. የመንግስት መ/ቤቱ ለግዥ ዕቅድ ዝግጅት በግብዓትነት የተጠቀመባቸውን ዋና ዋና መረጃዎች ምንጭ እና ሌሎች የግዥ ዕቅዱን ለተጠቃሚው የበለጠ ግልፅ ያደርጋሉ ብሎ የሚያስባቸውን መረጃዎች ከግዥ እቅድ ቅፁ ጋር በአባሪነት ማያያዝ ይኖርበታል::

## 14. የግዥ ዕቅድ የሚፀድቅበት እና የሚሻሻልበት ሁኔታ

፲፬፥፩. የግዥ ሥራ ክፍሎች ያዘጋጁትን ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ በመ/ቤቱ ለተቋቋመው የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ አቅርበው አስተያየት ከተቀበሉ በኋላ እቅዱን ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ አቅርበው ማፀደቅ አለባቸው::

፲፬፥፪. የመንግስት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ የመ/ቤቱ ግዥ አፈጻጸም ሂደት በፀደቀው የግዥ ዕቅድ መሠረት መመራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሠራር በመዘርጋት አፈጻጸሙን መከታተል አለበት::

፲፬፥፫. በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የፀደቀው ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ቅጅ በአዋጁ አንቀጽ ፩፩ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት ለአፈጻጸም በመ/ቤቱ ለሚገኙ የሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎችና ለኤጀንሲው መላክ አለበት::

፲፬፥፬. በመንግስት መ/ቤቶች የተዘጋጀው ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ተቀባይነት ካገኘና የዕቅዱ ቅጅ ለኤጀንሲው ከተላከ በኋላ የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ አፈጻጸሙን መከፋፈል ወይም በዕቅዱ ከተገለጸው አሠራር ውጭ መፈጸም አይችሉም::

፩፬፥፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩፬፥፬፥ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቶች አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት እና በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሲታመንበት በማንኛውም ጊዜ የግዥ ዕቅዳቸውን ሊያሻሽሉ ይችላሉ::

፩፬፥፮. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩፬፥፫ በተገለጸው መሠረት የተሻሻለው የግዥ ዕቅድ የመጀመሪያው ዕቅድ ለተላከላቸው በመ/ቤቱ ለሚገኙ የሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎችና ለኤጀንሲው መላክ አለባቸው::

## 15. ዓመታዊ የግዥ እቅድን ይፋ ማድረግ

ኤጀንሲው በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፩፬ ንዑስ አንቀጽ ፩፬፥፫ መሠረት ከመ/ቤቶች የተላከለትን ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ በማሰባሰብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፮ ንዑስ/አንቀጽ ፫ ከተገለፀው የገንዘብ መጠን በላይ የሆነን የግዥ ዕቅድ እንደአስፈላጊነቱ በየግዥው አይነት በመለየት ይፋ ያደርጋል:: ወይም መ/ቤቶች የተጠቀሰውን መረጃ በኤጀንሲው ድረ-ገጽ ላይ የሚያወጡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

# ክፍል 4

## የግዥ ዘዴዎችና አፈጻጸማቸው

## ፩፮. የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች

16.1. በአዋጁ አንቀጽ 22 መሠረት የሚከተሉት የግዥ ዘዴዎች ተፈቅደዋል

- ሀ/ ግልጽ ጨረታ፣
- ለ/ ውስን ጨረታ፣
- ሐ/ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸም ግዥ፣
- መ/ ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ፣
- ሠ/ በመወዳደሪያ ሃሣብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ፣
- ረ/ በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ፣

፩፮፥፪፥ በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልጽ የጨረታ ዘዴ መፈጸም አለባቸው።

፩፮፥፫፥ የመንግስት መ/ቤቶች ከግልጽ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው።

፩፮፥፬፥ በአዋጁ አንቀጽ ፪፪ ንዑስ አንቀፅ ፫ በተደነገገው መሠረት ከግልፅ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚጠቀም ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት በእነዚህ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያት እና ሁኔታዎች የሚገልጽ ሠነድ መያዝ ይኖርበታል።

## 17. ግልጽ ጨረታ ግዥ አፈፃፀም

የመንግስት መ/ቤቶች በግልፅ ጨረታ ዘዴ ግዥን ለመፈፀም በቢሮ የተዘጋጀውን የመደበኛ የጨረታ ሰነድ መጠቀም እና እንዲሁም በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 17.1 እና 17.2 የተዘረዘሩትን አፈፃፀሞች መከተል አለበት።

### 17.1. የብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ግዥ አፈፃፀም

የመንግስት መ/ቤቶች በብሄራዊ ደረጃ በግልፅ ጨረታ ዘዴ ግዥን ለመፈጸም በኤጀንሲው የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሠነድ መጠቀም እና በዚህ አንቀጽ ሥር የተዘረዘሩትን አፈፃፀሞች መከተል አለባቸው።

#### 17.1.1. ቅድመ ሁኔታዎች

የመንግስት መ/ቤቶች በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ዘዴ ግዥ ለመፈፀም የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

ሀ/ የሚፈለገው ግዥ በአገር ውስጥ ተጫራቾች ብቻ ሊያሟላ መቻሉን እና ግዥው በዚህ መመሪያ በንዑስ አንቀጽ 17.፪፥፪፥ ለዓለም አቀፍ ጨረታ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በታች መሆኑን፣ ወይም

ለ/ የግዥው መጠን በዚህ መመሪያ በንዑስ አንቀጽ ፩፯÷፪÷፪ ላይ ከተገለፀው የገንዘብ ገደብ በላይ ቢሆንም ምርቱ ወይም አገልግሎቱ በአገር ውስጥ ብቻ የሚገኝ መሆኑን፣

## ፩፯÷፪. ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ

የመንግስት መ/ቤቶች በአለም አቀፍ ደረጃ በግልፅ ጨረታ ዘዴ ግዥን ለመፈጸም በኤጀንሲው የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሠነድ መጠቀም እና በዚህ አንቀጽ ሥር የተዘረዘሩትን አፈፃፀሞች መከተል አለባቸው።

፩፯÷፪÷፩÷ በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ በአዋጁ አንቀጽ ፴፰ እና በዚህ ን/አንቀፅ ላይ በተደነገገው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል።

17.2.፪÷ በአዋጁ አንቀጽ ፴፰ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ የተመለከቱት ሌሎች የግዥ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ ዘዴ ግዥ ሊፈፀም የሚችለው የግዥው መጠን ከሚከተለው በላይ ሲሆን ነው፣

ሀ/ ለግንባታ ዘርፍ ሥራ ከብር 50,000,000.00 በላይ፣

ለ/ ለዕቃ ግዥ ከብር 10,000,000.00 በላይ፣

ሐ/ ለምክር አገልግሎት ከብር 2,500,000.00 በላይ፣

መ/ ለአገልግሎቶች ከብር 7,000,000.00 በላይ፣

፩፯÷፪.፫ በዓለምአቀፍ ግልጽ ጨረታ በሚፈፀም የዕቃ ግዥ ተሳታፊ የሚሆኑ ተጫራቾች ራሳቸው የዕቃው አምራቾች ካልሆኑ እንደአስፈላጊነቱ በመሥሪያ ቤቶች ሲጠየቁ ከአምራቹ የተሰጣቸውን ውክልና ማቅረብ አለባቸው።

፩፯.2.፬ በዚህ መመሪያ በክፍል 7 እና በክፍል 8 ከተገለጸው ዝርዝር የግዥ አፈፃፀም በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ የሚከተሉትን ማካተተ አለበት:-

ሀ/ የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ እና የጨረታ ሠነዱ የሚዘጋጀው በእንግሊዝኛ ቋንቋ መሆን አለበት፣

ለ/ የጨረታው ጥሪ በቂ የሥርጭት ሽፋን ያለውና የውጭ ተጫራቾችን ለውድድር ሊጋብዝ በሚችል ጋዜጣ ላይ መውጣት ያለበት ሲሆን፣ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ ፫ ላይ ከተመለከተው የገንዘብ ገደብ በላይ ለሆነ ግዥ በኤጀንሲው ድረ ገጽ ላይ መውጣት አለበት። በተጨማሪም በርካታ

ተጫራቾችን ለማግኘት እንዲቻል የጨረታውን ጥሪ እንደአስፈላጊነቱ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ድረ-ገጽ ላይ ማወጣት እና ለተለያዩ ሃገራት ኤምባሲዎች ማሳወቅ ይቻላል፡፡

ሐ/ ተጫራቾች ተገቢ የመጫረቻ ሠነድ ማዘጋጀት እንዲችሉ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 34 ላይ በተገለጸው መሠረት በቂ ጊዜ መሠጠት አለበት፣

መ/ የሚዘጋጀው የፍላጎት መግለጫ የአገር ውስጥ ደረጃን ያሟላና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መሆን አለበት፣

ሠ/ የውጭ አገር ተጫራቾች የሚያቀርቡት የመጫረቻ ዋጋና የጨረታ ማስከበሪያ በቀላሉ ሊመነዘር በሚችልና በአለም አቀፍ ንግድ በሚሠራበት የገንዘብ ዓይነት ሊሆን ይገባል፡፡

ረ/ የግዥ ፍላጎቱን ለማሟላት አሸናፊው የውጭ አገር ተጫራች ከአገር ውስጥ የሚጠቀመው ግብዓት በሚኖርበት ጊዜ ከአጠቃላይ የውሉ ክፍያ በብር ሊከፈል የሚገባው መጠን በዋጋ ማቅረቢያው ሠንጠረዥ ላይ መመልከት ይኖርበታል፡፡

ሰ/ በአለም አቀፍ ግዥ የሚፈፀሙ ውሎች አዋጁን እና የአፈፃፀም ድንጋጌዎችን እስካልተቃረኑ ድረስ አለም አቀፍ ንግድ የሚሰራባቸውን የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች ተመርኩዘው መፈፀም አለባቸው፣

ሸ/ በውሉ በተለየ ሁኔታ ካልተመለከተ በስተቀር በውል አፈፃፀም ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች በኢትዮጵያ ሕግ ሊዳኙ ይገባል፡፡

## <u>፩፯፥፫. የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ</u>

፩፯፥፫.፩ የመንግስት መ/ቤቱ ግዥው ከሚኖረው የተለየ ባሕርይ አንፃር በቅድሚያ የተወዳዳሪዎችን ብቃት መሠረት በማድረግ ግምገማ ማድረግ አለብኝ ብሎ ሲያምን እንደግዥው አይነት ብሔራዊ ወይም ዓለም ዓቀፍ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፩፯፥፫.፪ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ የሚያስፈልጋቸው ግዥዎች ከሚከተሉት ሁኔታዎች ቢያንስ አንዱን የሚያሟሉ መሆን ይኖርባቸዋል

ሀ/ በጣም ከፍተኛ ዋጋ ያለው ወይም በባህርይው ውስብስብ የሆነ የዲዛይን፣ የማምረትና የተከላ ሥራ በአንድ ድርጅት መጠናቀቅ ያለበት የግንባታ፣ የማምረቻ መሳሪያ ወይም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ግዥ ሲሆን፣ ወይም

ለ/ የሚቀርበው ዕቃ ወይም መሣሪያ ጥራትና ጠቀሜታ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው እና የተከላ አገልግሎትን ያካተተ ሲሆን፣ ወይም

ሐ/ የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ግዥ በመሆኑ ብቃታቸው በቅድመ ብቃት ምዘና የሚረጋገጥ ተጫራቾች ብቻ በውድድሩ ተካፋይ መሆን እንደሚገባቸው ሲታመንበት፣

፲፯፥፫.፫ ጨረታው የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ጥሪ መሆኑ በማስታወቂያው ላይ መገለፅ ይኖርበታል።

17.3.፬ የቅድመ ብቃት ግምገማ ለማድረግ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ የቅድመ ብቃት ጨረታ በኤጀንሲው የተዘጋጀውን የቅድመ ብቃት ጨረታ መደበኛ የጨረታ ሠነድ መሠረት በማድረግ ይሆናል ። የቅድመ ብቃት መምረጫ መሥፈርት እንደግዥው ባህርይና ዓይነት ሊለያይ የሚችል ቢሆንም ተወዳዳሪ ድርጅቶቹ እንዲያቀርቡ የሚጠየቁት ማስረጃ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማካተት ይኖርበታል ።

ሀ/ በተመሳሳይ ሥራ ወይም ዕቃ ማምረት ላይ ድርጅቱ ያለው ልምድ፣

ለ/ ድርጅቱ ሥራውን ለማከናወን ወይም ዕቃውን ለማምረት የሚያስችል በቂ የሰው ኃይል፣ ማሽነሪ፣ የማምረቻ መሣሪያ ብዛት እና የተሟላ ኢንፍራስትራክቸር ያለው መሆኑን፣

ሐ/ ድርጅቱ አሁን በመሥራት ላይ ያለው የግንባታ ሥራ ወይም በማምረት ላይ ያለው ዕቃ ብዛት ወይም መጠን፣

መ/ ድርጅቱ የውል ግዴታውን ለማጠናቀቅ የሚያስችል በቂ የገንዘብ አቅም እና መልካም ዝና ያለው መሆኑን፣

17.3.፭ የተጫራቾች ግምገማ የሚከናወነው ለቅድመ ብቃት ማረጋገጫ በመንግስት መ/ቤቱ የተዘጋጀውን መሥፈርት መሠረት በማድረግ ይሆናል።

17.3.፮ ለቅድመ ብቃት ውድድሩ ያመለከቱ ተጫራቾች በሙሉ የግምገማ መሥፈርቱን እስካሟሉ ድረስ ምንም ዓይነት የቁጥር ገደብ ሳይደረግ በሚቀጥለው ውድድር እንዲሳተፉ መደረግ አለበት።

17.3.፯ የመንግስት መ/ቤቶች በቅድመ ብቃት ውድድር የሚሳተፉ ድርጅቶች በሽርክና ወይም በጋራ መወዳደር እንዲችሉ ሊፈቅዱ ይችላሉ:: ሆኖም የቅድመ ብቃት ውድድሩን በግል ያለፉ ተወዳዳሪዎች በግዥው ሂደት የሚኖራቸውን ውድድር እንደማያጠብ በመ/ቤቱ ካልታመነ በስተቀር በጋራ ወይም በሽርክና የመጫረቻ ሠነዱን እንዲያቀርቡ መፈቀድ የለበትም::

17.3.፰ በንዑስ አንቀጽ ፩፯÷፫÷፯÷ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በጋራ ወይም በሽርክና ለቅድመ ብቃቱ ውድድር ቀርበው ይህንኑ መሰረት በማድረግ በተካሄደ ግምገማ ለሚቀጥለው ጨረታ ያለፉና የተመረጡ ተጫራቾች በጨረታው በግል እንዲወዳደሩ አይፈቀድላቸውም::

17.3.፱ የቅድመ ብቃቱ ግምገማ ውጤት እንደታወቀና በመ/ቤቱ ተቀባይነት እንዳገኘ ውጠ ጌቱ በጨረታው እንዲሳተፉ ለተመረጡትና ላልተመረጡት ተጫራቾች በእኩል ሁኔታ ሊገለጽላቸው ይገባል::

17.3.1፲ አንድ ተጫራች በጨረታው ግምገማ አሸናፊ ለመሆን ቢችልም ለቅድመ ብቃት ውድድር የሰጠው መረጃ የተሳሳተ ከሆነ ወይም በቅድመ ብቃት ውድድሩ ወቅት የነበረው ብቃት ባለመኖሩ ውሉን በሚጠበቅበት ሁኔታ ለመፈጸም አለመቻሉ በበቂ ሁኔታ ከተረጋገጠ የመንግስት መ/ቤቱ ድርጅቱ ውሉን እንዲፈርም ላይፈቅድ ይችላል::

፩፯÷፫.፩፩÷ በዚህ መመሪያ በክፍል 7 እና 8 የተመለከተውን ስርአት በመከተል የሚዘጋጀው የጨረታ ሠነድ በቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ውድድሩ ተቀባይነት ላገኙት ተጫራቾች በየአድራሻቸው እንዲላክላቸው ወይም ከመ/ቤቱ ቀርበው እንዲወስዱ የሚደረግ ሲሆን፣ ቀሪው የግዥ አፈፃፀም ስርአት በዚህ መመሪያ የተደነገገውን አሠራር ተከትሎ ይፈፀማል::

## 17.4. <u>የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ ጨረታ</u>

17.4.1. የመንግስት መ/ቤት የሚገዛው የምክር አገልግሎት ግምታዊ ዋጋ ከብር 300 ሺህ /ሦስት መቶ ሺህ/ የማይበልጥ ሲሆን በምክር አገልግሎቱ አቅርቦት ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸውን ዕጩ ተወዳዳሪዎች በመጋበዝ ጥሪ ማድረግ አለበት::

ሀ/ ለፍላጎት መግለጫ የሚደረገው ጥሪ እንደሁኔታው በዚህ መመሪያ አንቀፅ ፫፫ ወይም ፩፯÷፪.፬ (ሀ) እና (ለ) ላይ የተመለከተውን ተከትሎ የሚፈፀም ሲሆን በተጨማሪነት ጥሪው የተደረገው ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች ፍላጎታቸውን እንዲገልፁ መሆኑን ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

ለ/ የፍላጎት መግለጫ ጥሪው የሚፈለገውን የምክር አገልግሎት አይነት፣ የሚጠበቀውን ውጤት፤ ጊዜውን፤ አማካሪው ሊኖረው የሚገባውን ብቃት፤ የስራ ልምድ እና የመሳሰሉትን የያዘ እና ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሊያቀርቡት የሚገባውን መረጃ ዝርዝር እና የሚያቀርቡበትን ቦታና ጊዜ የሚገልጽ መሆን አለበት፣

ሐ/ ፍላጎታቸውን ያሳወቁ ተወዳዳሪዎች ያቀረቡት መረጃ ተገምግሞ የተፈለገውን የምክር አገልግሎት ለመስጠት ከፍተኛ ብቃት ያላቸው በቅደም ተከተላቸው መሠረት እስከተቻለ ድረስ ከሦስት ያላነሱ እና ከሰባት ያልበለጡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ተመርጠው በዚህ መመሪያ አንቀፅ ፩፰ መሰረት የመወዳደሪያ ሐሳባቸውን እንዲያቀርቡ መደረግ ይኖርበታል፡፡

## 18. <u>በመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ</u>

፩፰.፩ **የመንግስት መ/ቤት የምክር አገልግሎት ግዥን የመወዳደሪያ ሐሣብ በመጠየቅ መፈፀም የሚኖርበት** ሲሆንና የግዥው ግምታዊ የገንዘብ መጠን ከብር 300 ሺህ (ሦስት መቶ ሺህ) በላይ በሚሆንበት ጊዜ በዚህ መመሪያ በን/አንቀፅ ፩፯÷፬ መሰረት የፍላጎት መጠየቂያ ጥሪ ማካሄድ ይኖርበታል፡፡

18.፪ የመወዳደሪያ ሐሳብ ለማቅረብ የሚጋበዙት አማካሪዎች አመራረጥ የሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ይፈፀማል፤

ሀ/ በዚህ መመሪያ ን/አንቀፅ ፩፯÷፬ መሰረት በወጣው የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ ጥሪ መሠረት ፍላጎታቸውን ከገለፁ አማካሪዎች ውስጥ የተሻለ ብቃት ያላቸውን በመምረጥ፣

ለ/ የሚፈለገውን የምክር አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ አማካሪዎች ውስን ሲሆኑ እነዚህን አማካሪዎች በሙሉ በመጋበዝ፣

ሐ/ የግዥው ግምታዊ የገንዘብ መጠን ከብር ፫፲፲ ሺህ (ሦስት መቶ ሺህ) በታች ሲሆን ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ በመምረጥ፣

፩፰.፫ የመወዳደሪያ ሐሳብ ለማቅረብ የሚጋበዙት አማካሪዎች ቁጥር እስከተቻለ ድረስ ከሦስት ያላነሰ እና ከሰባት ያልበለጠ መሆን ይኖርበታል፡፡

፩፰.፬ መ/ቤቱ የመወዳደሪያ ሐሳብ እንዲያቀርቡ ለተመረጡ አማካሪዎች የጥሪ ደብዳቤ በተመሳሳይ ጊዜ በአድራሻቸው መላክ አለበት፡፡ ለግዥው የተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ያለ ክፍያ ሊሰጥ እንደሚገባ መ/ቤቱ ሲያምን ከጨረታ ጥሪው ደብዳቤ ጋር የጨረታ ሰነዱን ሊልክላቸው ይችላል፡፡

፩፰.፭ ለመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ኤጀንሲው ያዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ በመጠቀም እንዲሁም በዚህ መመሪያ በክፍል 6 የተቀመጠውን ስርአት በመከተል የሚዘጋጅ መሆን ይኖርበታል፡፡

፩፰.፮ የመንግስት መ/ቤቱ ከተመረጠው አማካሪ ጋር የሚያደርገው ድርድር መሠረታዊውን የጨረታ ይዘትና የሥራ ጥራት የማይቀይር ሆኖ ስለስራው ይዘት፣ ስለአሰራር ዘዴው፣ በስራው ስለሚሰማራው የሰው ኃይል እና መሳሪያ፣ ስለሪፖርት አቀራረብ እና ይዘት በመሳሰሉት ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል፡፡

፩፰.፯ በንዑስ አንቀ18.፮ መሰረት የሚደረገው ስምምነት የመንግስት መ/ቤቱን ጥቅም የሚጎዳ ወይም ለተመረጠው አማካሪ ከሌሎች ተጫራቾች አንፃር ፍትሐዊ ያልሆነ ጥቅም የሚያሰጠው መሆን የለበትም፡፡

፩፰.፰ በንዑስ አንቀጽ ፩፰.፱ ስር የተገለጹት የመረጣ ዘዴዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሌሎች የጨረታ አፈጻጸም ሂደቶች በዚህ መመሪያ በክፍል 6፣ 7 እና 8 ስር የተገለጹትን የግልጽ ጨረታ አሠራሮች በመከተል የሚፈጸሙ ይሆናል፡፡

፩፰.፱ ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ ፩፰፥፩፲ እስከ 18.15 በተገለጹት የመምረጫ ዘዴዎች ለሚፈጸሙ ግዥዎች የሚቀርበው የመጫረቻ ሰነድ በቴክኒክና በዋጋ ማቅረቢያ ተለይቶ በሁለት ኤንቬሎፕ ታሽጎ መቅረብ የሚኖርበት ሲሆን ለምክር አገልግሎቱ የሚዘጋጀው የመምረጫ መስፈርት እና የሚደረገው ግምገማ የሚከተለውን አሠራር ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

18.10. በጥራት እና በዋጋ ላይ የተመሠረተ መረጣ፣

፩፰.1፲.፩ የመንግስት መ/ቤቶች ለምክር አገልግሎት የጨረታ ሠነድ በሚያዘጋጁት፣ በዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚቀርበውን እያንዳንዱን የቴክኒክ ሃሳብ በሚገመግሙበት እና በሚያወዳድሩበት ወቅት የሚከተሉትን መስፈርቶች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል:-

ሀ/ ከሚሰጠው ሥራ ጋር በተገናኘ አማካሪው ያለውን ልምድ፣

ለ/ በሥራ ላይ እንዲውል የቀረበውን የጥናት ዘዴ ደረጃ፣

ሐ/ ምክሩ ለመንግስት መሥሪያ ቤቱ የሚያስገኘውን ዕውቀት፣

መ/ የውጭ ተወዳዳሪዎች በሚያቀርቧቸው የመወዳደሪያ ሐሳቦች ኢትዮጵያውያን ዜጎች በምክር ሥራው ሂደት በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የሚኖራቸውን ተሳትፎ፣

፩፰.፩፲.፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩፰፥፩፲.፩፥ ላይ ለተመለከቱት መስፈርቶች መ/ቤቱ እንደሚገዛው የምክር አገልግሎት ዓይነት ለእያንዳንዱ መስፈርት ከዚህ በታች በተገለጸው መሠረት ነጥብ መስጠት ከመቶ መመዘን ይኖርበታል ይኖርበታል::

ሀ/ የአማካሪው ልዩ ልምድ .......................... ከ፭ እስከ 1፲ ነጥብ

ለ/ ሥራ ላይ ይውላል ተብሎ የቀረበው የምክር ዘዴ ........ ከ፪፲ እስከ ፭፲ ነጥብ

ሐ/ ዕውቀት የማሸጋገር ችሎታ ....................... ከ፭ እስከ 1፲ ነጥብ

መ/ በምክር አገልግሎቱ ለሚሳተፉ ቁልፍ ባለሙያዎች... ከ፫፲ እስከ ፯፲ ነጥብ

ሠ/ የኢትዮጵያውን ተሳትፎ ........................... ከ፭ እስከ 1፲ ነጥብ

ረ/ ከዚህ በላይ የተቀመጡት ነጥቦች ድምር ከ100 መብለጥ የለበትም

፩፰.፩፲.፫ በቴክኒክ ብቃት ፯፲% (ከመቶ ሰባ) በታች ያገኙ ተወዳዳሪዎች ውድቅ ተደርገው 70% እና ከዚያ በላይ የሚያገኙት ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ፖስታ ተጫራቾች በተገኙበት ይከፈታል::

፩፰.1፲.፬ በቴክኒክ ብቃት ግምገማ ለዋጋ ውድድር የሚያበቃቸውን ዝቅተኛ ውጤት ያላመጡ ተጫራቾች የዋጋ ፖስታ ሳይከፈት እንዲመለስ መደረግ አለበት::

18.10.5 የምክር አገልግሎቱ የሚገኘው ከውጭ አማካሪዎች ካልሆነ በስተቀር የአገር ውስጥ አማካሪዎች የሚያቀርቡት ዋጋ ለግምገማ ሲባል የአገር ውስጥ ታክስን ይጨምራል:: ከዚህ በላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ

የአገር ውስጥ እና የውጭ አማካሪዎች የሚያቀርቡት ዋጋ የመጓጓዣ፣ የትርጉም፣ የጽሕፈት ሥራ ወጪን እና የመሳሰሉትን ሊጨምር ይችላል፡፡

፩፰.1፲.፮÷ ዝቅተኛ የመጫረቻ ዋጋ ላቀረበው ተወዳዳሪ ለዋጋ በሙሉ ነጥብ የሚሰጠው ሲሆን፣ በተነፃፃሪ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበው ተወዳዳሪ አነስተኛ ነጥብ ይሰጣል ሌሎች ተወዳዳሪዎችም የሚያገኙት ነጥብ ባቀረቡት ዋጋ ላይ በመመስረት ተሰልቶ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፩፰.1፲.፯÷ የቴክኒክ ግምገማ የነጥብ ድርሻ 80% /ሰማንያ በመቶ/፣ የዋጋ ግምገማ የነጥብ ድርሻ ደግሞ ፪፲% (ሃያ በመቶ) ይሆናል፡፡

፩፰.1፲.፰÷ ለቴክኒክ ብቃት ደረጃ እና ለዋጋ የተሰጡትን ነጥቦች በማዳመር በአጠቃላይ ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘው ተወዳዳሪ የጨረታው አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፡፡

፩፰.1፲.፱÷ በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈፀም የምክር አገልግሎት ግዥ በዚህ መመሪያ በክፍል 7 እና 8 የተገለጸውን የግዥ አፈጻጸም ሂደት በተጨማሪነት መሠረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## ፩፰.፩፩ <u>በሚከናወነው የሥራ ጥራት ላይ የተመሠረተ መረጣ፣</u>

፩፰.1፩.፩ በሥራ ጥራት ላይ የተመሠረተ መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የምክር አገልግሎቱ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲያሟላ ይሆናል:-

ሀ/ የምክር አገልግሎቱ ውስብስብና የተለየ የሙያ ብቃት የሚጠይቅ በመሆኑ ለዚሁ ግዥ የተሟላ ማጣቀሻ ሠነድ ወይም ቢጋር ማዘጋጀት የማይቻል ሲሆን ወይም ከአማካሪው የሚገኘውን የምክር አገልግሎት ዓይነት ለይቶ ማወቅ የማይቻል ሲሆን ወይም አማካሪው የራሱን የፈጠራ ችሎታ ተጠቅሞ የመወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረብ የሚኖርበት ሲሆን፣

ለ/ ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን አማካሪዎች ማግኘት አስፈላጊ በሚሆንባቸው እና የወደፊት ውጤታቸው አሳሳቢ የሚሆን ከፍተኛ ጉዳዮች ሲሆኑ፣

ሐ/ የምክር አገልግሎቱ በተለያዩ አማራጭ መንገዶች ሊቀርብ የሚችል በመሆኑ ምክንያት የሚቀርቡትን ሀሳቦች በተመሳሳይ ሁኔታ ማወዳደር አስቸጋሪ እንደሚሆን ሲታመን፣

፩፰.፩፩.፪ የቴክኒክ ሀሳቦችን የያዙ ፖስታዎች ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈቱ ይደረጋል::

፩፰.፩፩.፫ በቴክኒክ ግምገማ ከፍተኛ ውጤት ያገኘው ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል

፩፰.፩፩.፬ በንዑስ አንቀጽ ፩፰÷፩፩.፫ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በውድድሩ አሸናፊ የሆነው ተጫራች ያቀረበው ዋጋ ከመ/ቤቱ የመክፈል አቅም በላይ ከሆነና በቴክኒክ ግምገማው ውጤት ሁለተኛ የወጣው ተጫራች ያቀረበው ዋጋ ከመ/ቤቱ የመክፈል አቅም ጋር የሚመጣጠን ከሆነ ግዥውን ሁለተኛ ከወጣው ተጫራች መፈፀም ይቻላል::

፩፰.1፩.፭ በጨረታው አሸናፊ ከሆነው ተጫራች ጋር የውል ስምምነት እንደተፈረመ የሌሎች ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ፖስታ ሳይከፈት ለተጫራቾቹ ተመላሽ መደረግ አለበት::

፩፰.፩፪ <u>በቁርጥ በጀት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን መረጣ፣</u>

ሀ/ በቁርጥ በጀት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የሚፈለገው የምክር አገልግሎት ውስብስብነት የሌለው፣ በትክክል ሊገለፅ የሚችል ሲሆን እና ለዚሁ ተግባር የተፈቀደው በጀት ጣሪያ ያለው ከሆነ ነው::

ለ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፴፪ በን/አንቀጽ 42.3 በፊደል ተራ "ሀ" መሠረት የቴክኒክ ሀሳቦችን የያዙ ፖስታዎች ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈቱ ይደረጋል::

ሐ/ የቴክኒክ ግምገማው በንዑስ አንቀጽ ፩፰.1፲.፩፣ ፩፰.1፲.፪ ፩፰.1፲.፫ እና ፩፰.1፲.፬ ላይ የተመለከቱትን ሥርዓቶች ተከትሎ የሚፈጸም ይሆናል::

መ/ በቴክኒክ ግምገማው ተፈላጊውን መስፈርት ያሟሉት ተጫራቾች የዋጋ ማቅረቢያ ፖስታ ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈት ይደረጋል:: ለጨረታው በእያንዳንዱ ተጫራች የቀረበውን ዋጋ በመክፈቻው ሥነ-ሥርዓት ላይ የተገኙ ተጫራቾች እንዲያውቁ መደረግ አለበት::

ሠ/ ለጨረታው ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ያቀረቡ ተጫራቾች ከጨረታው ውጭ እንዲሆኑ ይደረጋል::

ረ/ ለጨረታው ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ዋጋ ያቀረበና በአጠቃላይ ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘ ተጫራች የውድድሩ አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል እንደአስፈላጊነቱም ዋጋን ያልጨመረ ድርድር ሊደረግ ይችላል::

## ፩፰.፩፫ <u>በዝቅተኛ ዋጋ ላይ የተመሠረተ መረጣ፣</u>

፩፰.፩፫.፩ በዝቅተኛ ዋጋ ላይ የተመሠረተ መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የሚገዛው የምክር አገልግሎት የባለሙያውን ልዩ ችሎታ የማይጠይቅ፣ ውስብስብ ያልሆነና ስታንዳርድ ያለው ወይም በተመሳሳይና ወጥ በሆነ አሠራር ሊከናወን የሚችል ሲሆን ነው::

፩፰.፩፫.፪ መ/ቤቶች በዚህ የመረጣ ዘዴ ተጫራቾችን ለመገምገም ሲፈልጉ ዝቅተኛውን የቴክኒክ መመዘኛ ነጥብ መጠን በመወሰን ከአቅራቢዎች ዝርዝር ለተመረጡ ተጫራቾች በሚሰጠው የመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ ሰነድ ላይ ይህንኑ ነጥብ በግልጽ ማመልከት አለባቸው::

፩፰.1፫.፫ የቴክኒክ ሀሳቦችን የያዙ ፖስታዎች ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈቱ በማድረግ የቴክኒክ ግምገማ መከናወን ይኖርበታል::

፩፰.፩፫.፬ በግምገማው ውጤት ለቴክኒክ ብቃት የተቀመጠውን ዝቅተኛ መሥፈርት ያላሟሉ ተወዳዳሪዎች ከጨረታው ውጭ እንዲሆኑ ይደረጋል::

፩፰.፩፫.፭ በቴክኒክ ብቃት ግምገማ ለዋጋ ውድድር የሚያበቃቸውን ዝቅተኛ ውጠ ኀት ያላመጡ ተጫራቾች የዋጋ ፖስታ ሳይከፈት እንዲመለስ መደረግ አለበት::

፩፰.1፫.፮ በቴክኒክ ግምገማ ውጤታቸው ለዋጋ ውድድር ያለፉት ተወዳዳሪዎች የዋጋ ፖስታ ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈት ይደረጋል:: ለጨረታው በተጫራቾች የቀረበው ዋጋ በመክፈቻው ሥነ-ሥርዓት ላይ የተገኙ ተጫራቾች እንዲያውቁት መደረግ አለበት::

፩፰.፩፫.፯ በቴክኒክ ግምገማ ለብቃት ማረጋገጫ የተቀመጠውን ዝቅተኛ መሥፈርት ካሟሉት ተወዳዳሪዎች መካከል አነስተኛ ዋጋ የሠጠው ተጫራች የውድድሩ አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል::

18.14፥ <u>በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሠረተ መረጣ፣</u>

18.14.1. በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሠረተ መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው ለአማካሪው የሚሰጠው ሥራ አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት የመወዳደሪያ ሀሳቦችን ለማዘጋጀት እና ለመገምገም የሚያስፈልገው ጊዜና ወጪ ከሥራው ጋር የማይመጣጠን ሲሆን ነው::

18.14.2. ይህ ዘዴ ጥቅም ላይ የሚውለው የምክር አገልግሎቱ ወጪ ከብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ ብር/ የማይበልጥ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ ነው::

18.14.3. ለዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚዘጋጀው ማጣቀሻ/ቢጋር/ አማካሪው ያለውን የሥራ ልምድና የብቃት ደረጃ እንዲገልጽ የሚጠይቅ መሆን አለበት::

18.14.4. ከአቅራቢዎች ዝርዝር ወይም መ/ቤቱ ያለውን መረጃ በመጠቀም በውድድሩ እንዲሳተፉ በመረጣቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበውን መረጃ መሠረት በማድረግ በሚከናወን ግምገማ የተሻለ ሆኖ የተመረጠው ዕጩ ተወዳዳሪ የቴክኒክና የዋጋ ማቅረቢያ ሐሳቡን በአንድ ላይ እንዲያቀርብ በማድረግና በመደራደር በሚደረስበት ስምምነት መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል::

፩፰፥፩፭፥ <u>አንድ አማካሪ የሚመረጥበት ሁኔታ፣</u>

የመንግሥት መ/ቤቶች የምክር አገልግሎት ግዥን ከአንድ አማካሪ ለመፈጸም የሚችሉት በአዋጁ አንቀጽ 40 እና ፬፩ እንዲሁም በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፪፩ የተገለጹት ሁኔታዎች መሟላታቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው:::

## ፩፱. <u>በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ</u>

፩፱.፩ በአዋጁ አንቀጽ ፴፮ እና ፴፯ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ በዚህ መመሪያ በክፍል 7 እና 8 እንደግዥው ዓይነት ለብሔራዊ ወይም ለዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የተዘረጋውን ሥርዓት ይከተላል።

፩፱.፪ በንዑስ አንቀፅ 1፱.፩ የተመለከተው ቢኖርም ለሁለት ደረጃ ጨረታ የሚደረገው የጨረታ አፈፃፀም የሚከተሉትን ልዩ ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ተፈጻሚ ይሆናል’

19.፪.፩ በጨረታ ጥሪው ላይ ግዥው በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም መሆኑ መገለፅ ይኖርበታል፣

፩፱.፪.፪ በመጀመሪያው ዙር ጨረታ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ ዋስትና እንዲያቀርቡ አይጠየቁም፣

፩፱.፪.፫ በመጀመሪያ ዙር የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ የመንግስት መ/ቤቱን አጠቃላይ ፍላጎት የሚገልፅ ሆኖ አላማው ከዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡ ሐሳቦች መሠረት ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት ስለሆነ አስፈላጊ ናቸው የሚባሉ መጠይቆችን እና መግለጫዎችን ማካተት ይኖርበታል፣

፩፱.፪.፬ በመጀመሪያው ዙር ጨረታ ላይ የተጫራቾች መገኘት ሳያስፈልግ በዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበው የቴክኒክ ሐሳብ ማቅረቢያ ሰነድ በጨረታ ጥሪው በተገለፀው ሁኔታ እንዲከፈት ይደረጋል፣

፩፱.፪.፭ የመጀመሪያው ዙር ግምገማ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበውን ሐሳብ በመመርመር ለሁለተኛው ዙር ጨረታ የሚያገለግለውን የፍላጎት መግለጫ እና በጨረታው ሊሳተፉ የሚገባቸውን ተጫራቾች መለየት የሚያስችል መሆን ይኖርበታል። ከዚህ በተጨማሪም፡-

ሀ/ በግምገማው ወቅት እንደአስፈላጊነቱ ከሁሉም ወይም ከተወሰኑ ወይም ከአንድ ከተለየ ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር የመንግስት መ/ቤቱ ውይይት ሊያደርግ ይችላል፣

ለ/ ከላይ በፊደል ተራ (ሀ) ላይ በተገለፀው መሰረት የሚደረገው ውይይት እጩ ተወዳዳሪዎች የሰጡትን ሐሳብ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ እና በተሻለ የዳበረ ሐሳብ ለማመንጨት ያለመ ሊሆን ይገባል፣

፩፱.፪.፮ በሁለተኛው ዙር የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ እስከተቻለ ድረስ በዚህ መመሪያ በክፍል 7 እና 8 እንዲሁም በን/አንቀጽ ፩፯÷፩ እና ፩፯÷፪ ለግልፅ ጨረታ የተገለፀውን አሠራር መከተል ይኖርበታል።

፩፱.፪.፯ በመጀመሪያው ዙር ተቀባይነት ያገኙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሁለተኛው ዙር ውድድር እንዲሳተፉ ጥሪ የሚደረግላቸው ሲሆን፣ የጨረታ ዋስትና እንዲያቀርቡም ይደረጋል።

፩፱.፪.፰ መ/ቤቱ ለሁለተኛው ዙር የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች መላክ ወይንም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ቀርበው እንዲወስዱ ማድረግ ይኖርበታል።

፩፱.፪.፱ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፩፱.፪.፯ ላይ በተገለፀው መሰረት ለዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚተላለፈው ጥሪ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሰነዱን ለመውሰድ ሊያሟሉ የሚገባቸውን ሁኔታዎች በግልፅ ሊያመለክት ይገባል።

## ፪፲. <u>የውስን ጨረታ ግዥ አፈጻጸም፣</u>

የአዋጁ አንቀጽ ፫፰ እና ፫፱ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤

፪፲.፩ በአዋጁ አንቀጽ 38 ን/አነቀጽ ፩ መሠረት በውስን ጨረታ የሚፈጸም ግዥ በዚህ መመሪያ በክፍል 7 እና 8 ለብሔራዊ ወይም ለዓለም አቀፍ ጨረታ የተፈቀደውን ዝርዝር የአፈጻጸም ሥርዓት ተከትሎ የሚከናወን ይሆናል።

፪፲.፪ በውስን ጨረታ የሚፈፀም ግዥ የሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ይከናወናል፤

፪፲.፪.፩ የጨረታ ጥሪው በቀጥታ ለዕጩ ተወዳዳሪው በአድራሻው የሚላክ ሆኖ።

ሀ/ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝ ሲሆን የጨረታ ጥሪው ደብዳቤ ለሁሉም አቅራቢዎች በአድራሻቸው ተዘጋጅቶ መላክ ይኖርበታል።

ለ/ በጨረታው ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉ አቅራቢዎች ቁጥር በርካታ ቢሆንም ግዥው በንዑስ አንቀፅ ፪፲÷.፫ በተቀመጠው የገንዘብ መጠን ገደብ

ውስጥ ከሆነ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት መካከል ፍትሐዊ በሆነ ምርጫ ቢያንስ አምስት ዕጩ ተወዳዳሪዎች መመረጥ ይኖርባቸዋል::

፪፲.፪.፪ የመንግስት መ/ቤቱ በውስን ጨረታ የተጋበዙ ተጫራቾችን ማንነት ለሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች ማሳወቅ የለበትም::

፪፲.፪.፫ በውስን ጨረታ የተጋበዙት ተጫራቾች በሙሉ ከጨረታ መቆያ ጊዜ ገደቡ በፊት የመጫረቻ ሠነዳቸውን ካቀረቡ የጊዜ ገደቡ እስከሚጠናቀቅ መጠበቅ ሳያስፈልግ የመንግስት መ/ቤቱ አዲሱን የጨረታ መክፈቻ ጊዜ ለሁሉም ተጫራቾች በማሳወቅ እና እንዲገኙ በመጋበዝ ጨረታው እንዲከፈት ሊያደርግ ይችላል::

፪፲.፪.፬ የመንግሥት መ/ቤቱ ለግዥው ለተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍያ መጠየቅ አያስፈልግም ብሎ ሲያምን ከጨረታ ጥሪው ደብዳቤ ጋር የጨረታ ሰነዱን አያይዞ ሊልክ ይችላል::

፪፲.፪.፭ መ/ቤቱ በአዋጁ አንቀጽ ፫፰(፫) መሠረት የጨረታ ማስከበሪያ መጠየቅ ቁጥራቸው ውስን የሆኑትን ተጫራቾች በጨረታው ውድድር እንዳይሳተፉ ያደርጋል ብሎ ሲያምን የጨረታ ማስከበሪያ ማስያዝ ሳያስፈልግ ዕጩ ተጫራቾች በዚህ መመሪያ አባሪ ፭ የተመለከተውን የስምምነት ማረጋገጫ ፎርመው ከመጫረቻ ሠነዳቸው ጋር እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይችላል::

፪፲.፫ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፪፲.፪ የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው በአዋጁ አንቀፅ ፫፰ መሰረት በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ መጠቀም የሚቻለው የሚገዛው ዕቃ፣ የምክር አገልግሎት፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ወይም አገልግሎት ጠቅላላ ዋጋ ከሚከተለው የማይበልጥ ሲሆን ብቻ ነው::

- ሀ/ ለግንባታ ዘርፍ ሥራ ግዥ.... ከብር 100,000.00
- ለ/ ለዕቃ ግዥ ......................... ከብር 250,000.00
- ሐ/ ለምክር አገልግሎት ግዥ...... ከብር 300,000.00
- መ/ ለአገልግሎት ግዥ................ ከብር 200,000.00

፪፲.፬ በአዋጁ አንቀጽ ፫፰ በተገለጸው መሠረት ግዥን በውስን ጨረታ ለመፈጸም የሚከተሉት ሁኔታዎች በቅደም ተከተል መሟላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:-

ሀ/ ግዥውን ለመፈጸም የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ ቢያንስ ለሁለት ጊዜያት ወጥቶ ምንም ተጫራች ያልቀረበ ወይም በድጋሚ በወጣ ጨረታ የቀረቡት ተጫራቾች በመ/ቤቱ የተዘጋጀውን የቴክኒክ ፍላጎት ያላሟሉ መሆኑን፣

ለ/ የመንግስት መ/ቤቱ የጨረታ ጥሪውን፤ የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ መጠን እና አይነት እንዲሁም ሌላ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ለመሳተፍ እንዳይችሉ የሚገድቡ ሁኔታዎች በአሰራሩ ወይም በጨረታ ማስታወቂያው እና ሰነዱ ውስጥ አለመኖራቸውን፣

ሐ/ የመንግስት መ/ቤቱ በመስኩ የተሰማሩት አቅራቢዎች በውስን ጨረታ ግዥው ቢጋበዙ ለመሳተፍ ፈቃደኛ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሲያምን፣

መ/ እስከተቻለ ድረስ በመስኩ የተሰማሩት አቅራቢዎች በግልፅ ጨረታ ለመሳተፍ ፍቃደኛ ያልሆኑበትን ምክንያት በማጣራት ምክንያታቸው፤ ሕጋዊ እና የመንግስት መ/ቤቱን ጥቅም ለመጉዳት ያለመ አለመሆኑን ማረጋገጥ ሲቻል፣

፪፲.፭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪፲.፩፣ ፪፲.፪፣ ፪፲.፫ እና ፪፲.፬ ሥር የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው፣ በውስን ጨረታ የሚፈፀም ግዥ በዚህ በዚህ መመሪያ በክፍል 7 እና 8 የብሔራዊ ግልፅ ጨረታ የአፈፃፀም ሥርዓት ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

፪፲.፮ በመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያ የሚፈፀመው የውስን ጨረታ የምክር አገልግሎት ግዥ በዚህ መመሪያ በክፍል 7 እና 8 እንዲሁም በን/አንቀጽ ፩፯÷፩÷ ላይ የተገለጹትን ተጨማሪ አሰራሮች ተከትሎ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

## 21. ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ፣

ከአንድ አቅራቢ ግዥ ለመፈፀም የሚሰጠው ውሳኔ የሚከተሉትን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

21.1 የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ ለመፈፀም የሚችሉት በአዋጁ አንቀጽ 40 እና 41 የተዘረዘሩት ድንጋጌዎች ሲሟሉ ይሆናል:-

21.2 በአዋጁ አንቀጽ 40 በንዑስ አንቀጽ 1 "መ" እና "ሠ" መሠረት በዓይነት እና በዋጋ አንድ የሆኑ ዕቃዎችን፣ አገልግሎቶችን፣ የግንባታ ዘርፍ ስራዎችን እና የምክር አገልግሎቶችን ቀደም ሲል እነዚህን ካቀረበ ተጫራች መግዛት ጠቃሚ መሆኑ ሲታመንበት በአቅራቢው ፈቃደኛነት ላይ በመመሥረትና የሚከተሉትን አሠራሮች በመከተል ተጨማሪ ግዥ ለመፈጸም ይቻላል፡፡

ሀ/ በተጨማሪነት የሚታዘዘው ዕቃ፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ወይም የምክር አገልግሎት ግዥ መጠን ቀደም ሲል ከተገዛው ከ25% (ሀያ አምስት በመቶ) መብለጥ የለበትም፣

ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀፅ መሰረት ተጨማሪ ግዥ ለማዘዝ የቀድሞው ግዥ ውል ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ወይም ውሉ ከተጠናቀቀበት ቀን አንስቶ በሚቀጥሉት 6 ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ የግዥ ትዕዛዙ መተላለፍ ይኖርበታል፣

ሐ/ በዚህ መሰረት ለሚፈፀም ግዥ በመጀመሪያው ውል ከነበረው የነጠላ ዋጋ የበለጠ የዋጋ ጭማሪ ማድረግ አይፈቀድም፣

መ/ ከላይ በፊደል ተራ (ሐ) የተቀመጠው ቢኖርም የመጀመሪያው ውል የዋጋ ማስተካከያ የሚፈቅድ ከሆነ እና የዋጋ ማስተካከያ ይደረግባቸዋል የተባሉት ግብአቶች በተጨማሪው ውል ውስጥ የሚገኙ ከሆነ በመጀመሪያው ውል ላይ በተመለከተው የዋጋ ማስተካከያ አሰራርና ስሌት መሰረት የዋጋ ማስተካከያ በማድረግ ግዥው ሊፈጸም ይችላል፡፡

፳፩.፫ የመንግስት መ/ቤቶች በአዋጁ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 "ሐ" በተገለጸው መሰረት የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን አረጋግጠው ያልታሰቡና በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎችን ማሠራት ይችላሉ፡፡

ሀ/ የመንግስት መ/ቤቱ በተጨማሪነት እንዲሰሩ የታሰቡት ስራዎች በመጀመሪያው ውል ውስጥ መካተት ይገባቸው የነበሩ እና ስራዎቹን ነጣጥሎ ማሰራት ለአፈፃፀም አስቸጋሪ ወይም የመ/ቤቱን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፣

ለ/ በተጨማሪነት የሚታዘዘው የግንባታ ስራ የገንዘብ መጠን ከመጀመያው ውል ጠቅላላ ዋጋ ከ30% /ሠላሳ በመቶ/ የበለጠ መሆን የለበትም፣

ሐ/ በተጨማሪነት የሚታዘዙት የግንባታ ሥራዎች የነጠላ ዋጋ በመጀመሪያው ውል ውስጥ ሊገኝ የሚችል ከሆነ የተጨማሪው ስራ በመጀመሪያው ውል ውስጥ

ባለው ነጠላ ዋጋ መሰረት ተፈፃሚ የሚሆን ሲሆን የነጠላ ዋጋው በመጀመሪያው ውል ውስጥ የማይገኝ ከሆነ በድርድር ስምምነት ላይ የሚደረስበት ዋጋ የገበያ ዋጋ መሆኑን መ/ቤቱ ማረጋገጥ አለበት።

፪፩.፬ የመንግስት መ/ቤቱ ለሚጠቀምበት ዕቃ የሚያስፈልገው መለዋወጫ የሚገኘው ቀደም ሲል ዕቃውን ከሸጠው አቅራቢ ብቻ መሆኑ ሲረጋገጥ፤ ሆኖም ለዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈፃፀም በቅድሚያ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸው ሊረጋገጥ ይገባል።

ሀ/ የመንግስት መ/ቤቱ በቂ የገበያ ጥናት ማድረግ እና ሌላ የተሻለ አማራጭ ገበያ ላይ የሌለ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

ለ/ የመንግስት መ/ቤቱ ለሚጠቀምበት ዕቃ ከሚገዛው መለዋወጫ ብዛት፣ ተደጋጋሚነት እና የገንዘብ መጠን አንፃር ወደፊት ሌላ አማራጭ መፈለግ የሚያስፈልገው መሆኑንና አለመሆኑን መወሰን ይኖርበታል።

፪፩.፭ ግዥው ከሌላ አቅራቢ እንዲፈፀም ቢደረግ የሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት መ/ቤቱ ከሚጠቀምበት መሣሪያ ወይም አገልግሎት ጋር ተጣጥሞ የማይሄድ መሆኑ በባለሙያ ሲረጋገጥ፣

21.6 በአዋጁ አንቀጽ ፬፲ ንዑስ አንቀጽ ፩ "ሰ" መሰረት ከገበያ በለቀማ የሚፈጸመው ግዥ ለጥናትና ለምርምር አገልግሎት የሚፈለግ፣ እና ከመደበኛ አቅራቢዎች የማይገኝ፣ ወይም በለቀማ ቢገዛ ለመሥሪያ ቤቱ የኢኮኖሚ ጥቅም እንደሚያስገኝ ሲረጋገጥ የሚከተሉትን አሠራሮች በመከተል የለቀማ ግዥ መፈፀም ይቻላል።

ሀ/ ግዥውን በለቀማ መፈፀም ያስፈለገበትን ምክንያት የሚያስረዳ ማስታወሻ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ለዚህ ሥራ በኃላፊው ውክልና ለተሰጠው አካል ቀርቦ መፈቀድ ይኖርበታል።

ለ/ የመንግስት መ/ቤቱ ግዥውን በለቀማ ሊገዙ የሚችሉ ብዛታቸው ከሦስት ያላነሱ ጊዜያዊ ኮሚቴ በደብዳቤ ይሰይማል። እስከተቻለ ድረስ ስለሚገዛው እቃ ዕውቀት ያለው ሰራተኛ የኮሚቴው አባል እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል።

ሐ/ የተቋቋመው ጊዜያዊ ኮሚቴ ግዥውን በጋራ በመሆን ማከናወን ያለበት ሲሆን ግዥውን ለማከናወን በቂ አቅርቦት የሚኖርበትን ገበያ እና የገበያ ዕለት በመምረጥ ለሚመለከተው ኃላፊ ያሳውቃል።

መ/ ጊዚያዊው ኮሚቴው በጋራ በመሆን በገበያው ውስጥ ካለው አቅርቦት የተሻለ ጥራት እና ዋጋ ያለውን ወይም ያላቸውን ሻጮች በመምረጥ ዋጋ ተደራድሮ ግዥውን ይፈፅማል፡፡

ሠ/ በግዥው አፈፃፀም ሒደት የተፈፀሙትን ግዥዎች ብዛትና አይነት፣ ግብይቱ የተፈፀመበትን ቦታ፣ የተከፈለውን የገንዘብ መጠን፣ የሻጮችን ሙሉ ስም እና አድራሻ የሚገልፅ ሰነድ ተዘጋጅቶ ሻጮች በፊርማቸው እንዲያረጋግጡ መደረግ ይኖርበታል፡፡

ረ/ በለቀማ የተገዙ ግዥዎች በሚጓጓዙበት ወቅት እንዳይበላሹ እና እንዳይጠፉ በጥንቃቄ መያዝ እና በተቻለ ፍጥነት የሚመለከተው ክፍል እንዲረከባቸው መደረግ ይኖርበታል፡፡

ሰ/ ጊዜያዊው ኮሚቴ አጠቃላይ የለቀማ ግዥ አፈፃፀሙን የሚገልፅ ቃለ-ጉባኤ በማዘጋጀት ተፈራርሞ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፪፩.፯ በአዋጁ አንቀጽ ፬፲ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት:-

ሀ/ የመንግሥት መ/ቤቶች በግዥ ዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ዋጋቸው ከብር 1500 (አንድ ሺህ አምስት መቶ) ያልበለጡ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ወይም በጉዞ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከመፍታት ጋር የተያያዙ የቀጥታ ግዥዎችን ከማናቸውም ሻጭ ድርጅት መፈፀም ይችላሉ፡፡ ሆኖም በዚህ ዓይነት የሚፈጸሙ ጥቃቅን ግዥዎች ድምር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከብር 6000 (ስድስት ሺህ ብር) መብለጥ አይኖርበትም፡፡

፪፩.፰ በአዋጁ አንቀፅ 40 ን/አንቀጽ 1 በ □□ል ተራ (ሰ) እና በን/አንቀጽ 2 መሰረት ለሚፈጸሙ ጥቃቅን ግዥዎች ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቱ ከአንድ አቅራቢ ለሚፈጽመው ግዥ ሊገዛ ያሰበውን የግዥ አይነትና መጠን በመግለፅ አቅራቢው ሐሳቡን እንዲሰጥ በደብዳቤ ሊጠይቅ ይገባል፡፡ በዚህ መልኩ የሚላከው ደብዳቤ እንደአስፈላጊነቱ ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ እና አቅራቢው ዋጋን ጨምሮ የተሟላ ሐሳቡን እንዲያቀርብ የሚያስችለውን መረጃ ያካተተ መሆን አለበት፡፡

፪፩.፱ የመንግስት መ/ቤቱ ከአቅራቢው በፅሁፍ የቀረበለትን ዋጋን የጨመረ ሐሳብ ተቀብሎ በመመርመርና የአዋጁን እና የዚህን መመሪያ አንቀፆች እንደማይጥስ በማረጋገጥ ዋጋን ጨምሮ ድርድር ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ከለየ በኋላ ድርድር ማድረግ ይችላል፡፡

፪፩÷፩፲ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፪፩.፱ ላይ በተመለከተው መሰረት ድርድር ለማድረግ የመንግስት መ/ቤቱ ተደራዳሪዎችን መምረጥ እና በአዋጁ አንቀጽ ፬፩ በን/አንቀጽ ፪ መሠረት የሚደረገው ድርድር በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚሠጠውን አቅጣጫና የድርድር አትኩሮተ ነጥቦች መሠረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፪፩.፩፩ በአዋጁ አንቀፅ ፬፲ በን/አንቀጽ ፩ በፊደል ተራ (ሰ) እና በአንቀጽ 40 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቱ ከአንድ አቅራቢ ለሚፈፅመው ግዥ የውል ስምምነት መፈረም ይኖርበታል፡፡

## ፪፪. በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ፣

፪፪.፩ የአዋጁ አንቀጽ ፬፬ እና ፬፫ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የመንግስት መ/ቤቶች አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ ግዥን በግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈፀም አለባቸው፡፡ ሆኖም ሊታቀዱ ያልቻሉና ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ እና ዋጋቸው ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ ፪፪.፪ በተመለከተው ገደብ ውስጥ ይሆናል ተብሎ የሚገመቱ ግዥዎችን በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ለመፈፀም ይችላሉ፡፡

፪፪.፪ ከሚከተሉት የገንዘብ መጠኖች የማይበልጡ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀሙ ግዥዎችን ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ መቅረብ ሳያስፈልግ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ በሚሰጠው ውክልና መሠረት እንዲፀድቁ በማድረግ ግዥ መፈፀም ይችላል፡፡

ሀ/ ለግንባታ ሥራ ግዥ............ እስከ ብር 100,000.00
ለ/ ለዕቃ ግዥ.......................... እስከ ብር 40,000.00
ሐ/ ለምክር አገልግሎት ግዥ..... እስከ ብር 40,000.00
መ/ ለአገልግሎት ግዥ............... እስከ ብር 40,000.00

፪፪.፫ የመንግስት መ/ቤቱ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ግዥ ሲፈጽም በውድድሩ ተሳታፊ የሚሆኑት አቅራቢዎች ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የሚመረጡ ሆኖ እስከተቻለ ድረስ ቁጥራቸው ከሶስት ማነስ አይኖርበትም፡፡ ውድድሩንም ፍትሐዊ ለማድረግ አፈፃፀሙ የሚከተለውን አሠራር መከተል ይኖርበታል፡

ሀ/ የመንግስት መ/ቤቱ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡት ሁሉም ተሳታፊዎች በዙር የመወዳደር ዕድል ማግኘታቸውን እና ለመ/ቤቱ ጠ

ቃሚ የሆነ የተለየ ሁኔታ መኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር አንድ ወይም የተወሰኑ አቅራቢዎችን ብቻ በተደጋጋሚ መጋበዝ አይኖርባቸውም፡፡

ለ/ የመንግሥት መ/ቤቱ የዋጋ ማቅረቢያ በመስጠት እና ዋጋ በመወሰን ሒደት ሊፈጠር የሚችል መመሳጠርን ለመከላከል የሚያስችል አሰራር መከተል እና በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 22.፮ በተመለከተው መሠረት በየጊዜው ጥብቅ የዋጋ ቁጥጥር ማድረግ ይገባዋል፡፡

፪፪.፬ እያንዳንዱ ዕጩ ተወዳዳሪ እንዲያቀርብ የሚፈቀድለት አንድ የመወዳደሪያ ዋጋ ብቻ ሆኖ ያቀረበውን ዋጋም መለወጥ አይፈቀድለትም፡፡ ዕጩ ተወዳዳሪው በሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ ላይ በመንግስት መ/ቤቱ እና በዕጩ ተወዳዳሪው መካከል ምንም ዓይነት ድርድር ሊደረግ አይችልም፡፡

፪፪.፭ ተቀራራቢ የጥራት ደረጃ ያላቸውና በመ/ቤቱ የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ የሚያሟሉ አቅርቦቶችን በማወዳደር ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች አሸናፊ አድርጎ መምረጥ ያስፈልጋል፡፡

፪፪.፮ በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ የሚደረገው የዋጋ ውድድር ታክስን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡

፪፪.፯ መ/ቤቱ በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈፅማቸው ግዥዎች በኤጀንሲው ድረ-ገጽ የሚወጣውን ወቅታዊ የዋጋ ዝርዝር ፣ በግዥ ስራ ክፍሉ የሚካሄድ የገበያ ጥናትን በመጠቀም ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ማመን ይኖርበታል፡፡

፪፪.8 የመንግስት መ/ቤቶች የዋጋ ማቅረቢያ በመሰብሰብ ለሚፈጽሙት ማናቸውም ግዥ እስከተቻለ ድረስ በኤጀንሲው የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሠነድ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

፪፪.፱ መ/ቤቱ ከዚህ በታች የተገለጹት ሁኔታዎች መሟላታቸው ተረጋግጦ በኤጀንሲው ሲፈቀድለት የዋጋ መጠየቂያ ለመላክና የዋጋ ማቅረቢያ ለመቀበል የሚያስችል የኤሌክትሮኒክ የመረጃ መለዋወጫ ዘዴ በመፍጠር ተግባራዊ ማድረግ ይችላል፡፡

ሀ/ የሚዘረጋው የኤሌክትሮኒክ የመረጃ መለዋወጫ ዘዴ መረጃ ሊደርሰው ከሚገባው አካል እና መረጃው ሊታወቅ ከሚገባው ቀን እና ሰዓት ውጪ በማንኛውም አካል ሊታይ እንደማይችል የሚያረጋግጥ የተሟላ የመረጃ ደህንነት ሲኖረው፣

ለ/ በዋጋ ማቅረቢያ ሊወዳደሩ የሚችሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሙሉ በዘዴው ለመጠቀም የሚያስችል ዕውቀት እና ዝግጁነት ያላቸው መሆኑ ሲያረጋግጥ፣

ሐ/ ከላይ በፊደል ተራ "ለ" የተቀመጠው ቢኖርም በኤሌክትሮኒክ የመረጃ መለዋወጫ ዘዴ ዋጋ መስጠት የማይችሉ በተለመደው አሠራር በፖስታ ዋጋ ሊሰጡ እንዲችሉ አማራጭ የተዘጋጀላቸው ሲሆን፣

፪፪.፩፲ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ለሚከናወኑ ግዥዎች አቅራቢው የሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ /ፕሮፎርማ/ እና መ/ቤቱ ለአቅራቢው የግዥ ትዕዛዝ የሰጠበት ደብዳቤ እንደውል ስለሚቆጠሩ ተጨማሪ ውል መዋዋል አስፈላጊ አይሆንም::

፪፪.11 በዚህ አንቀጽ ለመጠቀም ሲባል የመንግሥት መ/ቤቶች በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍለው መግዛት አይኖርባቸውም::

## ፪፫. ሌሎች ዓለም አቀፍ ግዥዎች

፪፫.፩ በአዋጁ አንቀጽ ፬፰ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሰረት የውጭ ኩባንያዎች ካልተሳተፉበት በቂና ውጤታማ ውድድር ሊኖር አይችልም ተብሎ ሲታመን በአዋጁና በዚህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ ለብሔራዊና ለዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የተገለጹት ሌሎች አሠራሮች እንደተጠበቁ ሆነው የመንግስት መ/ቤቶች የሁለት ደረጃን፤ የመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያን፤ የውስን ጨረታን፣ የዋጋ ማቅረቢያንና ከአንድ አቅራቢ የግዥ ዘዴን በመጠቀም ዓለም ዓቀፍ ግዥ መፈጸም ይችላሉ::

፪፫.፪ በንዑስ አንቀፅ ፪፫.፩ ላይ በተገለፀው መሰረት ከአለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች በመጠቀም አለም አቀፍ ግዥ መፈፀም የሚቻለው ለየግዥ ዘዴው የተመለከተውን ሁኔታ እና የተፈቀደውን የገንዘብ መጠን መሰረት በማድረግ ይሆናል::

# ክፍል ፰

## ልዩ ግዥ

### 24. ከፍተኛ ግዥ

ሀ/ መንግስት ያለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ይረዳል ወይም ለአስተዳደሩ የተለየ ጥቅም ያስገኛል ተብሎ በመንግስት የበላይ ኃላፊዎች ሲታመን በቢሮ ኃላፊ ትዕዛዝ መሰረት ልዩ ግዥ በማዕከል ሊፈፀም ይችላል፡፡

ለ/ ልዩ አስተዳደራዊ ጥቅም የሚኖራቸውን ግዥዎች እንዲፈጽም የሚቋቋመው አካል ግዥውን በልዩ ሁኔታ እንዲፈጽም በአስተዳደሩ ካልታዘዘ በስተቀር የአዋጁን እና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ጠብቆ ግዥውን ተፈፃሚ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

### ፪፭. በመንግሥት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃና አገልግሎቶች ልዩ ግዥ

፪፭.፩ የልዩ ግዥ አፈጻጸም አዋጁን እና ይህን መመሪያ መሠረት በማድረግ ለግዥው በሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ መሰረት ተፈፃሚ ይደረጋል፡፡

፪፭.፪ በሁሉም ወይም በተወሰኑ መ/ቤቶች መሠረት በማድረግ ሲሆን የሚከተሉትን አሠራሮች ተከትሎ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

ሀ/ በዚህ መመሪያ በክፍል ሁለት ላይ የተመለከተውን መሠረት በማድረግ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም የተቋቋመው አካል በቂ እና ግልፅ የሆነ የውስጥ አደረጃጀት በመፍጠር የጨረታ ሰነድ የማዘጋጀት፣ የመገምገም፣ የማፅደቅ እና ውል የማስተዳደር ስራዎች በተለያዩ ቡድኖች እንዲፈፀሙ ያደርጋል፣

ለ/ ለስራው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጨረታ ዝግጅት እና ግምገማ ወቅት የሙያ ድጋፍ ከመንግስት መ/ቤቶች ሊጠይቅ እና ሊያገኝ ይችላል፡፡

፪፰.፫ በሁሉም ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የመንግሥት መ/ቤቶች የሚፈለጉ ተመሳሳይ ግዥዎች በአንድ ላይ ተሰባስበው በሚከተሉት እና ይህንን መመሪያ ተከትሎ አሰራሩን ለማስፈፀም በሚወጡት ሰነዶች መሰረት ይፈፀማል፡፡

ሀ/ ኤጀንሲው በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶችን በመለየት ዝርዝር ያወጣል፤ ዝርዝሩንም በየጊዜው ያዳብራል፤ ለመንግስት መ/ቤቶች እና ልዩ ግዥ ለማስፈጸም ለተቋቋመው አካል ያሳውቃል፣

ለ/ እያንዳንዱ የመንግስት መ/ቤት በተላለፈለት ዝርዝር መሰረት አመታዊ የግዥ ፍላጎቱን ልዩ ግዥ ለሚፈፅመው አካል እንዲያሳውቅ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ማቅረብ (ማሳወቅ) አለበት፣

ሐ/ ልዩ ግዥ እንዲፈጽም የተቋቋመው አካል የሁሉንም የአስተዳደሩን የመንግስት መ/ቤቶች ፍላጎት በማሰባሰብ የግዥ እቅድ ያዘጋጃል፤ ያዘጋጀውን እቅድ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፩፬ ንዑስ አንቀፅ 14.፫ መሠረት ለኤጀንሲው እና ግዥው ለሚመለከታቸው የመንግሥት መ/ቤቶች ያሳውቃል፡፡

፪፰.፬ ልዩ ግዥ እንዲፈፅም የተቋቋመው አካል ለየግዥው የሚፈረመውን የውል አይነት እና ዋጋ በገበያ ጥናት ላይ ተመርኩዞ ይወስናል፤

፪፰.፬.፩ በዚህ መመሪያ አንቀፅ ፫፫ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ልዩ ግዥ የሚፈጽመው አካል የሚከተሉትን ተጨማሪ ዝርዝሮች ያካተተ የግዥ ማስታወቂያ ማውጣት አለበት:

ሀ/ የማስታወቂያ ጥሪ የተደረገው የማዕቀፍ ስምምነት ለመፈራረም እንዲቻል መሆኑን፣

ለ/ በማዕቀፍ ስምምነቱ የሚፈፀመው ግዥ ዓይነት፣ ግምታዊ መጠን እና የርክክብ ሁኔታ፣

ሐ/ የማዕቀፍ ስምምነቱ የሚቆይበትን ጊዜ

መ/ በማዕቀፍ ስምምነቱ የሚጠቀሙትን የመንግስት መ/ቤቶች ብዛት፣

፪፭.፩.፪ ልዩ ግዥ በሚፈጽመው አካል ለማዕቀፍ ስምምነት ግዥ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ መደበኛ የጨረታ ሰነድ በመጠቀም የሚዘጋጅ ሆኖ የሚከተሉትን እንዲያካትት መደረግ አለበት፡

ሀ/ የሚገዛውን ዕቃ ዝርዝር እና እስከተቻለ ድረስ ግምታዊ የግዥ መጠን እና የርክክብ ሁኔታ፣

ለ/ የማስረከቢያ ቦታ እና እስከተቻለ ድረስ ግምታዊ የማስረከቢያ ጊዜ፣

ሐ/ የማዕቀፍ ስምምነቱን የሚጠቀሙ የመንግስት መ/ቤቶች ዝርዝር፣

መ/ ግዥው የዋጋ ማስተካከያ የሚፈቅድ ከሆነ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበትን ሁኔታ እና አፈፃፀሙን፣

ሠ/ የግዥው ውል ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፣

፪፭.፭ በአዋጁ አንቀፅ ፭፲ ን/አንቀጽ ፩ ላይ በተገለፀው መሰረት ለማዕቀፍ ስምምነት በወጣ ጨረታ አሸናፊ ከሆነው አቅራቢ ጋር እስከ ሦስት አመታት ሊደርስ የሚችል ውል የሚፈረም ሲሆን የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም የተቋቋመው አካል የሚከተሉትን እና ሌሎች ሁኔታዎችን በማገናዘብ እንደግዥው ሁኔታ እና እንደአስፈላጊነቱ ከአንድ በላይ ከሆኑ ፈቃደኛ ተወዳዳሪዎች ጋር በደረጃቸው ቅደም ተከተል መሰረት ተመሳሳይ የሆነ የማዕቀፍ ስምምነት ሊፈርም ይችላል፡-

ሀ/ የሚፈለገው የግዥ መጠን እና የተመረጠው አቅራቢ አቅም ከሚፈለገው አቅርቦት ጋር የማይመጣጠን ሲሆን፣ ወይም

ለ/ በገበያው ላይ ያሉ ተመሳሳይ አቅራቢዎች ብዛት ያላቸው ሲሆኑና የግዥ ዕድሉን ለብዙ አቅራቢዎች መስጠት ሲያስፈልግ፣ ወይም

ሐ/ የገበያው ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ ተለዋዋጭ በመሆኑ ምክንያት ግዥውን በቀረበው ዋጋ በቶሎ ማጠናቀቅ ሲያስፈልግ፣

፪፭.፮ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም የተቋቋመው አካል ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፪፭.፭ ላይ በተገለጸው መሰረት በአሸናፊው ዋጋ እንዲያቀርቡ በደረጃቸው ቅደም ተከተል ሌሎች ተጫራቾችን ለውል ስምምነት ሲጋብዝ የሚጋብዛቸውን አቅራቢዎች ቁጥር እንደ ግዥው ሁኔታ አይቶ ይወስናል፡፡

በዚህ መሰረት የሚፈፀም ውል፣

ሀ/ በአሸናፊው ዋጋ ለማቅረብ ፈቃደኛ ከሆኑ አቅራቢዎች ጋር ይፈረማል፣

ለ/ አሸናፊው ድርጅት ለውል ስምምነት እና ምርጫ በሚኖራቸው ጉዳዮች ላይ የምርጫ ቅድሚያ እንዲያገኝ ይደረጋል፣

ሐ/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፪፫.፭ ላይ የተመለከተው ሁኔታ ሲያጋጥም ከጨረታው ዋና አሸናፊ ጋር የሚፈረመው የግዥ መጠን ከጠቅላላው ግዥ ከ፷፲% (ስድሳ በመቶ) ያነሰ መሆን የለበትም::

፪፫.፮ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም የተቋቋመው አካል የመንግስት መሥሪያቤቶችን ወክሎ አጠቃላይ የውል ስምምነት የሚፈርም ሲሆን ስምምነቱም የሚከተሉትን እና ሌሎች ተገቢ ናቸው የሚባሉ ሁኔታዎችን በግልፅ እንዲያካትት መደረግ አለበት፡-

ሀ/ በውል ስምምነት አስተዳደር ወቅት በማዕቀፍ ስምምነቱ የሚጠቀሙ የመንግስት መ/ቤቶችን ዝርዝር፤ የማዕቀፍ ስምምነቱን የሚፈርመውን እና የሚያስተዳድረውን አካል እንዲሁም የማዕቀፍ ስምምነቱ አቅራቢዎች የሚኖራቸውን ኃላፊነት እና ግዴታ፣

ለ/ በማዕቀፍ ስምምነቱ የግዥ ትዕዛዝ የሚተላለፍበትን፣ ርክክብ የሚደረግበትን፣ ክፍያ የሚፈፀምበትን እና ክትትል እና ግምገማ የሚደረግበትን ስርአት፣

ሐ/ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ የሚፈቱበትን ስርአት፣

፪፫.፯ በአዋጁ፣ ልዩ ግዥ እንዲፈጽም ኃላፊነት በተሰጠው አካል የማቋቋሚያ ደንብ እና ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፪፫.፮ ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ የሚፈጽመው አካል በማዕቀፍ ስምምነት አስተዳደር ወቅት የሚከተሉት ተጨማሪ ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ/ የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው በውሉ መሰረት እየፈፀመ መሆኑን ይከታተላል፤

ለ/ ለማዕቀፍ ስምምነቱ ተፈፃሚነት የተያዘውን የውል ማስከበሪያ ይይዛል፤ ያስተዳድራል፤ በውሉ መሰረት አለመፈፀሙን ሲያረጋግጥም እንደአስፈላጊነቱ በመውረስ ገንዘቡን ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ገቢ ያደርጋል:: አቅራቢው

የፈፀመውን ጥፋት በሚመለከትም በአዋጁ አንቀጽ ፯፪ እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፯፫ በን/አንቀጽ ፩ መሠረት ለኤጀንሲው ሪፖርት ያቀርባል፣

ሐ/ በማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው እና በመንግስት መ/ቤቱ መካከል አለመግባባት ሲፈጠር ጉዳዩን በውይይት ለመፍታት ጥረት ያደርጋል፤

መ/ በጋራ ስምምነት ላይ በተመሠረተ መንገድ በማዕቀፍ ስምምነቱ ሁኔታ ላይ ለውጥ ማድረግ ሲያስፈልግ ይህንኑ ይፈፅማል፤

ሠ/ በውል አፈፃፀም ወቅት ለመንግስት መ/ቤቶች ድጋፍ ያደርጋል፤

ረ/ የማዕቀፍ ስምምነቱ ሲጠናቀቅ የውል አፈፃፀም ግምገማ በማድረግ የውል ማስከበሪያው እንዲለቀቅ ያደርጋል፡፡

፪፫.፱ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ የሚፈጽመው አካል ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት የማእቀፍ ስምምነቱን ሊሰርዝ ይችላል፡፡

ሀ/ የማዕቀፍ ስምምነቱ አቅራቢ በውሉ መሰረት ግዴታውን አለመወጣቱ ሲታወቅ፣

ለ/ የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ ፍላጎት በግልጽና በታወቀ ምክንያት ሲለወጥ፣

ሐ/ የተደረገው የማዕቀፍ ስምምነት ዋጋ፣ ሌሎች ሁኔታዎች እንዲሁም የገበያው ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ የመንግስት መ/ቤቶችን ሊጎዳ የሚችል ሰፊ ልዩነት መኖሩ ሲረጋገጥ፣

መ/ በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ "ለ እና ሐ" መሰረት የማዕቀፍ ስምምነት እንዲቋረጥ ሲወሰን፣ የማዕቀፍ ስምምነቱ የሚቋረጥበትን ምክንያት እና ተፈፃሚ የሚሆንበትን ቀን በመግለፅ የአንድ ወር የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ለማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው በጽሑፍ መስጠት አለበት፣

ሠ/ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያው ጊዜ እስከሚጠናቀቅ በውሉ ላይ የተገለፁት መ/ቤቶች ግዥያቸውን ከሌላ አቅራቢ መፈፀም አይችሉም፡፡

፪፫.1፲ የመንግስት መ/ቤቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም ከተቋቋመው አካል የተላለፈላቸውን የማዕቀፍ ስምምነት ቅጂ በመጠቀም በውሉ ላይ የተገለፁትን አቅርቦቶች ለመግዛት የሚያስችል የግዥ ትዕዛዝ ለማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው ያስተላልፋሉ፡፡ መ/ቤቱ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም ከተቋቋመው አካል ጋር በመመካከር ከአቅራቢው ጋር ተጨማሪ የተናጠል ውል መፈረም ይችላል፡፡

፪፫.1፲.፩ የግዥ ትእዛዙ ወይም ተጨማሪው የተናጠል ውል በአጠቃላይ ውሉ ውስጥ የተካተቱ መሰረታዊ የሆኑ ዋጋ እና ሌሎች የውል ሁኔታዎችን አይለውጥም፣

ሆኖም የመንግስት መ/ቤቱ በሚከተሉት እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ከማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው ጋር የተናጠል ውል ሊፈፅም ይችላል፡-

ሀ/ ዕቃው የሚቀርብበትን እና ክፍያ የሚፈፀምበትን ጊዜ ለማሳጠር፣

ለ/ በአንድ የግዥ ትዕዛዝ የሚቀርበውን ዕቃ ብዛት ለመወሰን፣

ሐ/ ዕቃው የሚቀርብበትን ቦታ ለማሳወቅ ወይም ለመቀየር፣

፪፫.1፲.፪ መ/ቤቱ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፪፫.1፲.፩ በተገለፀው መሰረት የፈፀመውን የተናጠል ውል ቅጅ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽምና እንዲያስተዳድር ለተቋቋመው አካል መስጠት አለበት፡፡

፪፫.፩፩ በማዕቀፍ ስምምነት አፈፃፀም ወቅት የመንግስት መ/ቤቶች የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ማድረግ ይኖርባቸዋል፡-

ሀ/ የግዥ ትዕዛዝ የሚሰጡት በማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ለሚፈፅመው አካል የገለፁትን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ግዥው በማዕቀፍ ስምምነት የተፈፀመውን ዕቃ ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ለ/ በማዕቀፍ ስምምነቱ ውስጥ የተገለፁ በመንግስት መ/ቤቶች የሚፈፀሙ ግዴታዎች በስምምነቱ መሰረት የተፈፀሙ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሐ/ በውሉ ላይ የሚነሱ አከራካሪ ጉዳዮችን የማዕቀፍ ስምምነት ከሚያስተዳድረው አካል ጋር በጋራ በመሆን ለመፍታት ጥረት ማድረግ፣

መ/ የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው በዋና ዋና የውል ጉዳዮች ማለትም የዕቃ ጥራት እና መጠን ማጓደል፣ የማቅረቢያ ጊዜ አለመጠበቅ፣ በአስተሻሸግ እና በመሳሰሉ የፈፀማቸውን ጥፋቶች የማዕቀፍ ስምምነቱን እንዲያስተዳድር ለተቋቋመው አካል በወቅቱ በጽሑፍ ማሳወቅ፣

ሠ/ በማዕቀፍ ስምምነት ለተካተቱ ፍላጎቶቻቸው የግዥ ትዕዛዝ የሚሰጡበትን ጊዜ እና እንዲቀርብላቸው የሚፈልጉትን የአቅርቦት መጠን መወሰንና ስለዝርዝር አፈፃፀሙ ልዩ ግዥ የሚፈጽመውን አካል ማማከር፣

፪፫.፩፪ የማዕቀፍ ስምምነትን እንዲያስተዳድር የሚቋቋመው አካል የመንግስት መ/ቤቶች ሥራ እንዳይጓተት የማዕቀፍ ስምምነት በወቅቱ መፈረም የሚኖርበት ሲሆን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በወቅቱ የማዕቀፍ ስምምነት ሊፈረም አለመቻሉን ካረጋገጠ ላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚኖራቸውን ፍላጎት በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎችን በመጠበቅ መግዛት ይችላሉ፣

፪፭.፩፫ በአዋጁ አንቀፅ ፭፲ ንዑስ አንቀፅ ፫ መሰረት የመንግስት መ/ቤት በተደጋጋሚ ለሚኖረው ተመሳሳይ ፍላጎት የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ግዥውን በማዕቀፍ ስምምነት መፈፀም ይችላል፡፡

ሀ/ በልዩ ባህርይው ምክንያት በመንግሥት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችን/አገልግሎቶችን አሰባስቦ የማዕቀፍ ግዥ እንዲፈጽምና እንዲያስተዳድር በተቋቋመው አካል ሊፈፀም የማይችል ግዥ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ/ ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በተደጋጋሚ እና ለተከታታይ ጊዜ መቅረብ ያለበት ሲሆን፣

ሐ/ የሚገዛው ዕቃ በሚሆንበት ጊዜ ዕቃውን አንድ ጊዜ ገዝቶ በመረከብ ለተከታታይ ጊዜ መጠቀም የማይቻል ወይም በየጊዜው ተጫራቾችን በማወዳደር ግዥውን መፈፀም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የማይኖረው ሲሆን፣

መ/ መ/ቤቱ ለግዥው የስያዘውን በጀት በተለያየ ጊዜ መጠቀም ሲኖርበት፣

፪፭.፩፬ በንዑስ አንቀፅ ፪፭÷፩፫ ላይ በተገለፀው መሰረት መ/ቤቱ በተደጋጋሚ ለሚኖረው ተመሳሳይ ፍላጎት፡-

ሀ/ የሚያካሒደው ጨረታ በዚህ መመሪያ በክፍል 6፣ 7 እና 8 ላይ የተቀመጠ ውን ስርዓት መከተል አለበት፣

ለ/ የሚፈርመው ውል ከሁለት አመታት በላይ የቆይታ ጊዜ ሊኖረው አይገባም፣

ሐ/ በዚህ መመሪያ በክፍል 10 የተቀመጡ የዋጋ ማስተካከያ ድንጋጌዎችን የተከተለ የዋጋ ማስተካከያ ሊፈቅድ እና በተፈቀደው የአፈፃፀም ስርዓት መሰረት ሊፈጽም ይችላል፡፡

# ክፍል 6

# የጨረታ ሰነድ

26. የጨረታ ሰነድ አዘገጃጀት

ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት በሚከተሉት ዝርዝሮች መሠረት የጨረታ ሰነድ ማዘጋጀትና መጠቀም አለበት

26.1. በአዋጁ አንቀጽ ፪፮ መሠረት ለሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነድ በኤጀንሲው የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ መጠቀማቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚያዘጋጁት የጨረታ ሠነድ በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን ያካተተ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው::

26.2. የጨረታ ሰነድ በሚያዘጋጁበት ወቅት በኤጀንሲው ከተዘጋጀው መደበኛ የጨረታ ሠነድ ውስጥ በተጫራቾች መመሪያ እና በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ ምንም ለውጥ ሳያደርጉ በሌሎች የሰነዱ ክፍሎች ላይ እንደግዥው አይነትና ባህርይ ማሻሻያ በማድረግ ሠነዱን ማዘጋጀት አለባቸው::

26.3. የጨረታ ሠነድ በዋናነት በግዥ የሥራ ክፍል ወይም ቡድን የሚዘጋጅ ሲሆን፣ በግዥ አጽዳቂ ኮሚቴው ውሳኔ መሠረት ለሚፈጸም ግዥ የሚዘጋጅ ማንኛውም የጨረታ ሠነድ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በኮሚቴው ተቀባይነት ማግኘቱ መረጋገጥ አለበት::

27. የተጫራቾች መመሪያ

27.1. ማንኛ□ም የመንግስት መ/ቤት የመደበኛ የጨረታ ሠነዶች አንዱ ክፍል ሆኖ የተዘጋጀውን የተጫራቾች መመሪያ እና የዚሁ አካል የሆነውን የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ የጨረታው ሰነድ ክፍል አድርጐ ለተጫራቾች መስጠት አለበት::

27.2. በመ/ቤቶች የሚዘጋጀው የተጫራቾች መመሪያ የሚከተሉትን ያካተተ መሆኑን የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ማረጋገጥ አለበት፡-

ሀ/ የሚገዛውን ዕቃ ወይም የግንባታ ስራ፤ የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች አጠቃላይ መግለጫ፤ የመንግስት መ/ቤቱን ሙሉ ስምና አድራሻ እንዲሁም የግዥውን የበጀት ምንጭ፣

ለ/ በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች ስለሚያሟሏቸው መስፈርቶች የሚገልፅ ሆኖ ከወጣው ጨረታ ውስጥ በገቢዎች ግምሩክ ባለስልጣን ወቅታዊ መመሪያ መሠረት ቫት ከፋይ ለመሆን የተቀመጠውን የብር ጣራ ግዥው በሚሆንበት ጊዜ

በጨረታው የሚሳተፍ ማንኛውም የአገር ውስጥ ተጫራች በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገበ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ እንዳለበት እንዲሁም የውጭ አገር ተጫራቾች በሚሆኑበት ጊዜ እንደአግባብነቱ በተቋቋሙበት አገር የተሰጣቸውን የኩባንያ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም ፈቃድ ማቅረብ እንዳለባቸው መጠቀሱን፣

ሐ/ በጨረታ ሰነዱ ግልፅ ያልሆኑ ጉዳዮችን አስመልክቶ ማብራሪያ የሚጠየቅበትን አድራሻ፣ ጊዜ እና የማብራሪያ ጥያቄው በፅሑፍ መቅረብ እንደሚገባው የሚያመለክት መግለጫ፣

መ/ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚያቀርቡት የመጫረቻ ሰነድ ይዘት ምን መሆን እንዳለበት፣ በምን ቋንቋ እንደሚዘጋጅ፣ በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ውስጥ የተገለፁ እና በተጨማሪነት የሚያስፈልጉ ማስረጃዎች እና ቅፆች አይነት እና ብዛት፣

ሠ/ ተጫራቹ የማጭበርበር ድርጊት እና ሙስናን በሚመለከት፣ በኢትዮጵያ ሕጎች የተደነገገውን የሚያከብር መሆኑን በማረጋገጥ ከጨረታ ሰነዱ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን ሙስና ላለመፈፀም ቃል የሚገባበትን ቅፅ እና ሌሎች በተጫራቹ ተሞልተው እንዲቀርቡ የሚፈለጉ ቅጾችን ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ እንዳለበት፣

ረ/ የጨረታውን አካሔድ ለማዛባት የሚሞክሩ ተጫራቾች ከጨረታው ውጪ እንደሚሆኑ፣ ለወደፊትም በመንግሥት ግዥ እንዳይሳተፉ እንደሚደረግ እና ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንደሚወረስ የሚያመለክት መግለጫ፣

ሰ/ የዕቃዎቹ ናሙናዎች በተጫራቾች እንዲቀርቡ የሚያስፈልጉ ከሆነ ተፈላጊዎቹ ናሙናዎች የሚቀርቡበትንና እንደፈስፈላጊነቱ በተጫራቾች የሚታዩበትን ጊዜ እና ቦታ እንዲሁም እነዚህ ናሙናዎች በጨረታው ለተሸነፉ ተጫራቾች የሚመለሱ ወይም ሊመለሱ የማይችሉ መሆናቸውን፣

ሸ/ የጨረታ ሳጥኑ የሚገኝበትን ቦታ እና ጨረታው ከተዘጋ በኋላ የሚቀርብ የመጫረቻ ሰነድ ተቀባይነት እንደማይኖረው የሚገልፅ መግለጫ፣

ቀ/ ጨረታውን ለመገምገም በሥራ ላይ የሚውሉትን ዘዴዎች፣ ለዚሁ ግምገማ የሚያገለግሉትን መስፈርቶች እና እያንዳንዱ መስፈርት የሚኖረውን የነጥብ ድርሻ፣ እንዲሁም ሁለት እና ከሁለት በላይ የሆኑ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በግምገማው እኩል ቢሆኑ አሸናፊውን ተጫራች ለመለየት የመወዳደሪያ ሐሳብ የሚቀርብበት ሁኔታና መስፈርቶች፣

በ/ በውል አፈጻጸም ወቅት የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ መቻል አለመቻሉን እና የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ የሚፈቀድ ከሆነ ተፈፃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ፣

ተ/ የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ፣ የውል አፈፃፀም ዋስትና መጠን እና ዓይነት እንዲሁም እነዚህ ዋስትናዎች ፀንተው የሚቆዩበትን ጊዜ፣

ቸ/ የመጫረቻ ሠነድ ማስረከቢያ ጊዜ የሚያበቃበትን እና ጨረታው የሚከፈትበትን ቦታ፣ ቀን እና ሰዓት፣

ነ/ የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ እንዲሁም የርክክቡን ቦታና ጊዜ፣

ኘ/ በአዋጁ ለአገር ውስጥ ምርትና ኩባንያዎች የተፈቀደውን ልዩ አስተያየት ዝርዝር አፈጻጸም የሚያመለክት መግለጫ፣

አ/ ጨረታው በአንድ ወይም በሁለት ኢንቨሎኘ የሚቀርብ ስለመሆኑ፣ ስለኤንቨሎፖች አስተሻሸግ፣ አንድ ወጥ የሆኑ ዋናና ቅጂ ሠነዶች መቅረብ እንዳለባቸው፣ የቅጂዎችን ብዛት፣ ሠነዶቹ ሥልጣን ባለው አካል የተፈረመባቸው ሊሆኑ እንደሚገባ እና ማህተም እንደሚያስፈልጋቸው፣ እንዲሁም (ወቅታዊ የግብር ክፍያ ምስክር ወረቀት፣ የታደሰ ንግድ ፈቃድ እና ሌሎች መ/ቤቱ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸው ደጋፊ ሰነዶች) ስለሚቀርቡበት ሁኔታ፣

ከ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፴፫÷፱ በተደነገገው መሠረት የቅድሚያ ክፍያ የሚሰጥ ከሆነ፣ የቅድሚያ ክፍያውን መጠን እና ተቀባይነት ያለውን የዋስትና አይነት እና፣

ወ/ ተጫራቾች በጨረታው አፈፃፀም ሒደት ቅሬታ ካላቸው በአዋጁ ምዕራፍ አሥራ ሶስት እንዲሁም በዚህ መመሪያ በክፍል ፩፬

መሠረት አቤቱታ የማቅረብ መብት እንዳላቸው እና አቤቱታው የሚቀርብበትን ቦታ፣

ዘ/ መ/ቤቱ ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ውል ከመፈረሙ በፊት በጨረታ ሠነዱ ከተገለጸው የአቅርቦት መጠን ላይ መጨመር ወይም መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በአሸናፊው ተጫራች የቀረበው ውድድሩ የተገኘው ዋጋ ሳይቀየር እስከ ፳% (ሃያ በመቶ) መጨመር ወይም መቀነስ እንደሚችል፣

27.3. በመደበኛው ጨረታ ሠነድ የተጫራቾች መመሪያ ይዘት ላይ ምንም ዓይነት ማሻሻያ ማድረግ አይቻልም:: በተጫራቾች መመሪያ ላይ የሚደረጉት ለውጦች የሚመለከቱት በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ላይ ነው::

28. የጨረታ ቋንቋ

28.1. በአዋጁ አንቀጽ ፩፺ መሠረት የሚዘጋጀው የጨረታ ማስታወቂያ፣ የጨረታ ሠነድ እና ጨረታው የሚካሄድበት ቋንቋ:-

ሀ/ የአገር ውስጥ ተጫራቾች ብቻ ለሚሳተፉበት የብሔራዊ ግልጽ ጨረታ በአማርኛ ቋንቋ ይሆናል:: ሆኖም መ/ቤቱ የጨረታ ቋንቋው በእንግሊዝኛ መሆኑ የተሻለ ውድድርና ጠቀሜታ እንዳለው ሲያምን የጨረታ ማስታወቂያው፣ የጨረታ ሠነዱ፣ እና የጨረታው ሂደት በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል::

ለ/ ለዓለም ዓቀፍ ግልጽ ጨረታ ማስፈጸሚያ የሚዘጋጅ ማናቸውም ሰነድ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ይሆናል::

28.2. ከላይ ዕጬ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሠነዶቻቸውና ደጋፊ ማስረጃዎቻቸው በጨረታ ሠነዱ ጨረታው እንዲካሄድበት ከተፈቀደው ውጭ በሌላ ቋንቋ የተዘጋጀ በሚሆንበት ጊዜ በተለይ የጨረታውን መሠረታዊ ይዘት ሊቀይሩ የሚችሉ ሠነዶች በሕጋዊ ተርጓሚ ከተተረጎመ ቅጂ ጋር አንድ ላይ በማድረግ ማቅረብ አለባቸው::

28.3. የመንግስት መ/ቤቱ በተጫራቹ የቀረበው ሠነድ በመጀመሪያ በተዘጋጀበት እና ለጨረታው በተፈቀደው ቋንቋ ትርጉም መካከል ልዩነት እንዳለው ሲያረጋግጥ ልዩነቱ በጨረታው ይዘት ላይ መሰረታዊ ለውጥ አያመጣም ብሎ ካላመነ በስተቀር ሰነዱን ውድቅ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

29. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ

ሀ/ የመንግስት መ/ቤት በተለይም በተፈጥሯቸው ውስብስብ እና ከፍተኛ ወጪ ለሚጠይቁ ግዥዎች በአዋጁ አንቀጽ ፩፰ መሠረት ዝርዝር የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት አለበት፡፡

ለ/ የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በተጠቃሚዎች ፍላጎት ላይ ተመስርቶ እንደግዥው ዓይነት ጠቀሜታን፣ አሠራርን፣ የቴክኒክ ወይም የዲዛይን ባህርይን መሠረት በማድረግ ውድድርን እንዳይገድብ ተደርጎ መዘጋጀት አለበት፡፡

ሐ/ የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የውሉ አንዱ ክፍል በመሆኑ አቅርቦቱን ትክክለኝነተ ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ይውላል

መ/ የሚፈለገው ዕቃ፣ የምክር አገልግሎት፣ የግንባታ ሥራ ወይም አገልግሎት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ግዥው እንዲፈፀምለት በሚፈልገው ክፍል ወይም ስለሚፈፀመው ግዥ በቂ እውቀት ባላቸው የመ/ቤቱ ባለሙያዎች መዘጋጀት አለበት ፡፡ ከፍተኛ ወጪ በሚጠይቁ እና ውስብስብ በሆኑ ግዥዎች የፍላጎት መግለጫ አዘገጃጀት ላይ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ከመሥሪያ ቤቱ ውጭ ያሉ ባለሙያዎችን ድጋፍ ሊጠይቁ ወይም አማካሪ ቀጥረው ሊያሠሩ ይችላሉ፣

ሠ/ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በሚዘጋጅበት ጊዜ የተወሰነን አምራች የንግድ ምልክት ወይም አገልግሎት ሰጪ ማመልከት የለበትም፡፡ ሆኖም ፍላጎትን በትክክል ሊገልፅ የሚችል መግለጫ ማዘጋጀት አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም ግዥው ለተለየ ፕላንት ወይም መሣሪያ የሚያስፈልጉ መለዋወጫዎችን የሚመለከት ሲሆን ወይም የተፈለጉትን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ማቅረብ የሚችል አንድ አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ ብቻ መሆኑ

ሲረጋገጥ የአምራቹን ወይም የአገልግሎት ሰጪውን ስም በመጥቀስ "ወይም ተመሳሳይ"የሚል ሐረግ እንዲታከል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ረ/ የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የመንግስት መ/ቤቱን የአሁን ወይም ወደፊት ሊፈጠር የሚችል ፍላጎትን ለማርካት የሚያስችሉ የጠቀሜታ እሴቶችን ለመግለፅ የሚያስችል እና ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉ እሴቶችን የማያካትት መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

ሰ/ የመንግስት መሥሪያ ቤቱ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን ወይም እንደግዥው ዓይነት አግባብ ያላቸው ሌሎች አካላት የሚያወጧቸውን ደረጃዎች በዝርዝሩ ውስጥ ሊያካትት ይችላል ፡፡

ሸ/ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የተሟላና ትክክለኛ የመጫረቻ ሠነድ እንዲያዘጋጁ በሚያስችል ዓይነት ተሟልቶ እና በዝርዝር ተዘጋጅቶ የጨረታው ሰነድ አንድ ክፍል መሆን አለበት፡፡

30. <u>የጨረታ ቅፅና የዋጋ ማቅረቢያ ሠንጠረዥ</u>

ሀ/ የመንግስት መ/ቤቶች ለጨረታ በሚያዘጋጁት የጨረታ ሠነድ ውስጥ በኤጀንሲው የተዘጋጀውን ወይም እንደግዥው ባህርይ የመንግስት መ/ቤቱ ያዘጋጀውን በተጫራቾች ሊሞላ የሚገባውን የጨረታ ቅፅ፣ ዋጋና ተያያዥ ጉዳዮችን ማቅረቢያ ቅጽ ወይም ሠንጠረዥ እና በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ውስጥ መካተታቸው ተገቢ ነው ተብሎ የሚታመንባቸው ሌሎች ቅፆችን ማካተት አለባቸው፡፡

ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" መሠረት በመንግስት መ/ቤቶች የሚዘጋጀው የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ እንደአስፈላጊነቱ ዋጋን፣ ታክስን እና ሌሎችን ከዋጋ አቀራረብ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በግልፅ ለማመልከት የሚያስችል እንዲሁም የጨረታ ግምገማን ግልጽና ቀልጣፋ ማድረግ የሚችል መሆን አለበት፡፡

ሐ/ የሚዘጋጀው የጨረታ ቅፅ በተቻለ መጠን ዕጩ ተወዳዳሪው ግልፅ የሆነ የመወዳደሪያ ሐሳብ እንዲያቀርብ የሚያስችል፣ የጨረታ አካሄዱን መረዳቱን የሚያረጋግጥ፣ ጨረታውን የሚያደናቅፉ ድርጊቶች እንዳይፈፀሙ የሚከላከል እና ተጫራቹ ላቀረበው የመወዳደሪያ ሐሳብ ሙሉ ኃላፊነት እንዲወስድ የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል፡፡

31. የጨረታ መገምገሚያ መስፈርት አዘገጃጀት

31.1. የመንግስት መ/ቤቱ የመጫረቻ ሰነድ የሚገመገምበትን መስፈርት በመደበኛ የጨረታ ሠነዱ የብቃትና የግምገማ መሥፈርቶች ክፍል ላይ በግልፅ ማሳየት ይኖርበታል፡፡

31.2. የጨረታ መገምገሚያ መስፈርት እንደ ግዥው አይነት የሚለያይ ቢሆንም ከሚከተሉት ሁለት መሰረታዊ የመምረጫ ዘዴዎች በአንዱ ተፈፃሚ መሆን ይኖርበታል:-

ሀ/ ለግዥው ተቀባይነት ያለውን ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛ መስፈርት በመወሰን ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛውን ካሟሉት ተጫራቾች መካከል አነስተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች መምረጥ፣ ወይም

ለ/ ግዥው የሚኖረውን ጠቀሜታ ወይም ኢኮኖሚያዊ እሴት ሊወስኑ የሚችሉ መስፈርቶችን እና እያንዳንዱ መስፈርት የሚኖረውን አንፃራዊ ክብደት በግልፅ በጨረታ ሰነዱ ላይ በማሳየትና በነዚህ መስፈርቶች ላይ የተመሠረተ ግምገማ በማካሄድ በአጠቃላይ ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘውን መምረጥ፣

31.3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፫፩፥፪፥ (ለ) በተገለጸው መንገድ ግምገማ ለማካሄድ የሚመረጥ መስፈርት ግዥው ማስገኘት የሚችለውን ከፍተኛ ጥቅም እንዲያስገኝ ከማድረግ አንፃር በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሠረተና እስከተቻለ ድረስ በገንዘብ ሊገለፅ የሚችል ሆኖ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል:-

ሀ/ የሚገዛው መደበኛ ወይም ደረጃው የታወቀ አቅርቦት በሚሆንበት ጊዜ ለመ/ቤቱ ጠቃሚ የሆነ እና በተጫራቾች መካከል ልዩነት ሊፈጥር የሚችል የተለየ እሴት ሊቀርብበት የሚችል መሆን አለመሆኑን፤ ወይም

ለ/ የመንግስት መ/ቤቱ ካስቀመጠው ዝቅተኛ መስፈርት በተጨማሪነት የሚቀርብ እሴት ተጨማሪ ፋይዳ ማስገኘት አለማስገኘቱን ወይም

ተጨማሪው እሴት ለመ/ቤቱ የሚሠጠውን ጥቅም ዝቅተኛነትና ከፍተኛነት፣

ሐ/ የሚገዛው ዕቃ ደረጃ ያልወጣለትና ተጨማሪ ፋይዳ ከመፍጠር አንፃር ስፔሲፊኬሽኑን በተለያየ ደረጃ ሊያሟሉ የሚችሉ ተቀራራቢ ዕቃዎች መኖር አለመኖራቸውን፣

መ/ ዕቃው ለረጅም ጊዜ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ሆኖ የአቅርቦቱ ምንጭ በመለያየቱ ምክንያት የተለያየ የመጠቀሚያ፤ የመጠበቂያና የመያዣ እንዲሁም የማስወገጃ ወጪ የሚፈልግ መሆን አለመሆኑን፣

31.4. የመንግስት መ/ቤቱ ተጫራቾች ያቀረቡትን ሠነድ በአንቀፅ ፫፩ በተገለፁት መስፈርቶች መሰረት በመገምገም አሸናፊ የሚሆነውን ተጫራች ከለየ በኋላ የአሸናፊው ተጫራች ወቅታዊ የብቃት ሁኔታ በድሕረ ግምገማ መረጋገጥ አለበት ብሎ ሲያምን ይህንኑና ለድሕረ ግምገማ ዓላማ የሚጠቀምበትን መስፈርት በቅድሚያ በጨረታ ሰነዱ ላይ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

31.5. በንዑስ አንቀፅ ፫፩.፫ መሰረት ለማወዳደሪያነት የሚመረጡት መስፈርቶች ዕቃው ወይም አገልግሎቱ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ለመወሰን አስተዋፅኦ የሚኖራቸው መሆኑን ማረጋገጥ እና የግዥውን ጠቀሜታ ለመወሰን ባላቸው አስተዋፅኦ ደረጃ መሰረት አንፃራዊ ክብደት እንዲሰጣቸው መደረግ ይኖርበታል፡፡

31.6. ለአገልግሎት ግዥ አፈፃፀም በሥራ ላይ የሚውለው የግምገማ ዘዴ በንዑስ አንቀጽ ፫፩.፪ (ለ) ላይ የተመለከተው ሲሆን፣ ለዋጋ የሚሰጠው አንፃራዊ ክብደት ከጠቅላላው የማወዳደሪያ ነጥብ ፳፲% /ሃምሳ በመቶ/ ማነስ የለበትም፡፡

32. <u>አጠቃላይና ልዩ የውል ሁኔታዎች</u>

32.1. ማንኛ□ም የመንግስት መሥሪያ ቤት የመደበኛ የጨረታ ሠነድ ክፍል ሆነው የተዘጋጁትን የአጠቃላይ እና የልዩ ውል ሠነድ ቅጂዎችን የጨረታው ሰነድ ክፍል አድርጐ ለተጫራቾች መስጠት አለበት፡፡

32.2. በመ□በኛ ጨረታ ሠነዱ አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ ማሻሻያ ሊደረግባቸው አይችልም፡፡ ልዩ የውል ሁኔታውን ግን እንደሚፈፀመው ግዥ ባህርይና ዓይነት አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ የሰፈሩትን አንቀጾች በማጣቀስ ማሻሻል ይቻላል፡፡

32.3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፫፪÷፩÷ እና ፫፪÷፪÷ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቶች የሚያዘጋጁት ልዩ የውል ሁኔታ እንደግዥው አይነት ሊለያይ ቢችልም የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት:-

ሀ/ የተጫራቹንና የመንግስት መ/ቤቱን ግዴታና ኃላፊነትን በግልጽ ያመላከተና በመ/ቤቱ ላይ የሚጣሉ ግዴታዎች ህጋዊ መሠረት ያላቸውና ሊፈጸሙ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

ለ/ እንደአስፈላጊነቱ የውሉ አፈጻጸም የሚከተላቸውን ዋና ዋና ሂደቶች፤ የማስረከቢያ ጊዜ፣ አስተሻሸግ፣ የማጓጓዝ ኃላፊነት፣ የዋጋ ማስተካከያ፣ የክፍያ አፈጻጸም፣ የርክክብ እና የፍተሻ ሥነ-ሥርዓት፤ ዋስትና እና የመሳሰሉትን አተገባበር በግልጽ ያስቀመጠ መሆን ይኖርበታል::

# ክፍል 7

## የጨረታ ጥሪና የጨረታ ሰነድ ስለመረከብ

33. የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ

33.1. ፊ ረታ ጥሪው በቂ ቁጥር ያላቸው ተወዳዳሪዎች በጨረታው እንዲሳተፉ ለማድረግ አገራዊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ቢያንስ አንድ ጊዜ ታትሞ መውጣት አለበት::

33.2. ከላይ በን/አንቀጽ 33.1. የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቱ በመረጠው ጊዜና መጠን በአዋጁ አንቀጽ ፪፬ በንዑስ አንቀጽ ፪ በተገለጸው መንገድ እና ሌሎች ተጨማሪ ስልቶችን በመጠቀም ጥሪ ሊያስተላልፍ ይችላል::

33.3. የጨረታው ጥሪ ማስታወቂያ ቢያንስ የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች ሊይዝ ይገባል:-

ሀ/ የጨረታው ጥሪ በማስታወቂያ እንዲወጣ ያደረገውን የመንግስት መ/ቤት ስምና አድራሻ፣

ለ/ የሚቀርበውን ዕቃ ወይም አገልግሎት፣ ዓይነት፣ ከተቻለ ብዛት እና ርክክቡ የሚፈፀምበትን ቦታ ወይም የግንባታ ሥራውን ዓይነት እና የሚከናወንበትን ቦታ ወይም የምክር አገልግሎቱን ዓይነት እና የሚካሄድበትን ቦታ፣

ሐ/ □ጬ ረታው መሳተፍ የሚችሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሊያሟሉ የሚገባውን መሥፈርት፣

መ/ የጨረታው ሰነድ የሚገኝበትን ቦታ፣

ሠ/ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና መጠን፣

ረ/ የጨረታውን ሰነድ ለመውሰድ የሚከፈልን ዋጋ፣እና የአከፋፈሉን ዘዴ፣

ሰ/ የመጫረቻ ሠነዱ የመጨረሻ ማስረከቢያ እና የሚከፈትበትን ቀን ፣ቦታና ሰዓት፣

ሸ/ የመንግስት መሥሪያቤቱ ጨረታውን በከፊል ወይም በሙሉ ለመሠረዝ መብት ያለው መሆኑን፣ እና

ቀ/ ለተጫራቾች መገለጽ እንዳለባቸው በመሥሪያ ቤቱ የታመነባቸው ሌሎች ጉዳዮች፣

33.4.. የጨረታው ጥሪ በዚህ መመሪያ አንቀፅ ፪፰ ላይ በተገለፀው መሰረት ጨረታው በሚካሔድበት ቋንቋ መዘጋጀት ይኖርበታል።

34. ጨረታ ለእጩ ተወዳዳሪዎች በአየር ላይ ክፍት ሆኖ የሚቆይበትን ጊዜን ስለመወሰን

፫፬፥፩፥ የመንግስት መሥሪያ ቤት የጨረታ ሰነድ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የመጫረቻ ሠነድ የሚቀርብበትን የመጨረሻ ቀን የሚከተሉትን መሠረት አድርጎ ይወስናል:-

ሀ/ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሠነዱን ለማግኘት፣ ተቀባይነት ያለው የመጫረቻ ሠነድ ለማዘጋጀት፣ መረጃ ለማሰባሰብ፣ ለመተንተን፣ እንደአግባብነቱ ሽርክና መመሥረት፣ ከአምራቹ የሚሠጥ ውክልና እና የመፈረም ሥልጣን ማረጋገጫ ለማግኘት እና ሌሎች በጨረታው

ለመሳተፍ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የሚፈጅባቸውን ጊዜ፣

ለ/ ግዥው በዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የሚፈፀም ሲሆን የመጫረቻ ሠነዱን የጨረታ ማቅረቢያው ቦታ ድረስ ለመላክ የሚያስፈልገውን ጊዜ፣

ሐ/ በተለይ የግንባታ ሥራ ግዥ በሚሆንበት ጊዜ ለግንባታ ቦታ ጉብኝትና ከጨረታ በፊት ለሚደረግ ቅድመ ጨረታ ውይይት የሚያስፈልገውን ጊዜ፣

፴፬÷፪÷ በንዑስ አንቀጽ 34.1 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ጨረታ በአየር ላይ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ በዚህ መመሪያ አባሪ ቁጥር ፫ ላይ ከተገለጸው ቀን ያነሰ መሆን የለበትም::

35. <u>የመጫረቻ ሠነድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ</u>

35.1. የመንግስት መ/ቤቱ የመጫረቻ ሠነድ ፀንቶ መቆየት ያለበትን ጊዜ በጥንቃቄ በመወሰን በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ማካተት ይኖርበታል:: የመጫረቻ ሰነድ ወይም የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንደ ግዥው አይነት ሊለያይ የሚችል ቢሆንም ጊዜውን ለመወሰን መ/ቤቱ የሚከተሉትን ማገናዘብ ይኖርበታል:-

ሀ/ የግዥውን ውስብስብነት እና የጨረታ አፈፃፀም ሂደቱ ሊወስድ የሚችለውን ጊዜ፣

ለ/ በጨረታው ሊሳተፉ የሚችሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ብዛት፣

ሐ/ የመንግስት መ/ቤቱ ተመሳሳይ ግዥዎችን በመገምገም ረገድ ያለው ልምድ፣

መ/ ግዥው በገበያ ላይ ያለውን የዋጋ ተለዋዋጭነት ሁኔታ፣

35.2. በንዑስ አንቀፅ ፴፭.፩ ላይ በተገለፀው መሰረት የሚወሰነው የጨረታ ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የመንግስት መ/ቤቱ ግዥውን ለመገምገም፣ በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ግዥውን ለማፀደቅ፣ አቤቱታ ቢነሳ ለማስተናገድ እና

ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል እስከመፈራረም ድረስ የሚፈጀውን ጊዜ ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

35.3. በንዑስ አንቀፅ ፫፭.፪ ላይ በተገለፀው መሰረት የመጫረቻ ሰነድ ረዘም ላለ ጊዜ ፀንቶ የሚቆይበት ሁኔታ መኖሩን መ/ቤቱ ካላመነ በስተቀር ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ጨረታው ከሚከፈትበት ዕለት ጀምሮ ከ፯፲ ተከታታይ ቀናት መብለጥ የለበትም፡፡

35.4. የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ ሂደታቸውን የመጫረቻ ሰነዱ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል መፈራረም ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች የግዥ ሂደቱ ሳይጠናቀቅ ለግዥው የቀረበው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የሚያበቃ መሆኑን መ/ቤቱ ሲረዳ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ዋጋቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለተጨማሪ ቀናት እንዲያራዝሙለት መጠየቅ አለበት፡፡

35.5. በንዑስ አንቀፅ ፫፭.፬ ላይ በተመለከተው መሰረት ተጫራቾች እንዲያራዝሙ የሚጠየቁት ተጨማሪ ቀናት የመንግስት መ/ቤቱ የቀረውን የግዥ ሒደት ለማጠናቀቅ የሚበቃውን ያህል ቀናት ብቻ መሆን አለበት፡፡ ሆኖም ተጫራቾች በማንኛውም ምክንያት ዋጋቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማራዘም ፈቃደኛ ባይሆኑ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙትን ዋስትና መውረስ ሳያስፈልግ ከጨረታው ውድድር እንዲወጡ ይደረጋል፡፡

35.6. የቀረበላቸውን ዋጋቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ የማሻሻል ጥያቄ የተቀበሉ ተጫራቾች ጥያቄውን መቀበላቸውን እና የመቆያ ጊዜውን ያራዘሙት እስከመቼ እንደሆነ በመጥቀስ በጽሑፍ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ለዚህ ጨረታ ያስያዙት የጨረታ ዋስትና መቆያ ጊዜ ማሻሻል ወይም አዲስ ዋስትና ማቅረብ አለባቸው፡፡

35.7. በንዑስ አንቀፅ ፫፭.፮ በተገለጸው መሠረት የጨረታ ዋስትናውን ፀንቶ መቆያ ጊዜ ያላሻሻለ ተጫራች ያቀረበው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማሻሻል ፈቃደኛ እንዳልሆነ ተቆጥሮ ከጨረታው ውድድር ውጭ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 36. የጨረታ ማስከበሪያ

36.1. ከምክር አገልግሎት ግዥ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ግልፅ ወይም ውስን ወይም የሁለት ደረጃ ጨረታ የግዥ ዘዴዎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ በጨረታው ሠነድ ውስጥ ለእያንዳንዱ ግዥ የሚጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በግልፅ መወሰንና ማመልከት አለባቸው:: ሆኖም በተለያዩ ምክንያቶች አስፈላጊነቱን መ/ቤቱ ካመነበት ለምክር አገልግሎት ግዥም ቢሆን ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንዲያሲዙ ሊጠይቅ ይችላል::

36.2. የመንግስት መ/ቤቱ የጠቅላላ ግዥውን ግምታዊ ዋጋ መሠረት በማድረግ ከ0.፭% ያላነሰና ከ፪% ያልበለጠ የጨረታ ማስከበሪያ የገንዘብ መጠን ወስኖ በጨረታ ጥሪው እና በጨረታ ሰነዱ ውስጥ መግለፅ ይኖርበታል:: በዚህ መሠረት የሚወሰነው የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ከብር 500,000.00 የበለጠ መሆን የለበትም::

36.3. በንዑስ አንቀጽ ፫፮.፪ በተገለጸው መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች የጨረታ ማስከበሪያ መጠንን ለመወሰን የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል:-

ሀ/ የሚገዛው ዕቃ/አገልግሎት የዋጋ ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ተለዋዋጭ መሆን፣

ለ/ በጨረታው የሚሳተፉ በቂ ተወዳዳሪዎች መኖር፣

ሐ/ ተጫራቾች እንዲያቀርቡ የሚጠየቀው ዋስትና በጨረታው እንዳይሳተፉ እንቅፋት እንደማይሆን፣

መ/ አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው ተጫራች ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ እንዲሆን የሚገፋፋ፣

ሠ/ አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው ተጫራች ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ባይሆን ዋስትናው በመ/ቤቱ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለማካካስ የሚመጥን መሆኑን፣

36.4. የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንደተጫራቹ ምርጫ በጥሬ ገንዘብ ወይም ከታወቀ ባንክ በሚሰጥ የክፍያ ማዘዣ ቼክ ወይም የባንክ ዋስትና ወይም በባንክ የተረጋገጠ ሌተርኦፍ ክሬዲት ሊሆን ይችላል፡፡

36.5. በንዑስ አንቀጽ ፫፮.፬ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በግንባታ ሥራ ዘርፍ የተሠማሩ የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች ለጨረታ ማስከበሪያ በሁኔታ ላይ የተመሠረተ የመድን ዋስትና ቢያቀርቡ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

36.6. ከተጫራቾች የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ፀንቶ መቆያ ጊዜ የጨረታው ዋጋ ፀንቶ ከሚቆይበት የመጨረሻ ቀን በኋላ ቢያንስ ለተጨማሪ 28 ቀናት ፀንቶ መቆየት ይኖርበታል፡፡

36.7. የውጭ አገር ተጫራቾች የሚያቀርቡት ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉ ባንኮች የተሠጠ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በአገር ውስጥ ባንኮች ማረጋገጫ ያገኘና በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ መሆን ይኖርበታል፡፡

36.8. ማናቸውም ተጫራች የሚከተሉትን ተግባራት ባለመፈጸሙ ምክንያት ያስያዘው ዋስትና በመንግስት መ/ቤቶች ሊወረስበት ይችላል:-

ሀ/ በጨረታ ሠነዱ የተገለጸው የመጫረቻ ሠነድ ማቅረቢያ የመጨረሻ ጊዜ ካለፈ በኋላ ወይም በመጫረቻ ሠነዱ ላይ በተገለጸው የጨረታ ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተጫራቹ ራሱን ከጨረታው ካገለለ፣

ለ/ በጨረታው ውድድር አሸናፊ በመሆኑ ውል እንዲፈርም እና የውል ማስከበሪያ እንዲያሲዝ ተጠይቆ ውል ለመፈረም እና የተጠየቀውን የውል ማስከበሪያ ለማስያዝ ፈቃደኛ ካልሆነ፣

37. <u>የጨረታ ሠነድ ሽያጭ</u>

37.1. ለማንኛውም ጨረታ የተዘጋጀው የጨረታ ሠነድ የመሸጫ ዋጋ በአዋጁ አንቀጽ ፪፯ መሠረት የሚከተሉትን ግምት ውስጥ በማስገባት በመንግስት መ/ቤቶች የሚወሰን ይሆናል:-

ሀ/ የጨረታ ሰነድ መሸጫ ዋጋ የመንግስት መ/ቤቱ ለግዥው በርካታ ተወዳዳሪዎች እንዳያገኝ የሚያደርግ መሆን የለበትም፣

ለ/ የመንግስት መ/ቤቶች ለማንኛውም የጨረታ ሠነድ የዋጋ ተመን በሚወስኑበት ወቅት ትርፍን ማዕከል ያላደረገና ለሰነድ ዝግጅቱ የወጣውን ወጪ ለመተካት ብቻ ያለመ መሆን ይኖርበታል::

፫፯÷፪÷ የመንግስት መ/ቤቶች የሚከተሉትን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደአስፈላጊነቱ የጨረታ ሠነዱ በነፃ እንዲሠጥ ወይም ለጨረታ ሠነድ ዝግጅቱ ከወጣው ወጪ ባነሰ ለተጫራቾች እንዲሸጥ ሊፈቅዱ ይችላሉ:-

ሀ/ በጨረታው በቂ ተወዳዳሪ አይኖርም ተብሎ ሲገመት፣ ወይም

ለ/ ለጨረታ ሠነድ ዝግጅቱ የወጣው የወጪ ግምት በጣም አነስተኛ ነው ብሎ መ/ቤቱ ሲያምን፣ ወይም

ሐ/ ለጨረታ ሠነድ ዝግጅቱ የወጣው የወጪ ግምት ከፍተኛ በመሆኑ ወጪውን ሙሉ በሙሉ ተጫራቾች እንዲሸፍኑ ቢደረግ የጨረታ ሰነዱ የመሸጫ ዋጋ ከፍተኛ ስለሚሆን በቂ ተወዳዳሪ እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል ብሎ ሲያምን፣

መ/ ጨረታው በድጋሚ እንዲወጣ የተደረገ እና በመጀመሪያው ጨረታ ለመሳተፍ ሰነድ የገዙ እጩ ተወዳዳሪዎችን እንደገና እንዲገዙ ማድረግ ተገቢ አለመሆኑ በመ/ቤቱ ሲታመን፣

፫፯÷፫÷ ጨረታ ሠነዱ ጨረታው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚዘጋበት ጊዜ ድረስ ባሉት የሥራ ቀናት በጨረታ ማስታወቂያው በተገለጸው አኳኋን ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ዝግጁ መሆን አለበት::

## 38. ስለናሙና አቀራረብ

38.1. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ ወይም ከተዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በተጨማሪነት ግዥው በተሻለ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው የናሙና ምልከታ ሲኖረው መሆኑ ሲታመንበት የመንግስት መ/ቤቱ በተጨማሪነት ናሙና ሊያቀርብ ወይም እንዲቀርብ ሊያደርግ ይችላል::

38.2፥ የመንግስት መ/ቤቱ ናሙና ራሱ አቅርቦ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ለዕይታ በቀረበው ናሙና መሠረት እንዲያቀርቡ በሚፈለግበት ወቅት:-

ሀ/ በመንግስት መ/ቤቱ የሚቀርበው ናሙና በአንድ አምራች ወይም የንግድ ምልክት በተሠራ ዕቃ የተወሰነ መሆን የለበትም:: እስከተቻለ ድረስ ተቀባይነት ያላቸው ናሙናዎች አይነት ለዕይታ እንዲቀርቡ ሆኖ ከቀረቡት ናሙናዎች ጋር ተመሳሳይ የሆነ የጥራት ደረጃ ያላቸው ሌሎች ዕቃዎችንም ማቅረብ እንደሚቻል ለተጫራቾች ማሳወቅ ይገባል::

ለ/ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ናሙናውን በግልፅ የሚያዩበት ቦታ ላይ መደረጉን እና ተገቢ እስከሆነ ድረስ ስለናሙናው መግለጫ የሚሰጥ ባለሙያ መመደቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ሐ/ መ/ቤቱ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ዕይታ ካቀረበው ናሙና በተጨማሪ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የሚያዘጋጅ ከሆነ የሚዘጋጀው መግለጫ እስከተቻለ ድረስ የቀረበውን ናሙና የሚገልፅና ለዕይታ ከቀረበው ናሙና የቴክኒክ ባሕርይ ጋር የተጣጣመ ሊሆን ይገባል::

38.3. በተሰጣቸው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ መሰረት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ናሙና እንዲያቀርቡ በሚፈለግበት ወቅት:-

ሀ/ የሚቀርቡት ናሙናዎችን አይነት፣ ብዛት የሚቀርቡበት ጊዜ እና አኳኋን ዕጩ ተወዳዳሪዎች በግልፅ እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል፣

ለ/ ናሙናዎች ጨረታው ከመከፈቱ በፊት መቅረብ ያለባቸው ቢሆንም ዕጩ ተወዳዳሪው ናሙናውን በወቅቱ ልኮ ከዕጩ ተወዳዳሪው ቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት በማጓጓዝ ሂደት ቢዘገይ የመንግስት መ/ቤቱ የግዥውን አፈፃፀም አይጎዳም ብሎ እስካመነ ድረስ ተጨማሪ የናሙና ማቅረቢያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል::

38.4. ተጫራቾች የተሟላ ናሙና በአካል ማቅረብ የማይችሉ ሲሆን እና የማይችሉበትንም ምክንያት የመንግስት መ/ቤቱ ሲቀበለው ስለናሙናው ያላቸውን መረጃ ማቅረብ እንዲችሉ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ይህም የናሙናውን ፎቶግራፍ ወይም የተገኘውን የናሙና ክፍል ማቅረብን ይጨምራል፡፡ ሆኖም በዚህ መልኩ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚቻለው አፈፃፀሙ የተሻለውን ተጫራች በመምረጥ ሒደት ልዩነት የማያመጣ እና በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ልዩነት ሊፈጥር የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

38.5. የመንግስት መ/ቤቱ በተጫራቾች የቀረቡ ናሙናዎችን በጥንቃቄ የመያዝ እና የመፈተሽ ኃላፊነት አለበት፡፡ ሆኖም ተጫራቾች ያቀረቡት ናሙና በሚመረመርበት ወቅት በዕቃው ባህርይ ምክንያት ቢጠፋ ወይም ቢበላሽ ካሣ አይከፈላቸውም፡፡ በምርመራ ሂደት ያልጠፉ ወይም ያልተበላሹ ናሙናዎች ከምርመራ በኋላ ለተጫራቾች ተመላሽ ይደረጋሉ፡፡ ተጫራቾች ያቀረቡትን ናሙና የጨረታው ውጤት ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልወሰዱ በውርስ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል፡፡

38.6. በመንግስት መ/ቤቱ የተለየ ውሳኔ ካልተሰጠ በስተቀር የአሸናፊው ተጫራች ናሙና ግዥው እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ በናሙናነት ተይዞ መቆየት ያለበት ሲሆን ናሙናውም በርክክብ ወቅት ለማነፃፀሪያነት እንዲያገለግል መደረግ ይኖርበታል፡፡

39. በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማብራሪያ ወይም ማሻሻያ

39.1. በአዋጁ አንቀጽ ፬፰ መሠረት የመንግስት መሥሪያ ቤቶች በመሥሪያ ቤቱ በተዘጋጀ የጨረታ ሠነድ ላይ ከማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ የሚቀርብ የማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄን ተቀብለው ምላሽ መስጠት አለባቸው፡፡

39.2. በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፫፱.፩ የተደነገገው ቢኖርም የሚከተለውን ሳያሟላ ለቀረበ ማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ መሥሪያ ቤቱ ምላሽ እንዲሰጥ አይገደድም:-

ሀ/ በዚህ መመሪያ በተገለፀው መሰረት ጨረታው ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ 30 የሥራ ቀናት ለሆነ ውስብስብ የአገር ውስጥ ግዥ ለመጫረቻ ሠነድ ማቅረቢያ የተወሰነው ጊዜ ሊያበቃ ከ1፲ ቀናት በታች ሲቀረው ለቀረበ ጥያቄ፣

ለ/ ለዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ለመጫረቻ ሠነድ ማቅረቢያ የተወሰነው ጊዜ ሊያበቃ ከ፪፩ ቀናት በታች ሲቀረው ለቀረበ ጥያቄ፣

ሐ/ ጨረታው ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ ፩፫ ቀናት ብቻ ለሆነ ውስብስብ ያልሆነ ግዥ ጨረታው ሊዘጋ ከ፫ ቀናት በታች ሲቀረው ለቀረበ ጥያቄ፣

39.3 ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ለሚቀርብ የማብራሪያ ጥያቄ የሚሠጠው ምላሽ በጽሑፍ ሆኖ የጠያቂውን ማንነት መግለጽ ሳያስፈልግ ለሁሉም በጨረታው ተሳታፊ ለመሆን ላመለከቱ ዕጩ ተወዳዳሪዎቸ በሙሉ በተመሳሳይ ጊዜ እንዲላክ መደረግ አለበት።

39.4 የመንግስት መ/ቤቶች ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚቀርብላቸውን የማብራሪያ ጥያቄ መነሻ በማድረግ ቀደም ሲል በመሥሪያ ቤቱ በተዘጋጀ የጨረታ ሠነድ ላይ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት የጨረታ ሠነዱን ማሻሻል ይችላሉ። ማንኛውም የጨረታ ሠነዱን ይዘት የሚቀይር ማሻሻያ በተጨማሪ የጨረታ ሠነድነት የጨረታውን ሠነድ ለገዙ ሁሉ በእኩል ጊዜ እንዲደርስ መደረግ አለበት።

39.5 የመንግስት መ/ቤቶች በንዑስ አንቀፅ ፫፱.፬ ላይ በተገለፀው መሰረት በጨረታ ሰነዱ ላይ ማሻሻያ ሲያደርጉና ጨረታውን ለመዝጋት በቀረው ጊዜ ውስጥ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የተደረገውን ማሻሻያ አካተው የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት እንደማይችሉ ሲገመት የጨረታ መዝጊያ ቀኑን ማራዘም ይኖርባቸዋል።

39.6 የመንግስት መ/ቤቱ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን በመሥሪያ ቤቱ በተዘጋጀ የጨረታ ሠነድ ላይ የጨረታ ሠነድ የገዙትን ተጫራቾች በሙሉ የማብራሪያና የማሻሻያ ገለጻና ውይይት ለማድረግ ሊጠራ ይችላል። የሚደረገው ውይይትም በቃለ -ጉባዔ መያዝ ይኖርበታል።

39.7 ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሠነዳቸውን በሚያዘጋጁበት ወቅት ማሻሻያውን ማካተት እንዲችሉ በተደረገው የጨረታ ሠነድ ማሻሻያና ማብራሪያ ውይይት ላይ የተያዘው ቃለ-ጉባዔ ቅጂ የጨረታውን ሠነድ ለገዙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሙሉ እንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡

## 40. <u>ከተጫራቾች ጋር ስለሚደረግ ውይይት</u>

40.1. በግዥ ሂደት በማናቸውም ደረጃ ከተጫራቾች ጋር ውይይት ሊደረግ የሚችለው የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥም ብቻ ይሆናል፡፡ በመንግስት መሥሪያ ቤቱ እና በአቅራቢዎች መካከል የሚደረጉ ውይይቶች በሁለት የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ይሆናሉ፡፡

እነዚህም፡-

ሀ/ በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ለመወያየት፣ ወይም

ለ/ የሁለት ደረጃ ጨረታ በሚሆንበት ጊዜ ጨረታው በሚያካትታቸው የግዢ ዓይነቶች ላይ ድርድር ለማድረግ፣

40.2. በንዑስ አንቀጽ ፬፲÷፩÷ በተፈቀደው መሠረት ካልሆነ በስተቀር፣ ጨረታውን ያወጣው የመንግስት መ/ቤት ጨረታው ከተከፈተ በኋላ የመወዳደሪያ ሃሳቡን ለመገምገም በሚያስችሉ ነጥቦች ላይ ማብራሪያ ከመጠየቅ በስተቀር ተጫራቾች ካቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ ውስጥ ዋጋን ወይም ሌሎች መሠረታዊ የሆኑ ነጥቦችን እንዲለውጡ መጠየቅ ወይም መፍቀድ የለበትም፡፡

## 41. <u>የመጫረቻ ሠነድ ስለመረከብ</u>

፬፩÷፩÷ የመንግሥት መ/ቤቶች ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዶቻቸውን የሚያስገቡበት የጨረታ ሳጥን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ የጨረታ ሳጥኑም የጨረታ ጥሪው ላይ በተገለፀው ቦታ ጥሪ ከተደረገበት ዕለት ጀምሮ እስከ መጨረሻው የመዝጊያ ሰዓት ድረስ ክፍት ሆኖ መገኘት ይኖርበታል፡፡

41.2. የጨረታ ሳጥን ደህንነት የተጠበቀ መሆን ያለበት ሲሆን ጨረታው እስከሚከፈት ድረስ ቁልፉ በግዥ የሥራ ክፍል ኃላፊ ተይዞ መቆየት ይኖርበታል፡፡

41.3. እስከተቻለ ድረስ ማንኛውም የመጫረቻ ሰነድ ለጨረታው በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ ገቢ መደረግ አለበት፡፡ ሆኖም ለግዥው የሚቀርበው የመጫረቻ ሠነድ በሳጥን ውስጥ ሊገባ የማይችል በሚሆንበት ጊዜ መ/ቤቱ የጨረታ ጥሪ ከተደረገበት ዕለት ጀምሮ የመጫረቻ ሠነድ የሚረከብ ሠራተኛ በመመደብ በተጫራቾች የሚቀርብን የመጫረቻ ሰነድ መረከብ ይኖርበታል፡፡

41.4. በንዑስ አንቀፅ ፬፩.፫ ላይ በተገለጸው መሰረት የመንግስት መ/ቤቱ ለሚረከበው የመጫረቻ ሰነድ መረከቡን የሚያረጋግጥ የመተማመኛ ሰነድ ሊሰጥ ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት የቀረቡ የመጫረቻ ሰነዶች ደህንነት መጠበቁን ግዥውን ለመፈጸም የተመደበው ኃላፊ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

41.5. ከመጫረቻ ሠነድ ማስረከቢያ የመጨረሻ ቀንና ሰዓት በኋል ዘግይቶ የደረሰ የመጫረቻ ሰነድ እሽጉ ሳይከፈት ወዲያውኑ ለተጫራቹ ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

# ክፍል 8. የጨረታ አከፋፈትና ግምገማ

## 42. □ፊ ረታ አከፋፈት

፬፪÷፩÷ ፊ ረታ□· የሚከፈተው በጨረታው ጥሪ ወይም ማሻሻያ ተደርጎ ከሆነ በማሻሻያ ሰነዱ ላይ በተገለጸው ቀን፣ ሰዓትና ቦታ በግልጽ ይሆናል፡፡ ጨረታው ሲከፈትም፡-

ሀ/ ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በሚገኙበት ይሆናል፡፡ ሆኖም ተጫራቹ በራሱ ምርጫ ጨረታው በሚከፈትበት ጊዜ ሳይገኝ መቅረቱ የጨረታውን መከፈት አያስተጓጉልም፣

ለ/ የጨረታ አከፋፈት ሂደቱን እስካላወከ እና የቦታ ጥበት እስከሌለ ድረስ በጨረታው አከፋፈት ሂደት ላይ መገኘት የሚፈልግ ማንኛውም የመገናኛ ብዙሐን ድርጅት ወኪል ወይም ሌላ ፍላጎት ያለው ሰው በታዛቢነት መገኘት ይችላል፣

ሐ/ እስከተቻለ ድረስ የውስጥ ኦዲት ተወካይ ጨረታው ሲከፈት መገኘት አለበት፣

መ/ ከግዥ ሥራ ክፍል ቢያንስ ፫ ባለሙያዎች በጨረታ አከፋፈት ሂደቱ ላይ መሳተፍ ይኖርባቸዋል፡፡ሆኖም እስከተቻለ ድረስ የግዥው ተጠቃሚ ከሆኑ ሥራ ሂደቶች የሚወከሉ ባለሙያዎች በአከፋፈት ስነ - ስርዓቱ ላይ ሊገኙ ይችላሉ፡፡

42.፪ በአንድ ኤንቬሎፕ እንዲቀርብ የተጠየቀ ጨረታ ከሆነ መ/ቤቶች እያንዳንዱ ዕጩ ተወዳዳሪ ያቀረበውን የመጫረቻ ሠነድ በመክፈት የተጫራቹን ስም፣ ለውሉ ያቀረበውን ዋጋ፣ የዋጋ ቅናሽ መጠንና ሁኔታውን፣ የጨረታ ማስከበሪያ ዓይነትን እና መጠን እና ማናቸውንም ዕጩ ተወዳዳሪዎች አንጻራዊ ደረጃቸውን ለማወቅ ይረዳቸዋል ተብለው የሚታሰቡ ሌሎች ሁኔታዎችን በንባብ ማሰማት አለባቸው፡፡

፬፪.፫ ጨረታው በሁለት ኤንቬሎፕ እንዲቀርብ የተጠየቀ ከሆነ፡-

ሀ/ በጨረታው መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት የቴክኒክ ዶክመንቱን የያዘው ኤንቬሎፕ እንዲከፈት ተደርጎ የተጫራቹን ማንነት ጨምሮ በወቅቱ ሊገለጹ የሚችሉ ነጥቦች በንባብ መሰማት አለባቸው::

ለ/ የሁሉም ዕጩ ተወዳዳሪዎች የዋጋ ኤንቬሎፕ ሳይከፈት አንድ ላይ በሌላ አንቬሎፕ ታሽጎና በእሽጉ ላይ የጨረታው መለያ ቁጥር ተፅፎበት፣ የዋጋ ኤንቬሎፖች መሆናቸው ተገልጾ እና ጨረታውን የከፈቱት የመ/ቤቱ ባልደረቦች ተፈራርመውበት ሁለተኛው ዙር የጨረታ መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት እስከሚካሄድ ድረስ የታሸገው ፖስታ በግዥ ሥራ ክፍል ወይም ኃላፊነት በተሰጠው አካል በጥንቃቄ ተይዞ መቆየት ይኖርበታል::

ሐ/ የቴክኒክ ግምገማ ተደርጎ የተገኘው ውጤት ስልጣን በተሰጠው አካል ከፀደቀ በኋላ ውጤቱ በጨረታው ለተሳተፉ ተጫራቾች በሙሉ በተመሳሳይ ጊዜ በጽሑፍ መገለጽ ይኖርበታል::

መ/ የቴክኒክ ግምገማውን ላላለፉ ተጫራቾች የሚጻፈው ደብዳቤ በጨረታው የተሸነፉበትን ምክንያት የሚገልጽ መሆን አለበት:: ተጫራቾቹም አቤቱታ ካላቸው አቤቱታቸውን ማቅረብ ይችላሉ:: አቤቱታ የሚቀርብበት እና የሚመረመርበት ስርዓት በዚህ መመሪያ ክፍል አሥራ አንድ የተገለፁትን ሁኔታዎች ተከትሎ ይሆናል::

ሠ/ የቴክኒክ ውጤታቸው ተቀባይነት ላገኘ ተጫራቾች የሚጻፈው ደብዳቤ የዋጋ ኤንቬሎፕ የሚከፈትበትን ዕለት፣ ሰዓት እና ቦታ የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል:: ደብዳቤውም በዕኩል ጊዜ እንዲደርሳቸው መደረግ እና ሁሉም ፈቃደኛ ተጫራቾች በጨረታው የዋጋ ኤንቬሎፕ መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ እንዲገኙ የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል:: ሆኖም አቤቱታ የቀረበ ከሆነ አቤቱታው ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ የዋጋ ኤንቬሎፑ መከፈት የለበትም::

ረ/ በንዑስ አንቀፅ ፬፪.፫ (ሠ) መሠረት በሚደረግላቸው ጥሪ ተከትለው የቴክኒክ ግምገማውን ያለፉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚገኙበት የዋጋ መወዳደሪያቸውን የያዘው ኤንቬሎፕ በግልጽ እንዲከፈት ይደረጋል::

ሰ/ ለዋጋ ውድድር ያለፉ ተወዳዳሪዎችን ኤንቬሎፕ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፬፪.፫(ረ) ላይ በተገለጸው መሠረት በመክፈት የተጫራቹን ስም፣ ለግዥው ያቀረበውን ዋጋ፣ የዋጋ ቅናሽ ካለው መጠኑን እና

ሁኔታውን፣ እንዲሁም ከዋጋ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ተጫራቾች እንዲያውቁ መደረግ አለበት::

ሸ/ የቴክኒክ ግምገማው ውጤት እንደታወቀ በቴክኒክ ውድድሩ ተቀባይነት ያላገኙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንዲሁም የዋጋ መወዳደሪያቸውን የያዘው ኤንቬሎፕ ሳይከፈት ተመላሽ ይደረግላቸዋል:: ሆኖም በንዑስ አንቀጽ ፬፪.፫ (መ) መሠረት በቴክኒክ ግምገማው ወጤት ላይ አቤቱታ የቀረበ ከሆነ በአቤቱታው ላይ የሚሰጠው የመጨረሻ ወሳኔ እስኪታወቅ ድረስ በቴክኒክ የወደቁት ተጫራቾች የዋጋ ማወዳደሪያ ኢንቬሎፕም ሆነ ያስያዟቸው የጨረታ ዋስትናዎች ተመላሽ አይደረጉም ::

፬፪.፬ የመንግሥት መ/ቤቱ የግዥ ሥራ ክፍል የጨረታውን አከፋፈት ሂደት ቃለ-ጉባዔ መያዝ አለበት:: ይህም ቃለ-ጉባዔ የተጫራቾቹን ሥም፣ ያቀረቡትን ዋጋ እና በጨረታው አከፋፈት ሂደት ላይ የተነሡ ሌሎችንም አስፈላጊ ነጥቦች የሚይዝ ይሆናል:: ቃለ-ጉባዔው እና ተጫራቾች ያቀረቡት ዋናው የመጫረቻ ሰነድ በጨረታ አከፋፈት ሂደቱ ላይ በተገኙት የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ይፈረማል:: ጨረታው በተከፈተበት ጊዜ የተገኙ ተጫራቾች መገኘታቸውን በሚያረጋግጠው ዝርዝር ላይ እንዲፈርሙ ይደረጋል::

፬፪.፭ ማንኛውም በጨረታ መክፈቻ ሥርዓት ላይ ያልተከፈተና ለተጫራቾች ያልተነበበ የመጫረቻ ሠነድ ለቀጣይ ውድድር ሊያገለግል አይችልም::

፬፪.፮ ማናቸውም ተጫራች በጨረታ መክፈቻ ሂደት ወቅት ከጨረታው ውጭ ሊደረግ አይገባም::

## 43. <u>ጨረታን መገምገምና ማወዳደር</u>

### 43.<u>፩ የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ</u>

43.፩÷፩÷ መንግስት መ/ቤቱ ጨረታውን የተሟላ ነው ብሎ ለቀጣዩ ዝርዝር የግምገማ ሂደት ሊያሳልፈው የሚችለው በተጫራቹ የቀረበው የመጫረቻ ሠነድ በመክፈቻ ስነ-ስርዓቱ ወቅት የተከፈተ እና በጨረታ ሰነዱ ላይ የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎችና ተፈላጊ ነጥቦች የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

43.1.፪ ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የማያሟሉ ተጫራቾችን ወደ ዝርዝር ግምገማ ማሳለፍ የለበትም፡-

ሀ/ በጨረታው የተወዳደረው አቅራቢ መ/ቤቱ የሚፈልገውን አነስተኛውን የጥራት መመዘኛ እና ሌሎች መሰረታዊ መስፈርቶችን ያላሟላ በመሆኑ ብቃት የሌለው ሆኖ ሲገኝ፣

ለ/ በንዑስ አንቀጽ 43.1.3 መሠረት የተደረገውን የሂሳብ ስህተት ማስተካከያ የማይቀበል አቅራቢ ሲሆን፣

ሐ/ ተጫራቹ የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ ያላስያዘ ወይም የውል ማስከበሪያ ለማስያዝ ፈቃደኛ ያልሆነ ከሆነ፣

መ/ በመሥሪያቤቱ የተጠየቁትን አስፈላጊ ማስረጃዎች ያላቀረበ ከሆነ፣

43.1.፫ በንዑስ አንቀፅ ፴፫.፩÷፩÷ ላይ የተመለከተው ቢኖርም የመንግስት መ/ቤቱ በምርመራ ወቅት የተገኙ የሒሳብ ስህተቶችን ማረም ይችላል፡፡ እንደዚህ ያሉትን የማስተካከያ ዕርምጃዎች የመንግስት መሥሪያ ቤቱ ባፋጣኝ ለሚመለከተው ተጫራች በፅሑፍ ማስታወቅ አለበት፡፡ ተጫራቹ በሒሳብ ማስተካከያው የማይስማማ ከሆነ ከጨረታው እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

43.1.፬ በጨረታ ሰነዱ ከተዘረዘሩት ባህርይዎች፣ የውል ሁኔታዎች እና ከሌሎች ተፈላጊ ነጥቦች ጋር መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እና ልዩነት እስከሌለው ድረስ ወይም የጨረታው ቁምነገር ሳይለወጥ ሊታረም የሚችል ጥቃቅን ስህተት

ወይም ግድፈት ቢኖረውም የመንግስት መ/ቤቱ ጨረታውን እንደተሟላ አድርጎ ሊቀበል ይችላል፡፡ ሆኖም ማናቸውም ልዩነት እስከተቻለ ድረስ በገንዘብ ተገልጾ በጨረታው ግምገማ እና ውድድር ወቅት ከግምት ውስጥ እንዲገባ መደረግ አለበት፡፡

## 43.፪ ዝርዝር ግምገማ ማድረግና አሸናፊውን መለየት

43.፪.፩ የመንግስት መ/ቤቱ አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ በመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ የተቀበላቸውን የመጫረቻ ሰነዶች እና በጨረታ ሰነዱ ላይ የተገለፁትን መስፈርቶች ተጠቅሞ ዝርዝር ግምገማ ማድረግ አለበት፡፡ በጨረታ ሠነዱ ውስጥ ከተገለጸው መስፈርት ውጭ ግምገማ ማድረግ አይፈቀድም፡፡ በጨረታ ሰነዱ በሚገለጸው መሠረት መ/ቤቱ አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ ከሚከተሉት የግምገማ ስርዓቶች በአንዱ መጠቀም ይኖርበታል:-

ሀ/ በአንድ ኤንቬሎፕ የቀረበን ጨረታ የቴክኒክ ግምገማ መመዘኛዎችን ማሟላቱ የተረጋገጠ እና አነስተኛ ዋጋ ያቀረበን ተጫራች፣ ወይም

ለ/ በሁለት ኤንቬሎፕ የቀረበን ጨረታ የግዥውን የጠቀሜታ እሴት የሚወስኑ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ በሚካሄድ የቴክኒክና የፋይናንስ አጠቃላይ ግምገማ ድምር ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘውን ተጫራች በመምረጥ ይሆናል፡፡

43.፪.፪ ዝርዝር ግምገማ በሚደረግበት ወቅት ተጫራቾች የሰጡት በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የዋጋ ቅናሽ ታሳቢ ይደረጋል፡፡

43.፪.፫ እንደአስፈላጊነቱ የተመረጠው ተጫራች ህጋዊነት፣ የፋይናንስና የቴክኒክ አቋም በመጫረቻ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሰረት መሆኑ በድሕረ ግምገማ ሊረጋገጥ ይችላል፡፡

43.፪.፬ ግዥው በዓለም አቀፍ የጨረታ ዘዴ የሚፈፀም ሆኖ ለግምገማ ዓላማ ሲባል በተለየ ሁኔታ እንዲቀርብ በጨረታ ሠነዱ ካልተገለጸ በስተቀር በተጫራቾች የሚቀርበው ዋጋና የሚካሄደው የጨረታ ግምገማ ታክስን ማካተት ይኖርበታል፡፡

43.፪.፫ በግምገማ ወቅት ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ተጫራቾች እኩል ነጥብ ቢያገኙ በአዋጁ አንቀጽ ፭፬÷፫÷ መሰረት ለሀገር ውስጥ ምርት ወይም አገልግሎት ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

43.2.6 በንዑስ አንቀፅ 43.2.5 ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ እኩል ነጥብ ያመጡ ወይም እኩል ተመራጭ የሆኑ ተጫራቾች በሚኖሩበት ጊዜ አሸናፊውን ለመለየት መ/ቤቱ እኩል የወጡት ተጫራቾች በተወሰኑ መስፈርቶች ላይ የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳባቸውን እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል፤ ይህንንም ተፈፃሚ ለማድረግ:-

ሀ/ እኩል የሚወጡ ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸው መስፈርቶች ቁጥር ከሦስት ያልበለጠ እና በአኃዝ ሊገለፅ የሚችል መሆን ይኖርበታል፣

ለ/ መስፈርቶቹ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተለይ በጨረታ ዝርዝር መግለጫው ላይ መገለፅ ይኖርባቸዋል፣

ሐ/ እኩል የወጡት ተጫራቾች እኩል መሆናቸው ሲረጋገጥ ይኸው ተገልፆላቸው መጀመሪያ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለፁት መስፈርቶች መሠረት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፣

መ/ እኩል የወጡት ተጫራቾች ያቀረቡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሀሣብ እስከተቻለ ድረስ እኩል የወጡት ተጫራቾች በተገኙበት ተከፍቶ የሰጡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳብ እንዲነበብላቸው ይደረጋል፣

ሠ/ እኩል የወጡት ተጫራቾች ያቀረቡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሀሣብ ተገምግሞ የተሻለ ሐሳብ ያቀረበው ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ተደርጎ ይመረጣል፣

ረ/ በንዑስ አንቀፅ ፬፫.፪.፮ ፊደል ተራ "ሠ" የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ እኩል የወጡት ተጫራቾች የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳብ ባለማቅረባቸው ወይም ባቀረቡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳብ መሰረት በተደረገ ግምገማ በድጋሚ እኩል ቢሆኑ እስከተቻለ ድረስ እኩል የሆኑት ተጫራቾች በተገኙበት አሸናፊው ተጫራች በእጣ እንዲለይ ይደረጋል፡፡

፬፫.፪.፯ የመንግስት መ/ቤቱ የጨረታውን አሸናፊ በሚመርጥበት ጊዜ መለኪያው ተለይቶ የሚታወቅ እስከሆነ ድረስ በእያንዳንዱ የዕቃ ወይም አገልግሎት መለኪያ የተሰጠውን የነጠላ ዋጋ ወይም ሌሎች የውል ቃሎች እና

ሁኔታዎችን ሳይለውጥ እንደአስፈላጊነቱ የዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን ብዛት (መጠን) እስከ 20% (ሃያ በመቶ) ድረስ ሊቀንስ ወይም ሊጨምር የሚችል ስለመሆኑ በጨረታ ሰነዱ ላይ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

፬፫.፪.፰ የመንግስት መ/ቤቶች የማናቸውም ጨረታ ግምገማ በተጫራቾች የተሰጠው የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የመጨረሻ ቀን ከማለፉ በፊት ግምገማውን በማጠናቀቅ ውጤቱን ለተጫራቾች መግለጽ አለባቸው፡፡ ሆኖም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ግምገማውን በጊዜው ማጠናቀቅ ካልቻሉ ተጫራቾች ዋጋው ፀንቶ የሚቆይበትን የጊዜ ገደብ እንዲያሻሽሉ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 35 በን/አንቀጽ ፬ መሠረት መጠየቅ ይገባቸዋል፡፡

፬፫.፪.፱ ጨረታውን ያወጣው የመንግስት መሥሪያ ቤት የቀረበው አንድ ተጫራች ያቀረበው የመወዳደሪያ ሃሳብ አጥጋቢ እና ዋጋውም ተወዳዳሪ የገበያ ዋጋ መሆኑን እንዲሁም የሌሎች ተወዳዳሪዎችን ተሳትፎ የሚገድቡ ምክንያቶች በጨረታ ሰነድ ላይ ያለመኖራቸውን ካረጋገጠ ድጋሚ ጨረታ ማውጣት ሳያስፈልግ የቀረበውን አንድ ተጫራች አሸናፊ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 43.3. ልዩ አስተያየት

43.3.፩ በፕሮፎርማና ከአንድ አቅራቢ ከሚፈጸም ግዥ በስተቀር በማናቸውም ግዥ ላይ በአዋጁ አንቀጽ ፩፬ መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ ለተመረቱ ዕቃዎች፣ በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት አዋጅ መሠረት ለተቋቋሙ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት፣ በኢትዮጵያ ኩባንያዎች ለሚከናወኑ የግንባታ ዘርፍ እና የምክር አገልግሎት ሥራዎች ልዩ አስተያየት ይደረጋል፡፡

43.፫÷፪÷ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ 43.3.፩ መሰረት የሚደረገው ልዩ አስተያየት በዋጋ ላይ በሚደረግ ውድድር ወቅት በሚከተለው መሠረት ተፈጻሚ መደረግ አለበት፡፡ ይኸውም:-

ሀ/ ለመድሐኒት እና የህክምና መሣሪያዎች ግዥ ፪፭% በመቶ (ሃያ አምስት በመቶ)

ለ/ ለሌሎች ዕቃዎች ግዥ ፩፭% በመቶ (አሥራ አምስት በመቶ)

ሐ/ ለግንባታ ሥራና ለምክር አገልግሎት ግዥዎች ፯.፭% (ሰባት ነጥብ አምስት በመቶ)

43.3.፫ በንዑስ አንቀፅ ፬፫÷፫÷፬÷ (ሀ እና ለ) መሠረት የሚደረገው ልዩ አስተያየት መድኃኒቱን ወይም የህክምና መሣሪያውን ወይም ዕቃውን ለማምረት ከወጣው ጠቅላላ ወጪ ፫፭% (ሰላሳ አምስት በመቶ) እና ከዚህ በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የታከለ እሴት መሆኑን የሚያስረዳ በተመሰከረለት ኦዲተር የተረጋገጠ ማስረጃ ሲቀርብ ይሆናል። ለዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈፃፀም '' የታከለ ዋጋ'' ማለት፣ ከጠቅላላ ወጪ ላይ ከውጭ አገር ለሚመጡ ጥሬ ዕቃዎች እና ሌሎች አቅርቦቶች እንዲሁም ከውጭ አገር ለተገኘ አገልግሎት የተደረገ ወጪ ተቀንሶ የሚቀረው ወጪ ሲሆን፣ በምርት ላይ የሚከፈሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን አይጨምርም።

43.3.፬÷ ማናቸውም የግንባታ ዘርፍ ወይም የምክር አገልግሎት ሥራ በንዑስ አንቀጽ 43.2.፬(ሐ) መሠረት የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች በሙሉ ሲሟሉ ይሆናል:-

ሀ/ ኩባንያው በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመ እና ዋና መ/ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣

ለ/ ከኩባንያው አክሲዮን ወይም የካፒታል ድርሻ ከ፭፲% (ሃምሳ በመቶ) በላይ በኢትዮጵያውያን የተያዘ ከሆነ፣

ሐ/ ከኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል ከ፭፲% (ሃምሳ በመቶ) በላይ ኢትዮጵያውያን ከሆኑ፣

መ/ ከኩባንያው ቁልፍ ሠራተኞች መካከል ቢያንስ ፭፲% (ሃምሳ በመቶ) ኢትዮጵያውያን ከሆኑ፣

43.3.፭ በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት አዋጅ መሠረት የተቋቋሙ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት:-

ሀ/ ከአገር ውስጥ አቅራቢዎች ጋር በሚያደርጉት ውድድር 3% ( ሦስት ከመቶ) ልዩ አስተያየት ይደረግላቸዋል።

ለ/ ግዥው በዓለም አቀፍ የግዥ ዘዴ የሚፈጸም ሲሆን በንዑስ አንቀጽ 43.3.2 ሀ፣ ለ እና ሐ ላይ የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ብቻ ተፈጻሚ ይደረጋል::

ሐ/ በጨረታ ማስከበሪያ፣ በውል ማስከበሪያ እና በቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ምትክ ተቋማቱን ካደራጃቸው አካል የሚሰጥ የዋስትና ደብዳቤ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

መ/ ለጨረታው የተዘጋጀው የጨረታ ሠነድ በአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋምነት የተቋቋሙበትን የሕጋዊነት ማስረጃ በማሳየት ያለክፍያ በነጻ ይሠጣቸዋል፡፡

ሠ/ በኮንስትራክሽን ዘርፍ በአጠቃላይ ተቋራጭነት፣ በህንፃ ግንባታና በመንገድ ሥራ ተቋራጭነት ከደረጃ 7 እስከ ደረጃ 10 የሙያ ፍቃድ ያላቸው ተቋራጮች በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ውስጥ የተመደቡ በመሆናቸው የአስተዳደሩ የመንግስት ተቋማት በደረጃቸው በሚከናወኑ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ላይ በአስተዳደሩ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው የደረጃ አድገት ለተሰጣቸው የግልና የንግድ ማህበር ተቋራጮችን ብቻ እንዲወዳደሩ ይህ የልዩ አስተያየት መብት ተሰቷቸዋል፡፡

ረ/ የእንጨትና ብረታ ብረት ሥራ ያለው የመንግስት ተቋም በአስተዳደሩ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ለተደራጁ የደረጃ አድገት ለተሰጣቸው የግልና የንግድ ማህበር አንቀሳቃሾችን እስከ ብር 1,500,000 ያሉ ሥራዎችን በማወዳደር ግዥ ይፈፀማል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ኢንተርፕራይዙ እስከ ብር 5,000,000 ብር እስከሚሞላ ድረስ ይህንኑ ማበረታቻ በመጠቀም ከተመሳሳይ ኢንተርፕራይዞች ጋር መወዳደር ይችላል፡፡ ኢንተርፕራይዙ በዚህ አንቀጽ እስከተጠቀሰው የብር መጠን ድረሰ ብቻ የዚህ ልዩ የማበረታቻ መብት ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ አጠ ቃላይ የሸነፈው ጨረታ ከ5 ሚሊየን ብር በላይ ሲሆን በንዑስ አንቀጽ ፵፫÷፫÷፯ በፊደል ሀ፣ ላይ የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ብቻ ተፈጻሚ ይደረጋል::

ሰ/ ይህ ደንብ የማይመለከተው የኮንስትራክሽን የሥራ ተቋራጭ በሚወዳደርበት የኮንስትራክሽን ጨረታ ላይ ከጨረታው ጠቅላላ ዋጋ ከ30 በመቶ የማያነሰው ዋጋ ያለውን ሥራ በሰብ ኮንትራክተርነት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በመስጠት የሚያሰራ ከሆነ የ3 በመቶ ልዩ አስተያየት ይደረግለታል፡፡ አፈፃፀሙም በጨረታ ሰነዱ መገምገሚያ መስፈርት ወስጥ የሚጠቀስ ይሆናል፡፡

ሸ/ የደንብ ልብስ፣ ጫማ እና አልባሳት ለመግዛት የሚፈልግ የመንግስት ተቋም እስከ ብር 500,000 የሚሆን ግዥውን ይህንኑ ምርት

ከሚያዘጋጁ ወይም እሴት በመጨመር ከሚያቀርቡ በአስተዳደሩ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ለተደራጁ እና የደረጃ አድገት ለተሰጣቸው የግልና የንግድ ማህበር አንቀሳቃሾች ግዥውን ይፈፅማል፡፡

ቀ/ ምግብና ምግብ ነክ ምርቶችን ለመግዛት የሚፈልግ የመንግስት ተቋም እስከ ብር 500,000 የሚሆን ግዥውን ይህንኑ ምርት ከሚያዘጋጁ ወይም እሴት በመጨመር ከሚያቀርቡ በአስተዳደሩ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ለተደራጁ እና የደረጃ አድገት ለተሰጣቸው የግልና የንግድ ማህበር አንቀሳቃሾች ግዥውን ይፈፅማል፡፡

43.4. <u>ድጋሚ ጨረታ ስለማውጣት</u>

ድጋሚ ጨረታ ማውጣት የሚያስፈልገው:-

ሀ/ በአሸናፊው ተጫራች የቀረበው ዋጋ ጨረታው ከመውጣቱ በፊት በመንግስት መ/ቤቱ ከተገመተው ዋጋ ጋር ሲነፃፀር በከፍተኛ ልዩነት የሚበልጥ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ባለመሆኑ አዲስ ጨረታ ማውጣት የሚሻል መሆኑ ሲታመንበት ወይም፣

ለ/ የቀረበው አንድ ተጫራች ብቻ ሲሆንና ይህን ተጫራች በብቸኝነት እንዲቀርብ ያስቻለው በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ የተዘረጉትን ሥርዓቶች ያልጠበቀ አሠራር (ሁኔታ) በመኖሩ ምክንያት መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም በጨረታ ሰነዱ ላይ ለውጥ በማድረግ በርካታ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ማግኘት የሚቻል መሆኑ ሲታመን፣

፵፫፥፭፥ ከጨረታ ውጪ ማድረግ፣

ከሚከተሉት ጥፋቶች ውስጥ አንዱን የፈፀመን ተጫራች የመንግስት መ/ቤቱ ከጨረታው ውጪ ሊያደርገው ይችላል:-

ሀ/ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የንግድ ግንኙነቶች ላለማድረግ ክልከላ ከጣለበት አገር የሚመጣ ዕቃና አገልግሎት ከሆነ፣ ወይም፣

ለ/ በተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት ውሳኔ ከዚያ አገር ዕቃዎችንና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ማስመጣት ወይም ለዚያ ሀገር ሰዎች ወይም ድርጅቶች ማንኛውንም ክፍያ መፈፀም የተከለከለ ከሆነ፣

ሐ/ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደርን አዋጅ እና ይህን መመሪያ የሚጥሱ ድርጊቶችን መፈፀሙ የተረጋገጠ እንደሆነ፣ ወይም

መ/ ቀደም ሲል በወጡ ጨረታዎች የገባውን የግዥ ውል ግዴታ ባለማክበሩ በመንግስት ጨረታዎች እንዳይሳተፍ በኤጀንሲው የታገደ ከሆነ፣ ወይም

ሠ/ የተለየ አስተያየትን ለማግኘት ወይም ጨረታውን ለማሸነፍ ለማናቸውም ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ መደለያ መስጠቱ ወይም የመደለያ ሀሳብ ማቅረቡ ሲረጋገጥ፣ ወይም

ረ/ ተወዳዳሪው በጨረታው ሰነድ ላይ የማጭበርበር ተግባር መፈፀሙ፣ ወይም ከሌላ ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር መመሳጠሩ ሲረጋገጥ፣

43.6. **ጨረታን ማፅደቅ**

43.6.፩. በመንግስት መ/ቤቶች የጨረታ ግምገማውን የሚያከናውነው የግዥ የሥራ ክፍል ወይም እንደአስፈላጊነቱ ጨረታ ለመገምገም የተቋቋመው ጊዜያዊ ቡድን በተጫራቾች የተሠጠው የጨረታ ዋጋ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ግምገማውን በማጠናቀቅ ውጤቱን ከአስተያየት ጋር ግዥውን ለማፅደቅ ስልጣን ለተሠጠው አካል ማቅረብ አለበት::

43.6.፪፥ በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሠረት ግዥውን እንዲያፀድቅ ሥልጣን የተሰጠው አካል ግዥው የመንግሥት ግዥ አፈጻጸም ሥርዓትን የተከተለ እና የጨረታ ግምገማው በጨረታ ሠነዱ በተገለጸው መሥፈርት መሠረት መሆኑን በማረጋገጥ ውሳኔ ይሰጣል:: ውሳኔውም ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል:-

ሀ/ የግምገማ ሪፖርቱን ሙሉ በሙሉ በመቀበል ቀጣይ አፈጻጸሞች እንዲከናወኑ መፍቀድ፣

ለ/ ሪፖርቱን ባለመቀበል ግምገማው እንደገና እንዲከናወን ማድረግ፣

43.6.፫ ግዥውን የሚያፀድቀው አካል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቀረበው የግምገማ ሪፖርት ላይ ግምገማውን የሰራው ቡድን ማብራሪያ እንዲሰጠው ሊያደርግ ይችላል::

43.6.፬ በንዑስ አንቀጽ ፴፫፥፮.፪ /ለ/ ላይ በተገለጸው መሰረት ግዥውን የሚያፀድቀው አካል የቀረበውን የግምገማ የውሳኔ ሃሳብ ያልተቀበለ ከሆነ ምክንያቱን በመግለጽ ከዚህ በፊት ግምገማውን ላከናወነው ቡድን እንዲመለስ የሚያደርግ ሲሆን

ገምጋሚ ቡድኑም ከአፅዳቂው አካል በተሠጠው አቅጣጫ መሠረት ግምገማውን እንደገና አከናውኖ የተስተካከለውን ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል::

43.6.፫ በዚህ አንቀጽ ን/አንቀጽ 43.6.፬ ላይ የተመለከተው ቢኖርም ገምጋሚ ቡድኑ ወይም ማንኛውም የጨረታ ገምጋሚ ቡድን አባል የግዥ አፅዳቂ አካሉ በሰጠው አቅጣጫ ወይም በግምገማ ውጤት ላይ የማይስማማ ከሆነ በግምገማ ሪፖርቱ ላይ ያልተስማማበት ሀሣብ ተገልፆ የግዥ አፅዳቂ አካሉ በሰጠው ውሳኔ መሰረት ግዥው እንዲፈፀም ይደረጋል::

43.7. **የጨረታ አሸናፊን ማሳወቅ**

43.7.፩÷ የመንግስት መ/ቤቶች የጨረታውን ውጤት በጨረታው ተሳታፊ ለሆኑት ተጫራቾች በሙሉ በእኩል ጊዜ በጽሑፍ መግለጽ አለባቸው:: ለተሸነፉ ተጫራቾች የሚገለፀው የተሸነፉበት ምክንያት እና አሸናፊ የሆነው ተጫራች ማንነት መሆን አለበት::

43.7.፪÷ በጨረታው አሸናፊ ለሆነው ተጫራች የሚላከው ደብዳቤ በመንግስት መሥሪያ ቤቱ እና በተጫራቹ መካከል እንደውል ሆኖ ሊያገለግል አይችልም:: በመንግስት መሥሪያ ቤቱ እና በተጫራቹ መካከል ውል እንደተፈፀመ የሚቆጠረው ዝርዝር ጉዳዮችን ያካተተ ውል በመ/ቤቱ ኃላፊና በተጫራቹ ሲፈረም ብቻ ነው::

43.7.፫ ለተጫራቹ ውል እንዲፈርም የሚላክለት ማስታወቂያ የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት

ሀ/ የመንግስት መ/ቤቱ በተጫራቹ የቀረበውን የመጫረቻ ሐሳብ የተቀበለ መሆኑን፣

ለ/ ውሉ የሚፈጸምበትን ጠቅላላ ዋጋ፣

ሐ/ ተጫራቹ ማስያዝ የሚገባውን የውል ማስከበሪያ መጠን እና የማስረከቢያውን የመጨረሻ ቀን፣

43.7.፬ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ተጫራች ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆነ የመንግስት መ/ቤቱ በቅድሚያ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ በመገምገም በውድድሩ ሁለተኛ የወጣውን ተጫራች አሸናፊ ማድረግ ወይም አዲስ ጨረታ ማውጣት ይችላል::

43.7.፰ የመንግስት መ/ቤቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ ተወዳዳሪዎች ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ተመላሽ ማድረግ አለበት፡፡

ሀ/ ከአሸናፊ ተጫራቹ ጋር ውል ፈርሞ ተጫራቹ የውል ማስከበሪያ ዋስትና ያቀረበ ከሆነ፣

ለ/ የተሸናፊ ተጫራች ወይም የጨረታ ማስከበሪያውን የመጠቀሚያ ጊዜ ለማራዘም ፈቃደኛ ያልሆነ ተጫራች የጨረታ ማስከበሪያ ፀንቶ መቆያ ጊዜ ያበቃ ከሆነ፣

43.8. <u>የውል ማስከበሪያ</u>

43.8.1 በዋጋ ማቅረቢያ ከሚፈፀም ግዥ እና ከኪራይ አገልግሎት ግዥ በስተቀር ለማናቸውም ሌላ የግዥ ውል የመንግስት መ/ቤቱ የውል ማስከበሪያ መቀበል አለበት፡፡

43.8.2 የጨረታው አሸናፊ ከመ/ቤቱ ጋር ውል ከፈረመበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ለጨረታ ማስከበሪያ ተቀባይነት እንዳላቸው በአንቀጽ 36 በንዑስ አንቀጽ ፬ በተገለፁት የዋስትና ዓይነቶች መሠረት ክፍያ በሚፈፀምበት የገንዘብ ዓይነት ቢያንስ የውሉን ዋጋ 1፲% (አስር በመቶ) በውል ማስከበሪያነት ለመንግስት መስሪያ ቤቱ ማስያዝ አለበት፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ በጨረታው ተጫራቹ ያስገባው ዋጋ በጨረታው ከተገመተው ዋጋ በታች ከሆነ የዋጋ ቅናሹ በቀነሰበት ልክ በመቶኛ ተሰልቶ ይህንን መጠን ከሚያስይዘው የ10 በመቶ ተጨማሪ በማከል የውል የዋስትና መጠን ማስያዝ አለበት፡፡

43.8.3 የመንግስት መ/ቤቱ አቅራቢው በውሉ መሠረት አለመፈፀሙን ሲያረጋገጥ በንዑስ አንቀፅ 45.8.፪ መሠረት አቅራቢው ያስያዘውን የውል ማስከበሪያ ሙሉ በሙሉ መውረስ ይኖርበታል፡፡

43.8.4 በንዑስ አንቀጽ 45.8.፫ የተገለጸው ቢኖርም በአቅራቢው ያልተሟላው የውል ግዴታ በመ/ቤቱ ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ወይም ተጨማሪ ወጪ እንደማያስከትል እና በአቅራቢው ቸልተኝነት ምክንያት የተፈፀመ አለመሆኑ

በመ/ቤቱ የግዥ አጽዳቂ አካል ሲታመንበት የውል ማስከበሪያው ለአቅራቢው ሊመልስለት ይችላል::

43.8.5 የመንግስት መ/ቤቱ በዚህ ንዑስ አንቀፅ 45.8.፬ መሰረት ለወሰዳቸው እርምጃዎች የተሟላ ሰነድ በመያዝ በኤጀንሲው ወይንም በሌላ ጉዳዩ በሚመለከተው ሕጋዊ አካል ሲጠየቅ ማቅረብ እና የአሰራሩን አግባብነት ማስረዳት ይኖርበታል::

43.8.6 በንዑስ አንቀጽ 45.8.2 የተመለከተው ቢኖርም:-

ሀ/ ከአገር ውስጥ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ተቋራጮች ወይም መድሐኒት እና የህክምና መሣሪያዎች አምራች ድርጅቶች ለሚፈጸም ግዥ ከታወቀ የመድን ድርጅት የሚቀርብ በሁኔታ ላይ የተመሠረተ የውል ማስከበሪያ ተቀባይነት ይኖረዋል፣

ለ/ የምክር አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይ የተሠማሩ አማካሪዎች በሚሰጡት የምክር አገልግሎት ሂደት ውስጥ በመ/ቤቱ ላይ ጉዳት ሊደርስ ይችላል ተብሎ ሲገመት የባለሙያ የካሣ መድን እንዲያቀርቡ መጠየቅ ይቻላል፣

ሐ/ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 43.3.5 (ሐ) በተገለጸው መሠረት በውል ማስከበሪያ ምትክ ካቋቋማቸው አካል የሚሠጣቸውን የዋስትና ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣

መ/ የመድን አገልግሎት ግዥ ለመፈፀም በወጣ ጨረታ አሸናፊ የሚሆኑ የመድን ድርጅቶች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለመጠባበቂያ ያስቀመጡትን ገንዘብ በውል ማስከበሪያነት ለመጠቀም ይችላሉ:: ሆኖም በዚህ መንገድ ለሚያስይዙት ዋስትና በቂ መጠባበቂያ ያላቸው ስለመሆኑ ከባንኩ ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣

43.8.፯ በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የተያዘው የውል ማስከበሪያ አቅራቢው የውል ግዴታውን ሙሉ በሙሉ እንዳጠናቀቀ መመለስ ይኖርበታል::

## 43.9 <u>የቅድሚያ ክፍያ</u>

43.9.1. በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እንደአስፈላጊነቱ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ እስከ 30% (ሠላሣ በመቶ) የሚደርስ የቅድሚያ ክፍያ ሊሰጥ ይችላል፡፡ የሚሰጠው የቅድሚያ ክፍያ መጠንም በተጫራቾች መመሪያ ላይ መገለፅ ይኖርበታል፡፡

43.9.፪ አቅራቢዎች በውሉ መሠረት ከሚጠይቁት የቅድሚያ ክፍያ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና እንደአቅራቢው ምርጫ ከታወቀ ባንክ የሚሰጥ የተረጋገጠ ቼክ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

43.9.3 በንዑስ አንቀጽ 46.9.2 ላይ የተመለከተው ቢኖርም የአገር ውስጥ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች እና የመድሀኒት እና ሕክምና መሳሪያዎች አምራች ኢንዱስትሪዎች በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ከታወቀ የመድን ድርጅት ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

43.9.4 በንዑስ አንቀፅ 43.3.5(ሐ) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ለአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ለሚሰጠው የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና መ/ቤቱ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው በጋራ በሚንቀሳቀስ የባንክ ሒሳብ ገንዘቡን ተቀማጭ በማድረግ ከውሉ ጋር ለተገናኙ እና አስፈላጊ ለሆኑ ወጪዎች በጋራ ፊርማ እንዲከፈል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

43.9.5 በንዑስ አንቀጽ 46.9.3 እና 46.9.4 መሰረት ለግንባታ ዘርፍ ሥራ በተደረገ ውል መሰረት ለሚፈፀም የቅድሚያ ክፍያ የቀረበው ዋስትና የመድን ድርጅት ሲሆን ወይም በንዑስ አንቀጽ 46.9.4 መሰረት ለአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋማት የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ከሆነ ውል ሰጪው የመንግሥት መ/ቤት ውል ተቀባይ ከሆነው ሥራ ተቋራጭ ወይም አነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋም ጋር የቅድሚያ ክፍያውን አጠቃቀም በሚመለከት የተለየ ውል መዋዋል አለበት፡፡ ውሉም የሚከተሉትን ያካተተ መሆን ይናርበታል፡፡

ሀ/ በውሉ መሠረት ለሥራ ተቋራጩ ወይም ለአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋሙ የሚፈፀመው የቅድሚያ ክፍያ ለዚሁ ዓላማ በሥራ ተቋራጩ

ወይም በአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋሙ ስም በሚከፈት የተለየ የባንክ ሂሣብ ውስጥ እንደሚቀመጥ፣

ለ/ ከላይ በፊደል ተራ "ሀ" መሠረት በተከፈተው ሂሣብ ውስጥ የተቀመጠው የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ወጪ ሊደረግ የሚችለው በውል ሰጪ እና በውል ተቀባዩ የጣምራ ፊርማ እንደሚሆን፣

ሐ/ በባንክ ሂሣቡ ከተቀመጠው ገንዘብ ላይ ለሥራ ተቋራጩ ወይም ለአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋሙ ክፍያ የሚፈፀመው ቀደም ሲል በወሰደው ገንዘብ ተገቢውን ሥራ የሠራ መሆኑ ሲረጋገጥ መሆኑን፣

መ/ በቅድሚያ ክፍያ መልክ ከሚከፈለው ገንዘብ ውስጥ ለመንገድ ሥራ የአገር ውስጥ ተቋራጮች እስከ 50% (ሃምሳ በመቶ) እንዲሁም ለሕንጻ ሥራ የአገር ውስጥ ተቋራጮች እስከ 30% (ሰላሳ በመቶ) ለመሣሪያ መግዣ ማዋል የሚችሉ መሆኑን፣ የሚገልጹ አንቀጾችን ሊይዝ ይችላል።

43.9.6 በንዑስ አንቀጽ 46.9.5 (መ) በተመለከተው መሠረት መሥሪያ ቤቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲረዳ የሥራ ተቋራጮች በቅድሚያ ክፍያ መልክ ከተሰጣቸው ገንዘብ ውስጥ ከፊሉን ለመሣሪያ መግዣ እንዲያውሉ ሊፈቅድ ይችላል:-

ሀ/ የሥራ ተቋራጩ በቅድሚያ ክፍያ መልክ በወሰደው ገንዘብ የገዛውን መሣሪያ በውሉ መሠረት ፕሮጀክቱ ከመጠናቀቁ በፊት ለዕዳ መያዣነት የማያውል እና በማናቸውም መልክ ለሦስተኛ ወገን የማያስተላልፍ ለመሆኑ ማረጋገጫ ካቀረበ፣

ለ/ የሥራ ተቋራጩ የቅድሚያ ክፍያ አከፋፈል ስምምነት ከመፈረሙ በፊት በቅድሚያ ክፍያ መልክ በሚወስደው ገንዘብ የሚገዛቸውን መሣሪያዎች ዓይነት ለአሠሪው መ/ቤት ተቆጣጣሪ መሐንዲስ አቅርቦ መሣሪያዎቹ ለሥራው አስፈላጊ መሆናቸው ከተረጋገጠ፣

ሐ/ መሣሪያዎቹ ከፕሮጀክቱ ባለቤት ፈቃድ ውጪ ከፕሮጀክቱ ወደ ሌላ ቦታ የማይንቀሳቀሱ መሆኑ ከተረጋገጠ ነው።

43.9.፯ በቅድሚያ ክፍያ መልክ በሚከፈል ገንዘብ ለመንገድ ሥራ እንዲሁም ለሕንጻ ግንባታ የሚገዙት ማሽነሪዎች በአባሪ 4 ላይ የተመለከቱት ብቻ ናቸው።

43.9.፰ ተቋራጩ በንዑስ አንቀጽ 46.9.6 በተመለከተው መሠረት በተከፈለው የቅድሚያ ክፍያ የገዛቸውን መሣሪያዎች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ

ፕሮጀክቱ ቦታ ካላጓጓዘ በውሉ መሠረት ሊከፈለው የሚገባው የሚቀጥለው ክፍያ አይፈፀምለትም።

43.9.፱ ተቋራጩ ወይም አነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋሙ የወሰደው የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ በውሉ መሠረት በየደረጃው ከሚዘጋጁት የክፍያ ምስክር ወረቀቶች ወይም በየደረጃው ከሚፈፀሙ አቅርቦቶች ሂሣብ ላይ እየተቀነሰ እንዲመለስ መደረግ አለበት።

፬፫÷፩፲÷ ውል መፈረም

፬፫÷፩፲.፩ ማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት የመደበኛ ጨረታ ሠነዶች አንድ ክፍል የሆነውን አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች እና ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ልዩ የውል ሁኔታዎች የያዘውን የውል ሠነድ ከአቅራቢው ጋር መፈራረም አለበት።

፬፫÷፩፲.፪ በመንግሥት መ/ቤቱ እና በአቅራቢው መካከል ውል ካልተፈረመ በስተቀር የጨረታው አሸናፊ በመገለፁ ብቻ ውል እንደተፈፀመ አይቆጠርም።

፬፫÷፩፲.፫ በአቅራቢው እና በመንግስት መሥሪያ ቤቱ መካከል የሚደረገው ውል የሁለቱን ወገኖች ኃላፊነት በግልፅ ማመልከት ያለበት ሲሆን የሚከተሉትን ጉዳዮች በተጨማሪነት ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡-

ሀ/ በውሉ የሚቀርበው እቃ፣ የግንባታ ዘርፍ ስራ ወይም የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች አይነት፣ ጥራት፣ ብዛት፣ የሚቀርብበት አኳኋን ወይም የማስረከቢያ ጊዜውን፣ የሚከፈለውን አጠቃላይ እና የነጠላ ዋጋ መጠን፣ የአከፋፈል ሁኔታ እና የክፍያ ጊዜውን፣

ለ/ ከሦስተኛ ወገን የሚገኙ አገልግሎቶችን እንደ ትራንስፖርት፣ ኢንሹራንስ፣ ትራንዚት እና የመሳሰሉ ተግባራትን የመከታተል እና የመፈፀም ኃላፊነት የማን እንደሚሆን መጠቀስ ያለበት ሲሆን ኃላፊነቶቹም በተሻለ ብቃት ሊፈፅማቸው በሚችል አካል እንዲሰሩ መደረግ ይኖርበታል፣

ሐ/ አቅራቢው በመጫረቻ ሠነዱ ላይ ያመለከተው የዋጋ ቅናሽ ወይም ሌሎች ሁኔታዎችን እና አፈጻጸማቸውን በግልጽ ያመላከተ መሆን አለበት፣

መ/ በውል አፈፃፀም ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱበትን አካሄድ፣

ሠ/ የውጭ አገር ተጫራች ከጠቅላላው የውሉ መጠን ውስጥ በውጭ አገር ገንዘብ እና በብር ሊከፈለው የሚገባው የገንዘብ መጠን ድርሻ ተለይቶ መገለጽ ይኖርበታል፣

ረ/ የውል አካል የሆኑ የግዥ ሰነዶች እና የተፈፃሚነት ቅድመ ወሰን፣

ሰ/ ለውል አፈጻጸም የተያዘው የውል ማስከበሪያ ሊወረስ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች፣

ሸ/ አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቆ ባያስረክብ፣ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደውን እርምጃ፤

፬፫÷፩፲.፬ በንዑስ አንቀፅ ፬፮÷፩፲.፫(ሸ) መሰረት የሚወሰደው እርምጃ በሚከተለው መሰረት መሆን ይኖርበታል:-

ሀ/ አቅራቢው ሳይፈፅም በቀረው የውሉ መጠን ላይ በየቀኑ ፩% ወይም ፩/፩ሺኛ የጉዳት ካሳ እንደሚከፍል፣

ለ/ በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ ከውሉ ዋጋ 1፲% የሚበልጥ መሆን እንደሌለበት፣

ሐ/ የውሉ አፈፃፀም መዘግየት በሥራው እንቅስቃሴ ላይ የበለጠ ችግር የሚያስከትል ከሆነ የመንግስት መ/ቤቱ የመቀጫው መጠን 1፲% እስከሚሞላ ድረስ ለመጠበቅ ሳይገደድ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን መሠረዝ እንደሚችል፣ የሚገልፅ አንቀጽ ውሉ እንዲይዝ መደረግ አለበት::

፬፫÷፩፲.፭ የመንግስት መ/ቤቱ በውል ሰነድ ላይ የሚሰፍሩ ኃላፊነቶችን እና ግዴታዎችን በጥንቃቄ መመርመር ያለበት ሲሆን በመ/ቤቱ ደረጃ ሊከናወኑ የማይችሉ ግዴታዎችን ተቀብሎ ውል መፈረም የለበትም::

፬፫÷፩፲.፮ በንዑስ አንቀጽ ፬፮÷፩፲.፯ ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌላ የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር አሸናፊው ተጫራች ማሸነፉ ከተገለፀለት ቀን ጀምሮ በ፩፭ ቀናት ውስጥ ቀርቦ ውሉን መፈረም ይኖርበታል::

፵፫÷፩፲.፯ ጨረታውን ያወጣው የመንግስት መስሪያቤት የጨረታውን ወይም የቅሬታውን ውጤት ለተጫራቾች ከገለፀበት ቀን ጀምሮ ፯ የሥራ ቀን ከመሙላቱ በፊት የግዥ ውል መፈረም የለበትም፡፡

# ክፍል ፱

## <u>የውል አስተዳደር</u>

### ፵፬. ውልን ተፈፃሚ ማድረግ

፵፬.፩ የመንግስት መ/ቤቶች የተለየ ሁኔታ ካላጋጠማቸው በስተቀር ከአቅራቢዎች ጋር የተደረጉ የውል ስምምነቶች በፍጥነት ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

፵፬.፪ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፵፬.፩ ላይ የተመለከተውን ተግባራዊ ለማድረግ ውሉ የሚያስ ቀምጠው ቅድመ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቱ የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸም ይኖርበታል፡-

ሀ/ ውሉ ቅድሚያ ክፍያ እንዲፈፀም የሚያዝ ከሆነ በዚህ መመሪያ ላይ በተቀመጠ ው መሰረት አቅራቢው የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና እንዲያሲዝ በማድረግ የቅድሚያ ክፍያውን በወቅቱ መፈፀም፣

ለ/ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ሊከፈትላቸው ለሚገባ ግዥዎች ተገቢው ፎርማሊቲ መሟላቱን በማረጋገጥ ሌተር ኦፍ ክሬዲቱን በፍጥነት መክፈት፣

ሐ/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፵፬.፪ ፊደል ተራ "ሀ እና ለ" ከተቀመጡት በተጨማሪ በመሥሪያ ቤቱ ሊፈፀሙ የሚገቡ ተግባራትን በውሉ መሰረት በወቅቱ ማከናወን፡፡

፵፬.፫ የመንግስት መ/ቤቶች ውሉን ተፈፃሚ ለማድረግ በአቅራቢው ሊከናወኑ የሚገባቸውን ተግባራት በመለየት አቅራቢው በውሉ መሰረት ተግባራቱን በወቅቱ መፈፀሙን ተከታትለው ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

፵፬.፬ የመንግስት መ/ቤቶች የውሉ ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው ውሉ ተፈፃሚ መሆን የጀመረበትን ቀን መዝግበው መያዝ እና እንደ አስፈላጊነቱም አቅራቢው እንዲያውቀው ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

፬፬.፫ የመንግስት መ/ቤት የግንባታ ዘርፍ ስራ ግዥ ሲፈፅም ክፍያ የሚፈፀመው የግንባታውን የክንውን ደረጃ መሠረት አድርጎ እና የሚከተለውን አፈፃፀም ተከትሎ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሀ/ ለግንባታ ዘርፍ ስራ ክፍያ የሚፈፀመው የስራውን ደረጃ ተከትሎ ከአማካሪ መሐንዲስ በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት መነሻነት ብቻ ይሆናል፡፡

ለ/ በዚህ መመሪያ በን/አንቀፅ ፴፫÷፱ በን/ን/አንቀጽ 9 ከተመለከተው በተጨማሪ ለማናቸውም የግንባታ ዘርፍ ስራ በክፍያ የምስክር ወረቀት መሠረት ከሚፈፀመው ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ ለግንባታ ሥራው ጥራት ዋስትና እንዲሆን 5% (አምስት በመቶ) በመያዣ መልክ ተቀንሶ ይያዛል፡፡

ሐ/ የግንባታ ስራው ሲጠናቀቅ እና ጊዜያዊ ርክክብ ሲደረግ በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ (ለ) መሠረት ከተያዘው ገንዘብ ላይ 50% (ሃምሳ በመቶ) ለሥራ ተቋራጩ ይለቀቃል፡፡ ቀሪው 50% (ሃምሳ በመቶ) ለአንድ አመት የጥገና ጊዜ ተይዞ ይቆያል፡፡ ሆኖም የሥራ ተቋራጩ ለ፩፪ ወራት የሚቆይ በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተ ዋስትና ካቀረበ የተያዘው ገንዘብ ሊለቀቅለት ይችላል፡፡

መ/ አማካሪ መሐንዲሱ የክፍያ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ከሥራ ተቋራጩ ተዘጋጅቶ በቀረበለት በ7 የሥራ ቀናት ውስጥ የምርመራውን ሥራ ማጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡

ሠ/ የክፍያ የምስክር ወረቀት በአማካሪ መሐንዲሱ ተረጋግጦ በቀረበ በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ መ/ቤቱ ተገቢውን ክፍያ ለሥራ ተቋራጩ መፈፀም አለበት፡፡

ረ/ አማካሪ መሐንዲሱ የክፍያ የምስክር ወረቀት ተዘጋጅቶ ከቀረበለት በኋላ ያለበቂ ምክንያት በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ (መ) ላይ ከተጠቀሰው ጊዜ ያሳለፈ እንደሆነ በመዘግየቱ ምክንያት ተቋራጩ በመ/ቤቱ ላይ ለሚያቀርበው ማንኛውም ተጨማሪ የክፍያ ጥያቄ አማካሪ መሐንዲሱ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ሆኖም የአማካሪ መሐንዲሱ ኃላፊነት ለአገልግሎቱ ከሚከፈለው ዋጋ ሊበልጥ አይችልም፡፡

ሰ/ መ/ቤቱ ያለበቂ ምክንያት በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ (ሠ) ላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በአማካሪ መሐንዲሱ በቀረበለት ማረጋገጫ መሠረት ክፍያ ባይፈፅም ተቋራጩ በውሉ መሰረት ለሚያቀርበው ተጨማሪ የክፍያ ጥያቄ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

## 45. <u>የውል አፈፃፀምን መከታተል</u>

45.1. የመንግስት መ/ቤቶች የውል አፈፃፀምን የሚከታተል አካል መለየት ወይም የውል ክትትል በተለያዩ አካላት በቅንጅት የሚፈፀም በሚሆንበት ወቅት አካላቱ ተግባራቸውን በግልፅ እንዲያውቁ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

45.2፥ የውል አፈፃፀምን የሚከታተለው የመንግስት መ/ቤቱ አካል አቅራቢው በውሉ መሰረት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት በውሉ ላይ በተገለፀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየተከናወኑ የሚገኙ መሆኑን መከታተል ይኖርበታል፡፡

45.3፥ የመንግስት መ/ቤቱ በውል ስምምነቱ መሰረት እንደ አስፈላጊነቱ የሚከተሉትን የውል አስተዳደር ተግባራት ማከናወን ይጠበቅበታል:-

ሀ/ ተከታታይ ክፍያዎችን በወቅቱ መፈፀም፣

ለ/ አቅራቢው የውል ግዴታውን እየተወጣ እንደሚገኝ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በወቅቱ መስጠት፣

ሐ/ አቅራቢው የውል ግዴታውን መወጣት እንዲችል ሕጋዊ የሆነ እገዛ በማድረግ የውሉ አፈፃፀም የተሳካ እንዲሆን ማድረግ ይኖርበታል፡፡

45.4 በውል አፈፃፀም ወቅት እንደሁኔታው የውል ማሻሻያ ማድረግ የሚቻል ሲሆን የሚደረገው የውል ማሻሻያ የመንግስት መ/ቤቱን ጥቅም የሚጎዳ እና በጨረታው ከተወዳደሩ ሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች አንፃር ለአቅራቢው የተለየ ጥቅም የሚሰጥ መሆን የለበትም፡፡

45.5 በውል አፈፃፀም ክትትል ወቅት የመንግስት መ/ቤቶች በተለይ የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም ይኖርባቸዋል:-

ሀ/ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የውል ስምምነቱን ሁኔታዎች ጠብቆ በወቅቱ መክፈት፣

ለ/ ተቀባይነት የሚኖራቸውን የሌተር ኦፍ ክሬዲት ማስተካከያ ጥያቄዎች ተቀብሎ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት፣

ሐ/ ተገቢው አገልግሎት ከመገኘቱ በፊት የውል ማስከበሪያ፣ የሌተር ኦፍ ክሬዲት፣ የዋራንቲ መጠቀሚያ ጊዜዎች እንዳያልፉ ጥንቃቄ እና ክትትል ማድረግ፣

መ/ የግንባታ ስራዎች በተያዘላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ መገንባታቸውን፤ የዕቃ አቅርቦቶች እና አገልግሎቶች በውሉ ጊዜ ውስጥ ለመከናወናቸው ክትትል መደረጉን እና ሪፖርት መቅረቡን፣

ሠ/ ከውል አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ከአቅራቢዎች ምንም ዓይነት የይገባኛል ጥያቄዎች እንዳይፈጠሩ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ

፬፮.፯ የመንግስት መ/ቤት በውል አፈፃፀም ወቅት ከሦስተኛ ወገን የሚገኙ አገልግሎቶችን መለየት እና አገልግሎቶቹ የውል አፈፃፀሙን በሚያግዝ መልኩ መስጠታቸውን ማረጋገጥ አለበት።

## ፬፯. ውል ማጠናቀቅ

፬፯.፩ የመንግስት መ/ቤት ከአቅራቢዎች ጋር የተፈረሙ ውሎችና እና ተያያዥ ጉዳዮች ተገቢውን ዕልባት በወቅቱ አግኝተው ውሉ መጠናቀቁን ማረጋገጥ አለባቸው ለዚህም:-

ሀ/ አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሰረት የሚገባውን የግንባታ ዘርፍ ስራ፣ ዕቃ፣ የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ማቅረቡን፣

ለ/ በውሉ መሰረት የተያዙ ዋስትናዎች፣ ዋራንቲዎች ተገቢው ክትትል የተደረገባቸው እና አስፈላጊ በሆነ ወቅት ውሳኔ የተሰጠባቸው መሆኑን፣

ሐ/ በውሉ መሰረት ለአቅራቢዎች ሊከፈል የሚገባ ክፍያ የተጠናቀቀ መሆኑን፣ ለተከፈሉ ክፍያዎች ሁሉ በውሉ መሰረት አገልግሎት መገኘቱን፣

መ/ ከሶስተኛ ወገን ማለትም ከኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ ከአጓጓዦች፣ ከጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከጉምሩክ አስተላላፊዎች፣ ከባንክ እና ከሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ጋር የተያያዙ የመንግስት መ/ቤቱ ጥቅሞች መከበራቸውን እና የመንግስት መ/ቤቱ ግዴታዎች የተፈጸሙ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፣

፬፯.፪ የመንግሥት መ/ቤቱ ከአቅራቢው እና ከሦስተኛ ወገን ጋር ያሉ ያልተጠናቀቁ ሒሳቦችን በመዝጋት እንደአስፈላጊነቱ የውል አፈጻጸም ግምገማ ማድረግ ይኖርበታል።

# ክፍል 10

# የጨረታ ዋጋና የዋጋ ማስተካከያ

47. <u>*የፊ ረታ ዋጋ እና የዋጋ ማስተካከያ*</u>

47.1. **የመንግስት መ/ቤት ከተጫራቾች የሚሰጡ የመጫረቻ ዋጋዎች በሌላ ተጫራች ዋጋ ላይ ያልተመሰረቱ እና በጨረታው እና በውል አፈፃፀሙ ወቅት የማይለዋወጡ ፅኑ ዋጋ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡**

47.2 **በንዑስ አንቀፅ ፬፯.፩ ላይ የተገለፀው ቢኖርም፣ የመንግስት መ/ቤቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲረዳ ለግንባታ ስራዎች ውሉ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት 12 ወራት በኋላ እና በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ ውሉ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት** 3 **ወራት በኋላ ለሚኖር ግዥ የዋጋ ለውጥ ወይም ማስተካከያ ማድረግ እንደሚቻል በጨረታ ሰነዱ ላይ ማመልከት ይኖርበታል:-**

ሀ/ **በውል ስምምነቱ መሰረት የግንባታ ስራውን ለማጠናቀቅ ከ**12 **ወራት እንዲሁም በማዕቀፍ ስምምነት ጊዜ የውል ግዴታውን ለማጠ ናቀቅ ከስድስት ወራት በላይ የሚፈጅ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን፣**

ለ/ **በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸም ግዥ የዋጋ ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስችል መነሻ እና የተለወጠ ወቅታዊ ዋጋ ኤጀንሲው ወይም ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሚሰጥ ሲሆን፣**

ሐ/ **የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግበት በሚመረጠው ስብስብ ላይ ኤጀንሲው ወይም የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የዋጋ ኢንዴክስ ወይም የጠቋሚ ዋጋ መረጃ መስጠት መቻሉ ሲረጋገጥ፣**

መ/ **በንዑስ አንቀጽ** 47.2 (ሐ) **የተገለጸው ቢኖርም ኤጀንሲው ወይም ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ወቅታዊ የዋጋ ኢንዴክስ መረጃ መስጠት ባልቻሉባቸው ስብስቦች ላይ የመንግስት መ/ቤቱ የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ ይገባል ብሎ ሲያምን ለውጥ የሚደረግባቸውን ስብስቦች በያዘው ምድብ ላይ ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስችል**

የዋጋ መረጃ ከታወቀ የአገር ውስጥ አምራች ድርጅት ወይም በውጭ አገር ከሚገኝ ሕጋዊ ተቋም ማግኘት ሲቻል፣

48. <u>ለግንባታ ሥራ ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ፤</u>

በንዑስ አንቀጽ 47.2 የተገለጹት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ከግንባታ ስራ ግዥ ጋር በተያያዘ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ ከዚህ በታች የተገለጹትን አሠራሮች ተከትሎ በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ላይ የተመለከተውን ቀመር በመጠቀም መሰላት ይኖርበታል:-

ሀ/ ለግንባታ ሥራው የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ግብዓቶችና በእያንዳንዱ ዋና ግብዓት ሥር ሊካተቱ የሚችሉ ዕቃዎችን ስብስብ መለየት፣

ለ/ በሥራቸው የተለያዩ ዕቃዎች ስብስቦችን የያዙት ዋና ዋና ግብዓቶች፣ ከግንባታ ሥራው ጠቅላላ ግብዓቶች ውስጥ የሚኖራቸውን ድርሻ በማስላት የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸውን እና የማይደረግባቸውን መወሰን ፣

ሐ/ ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት በሥራ ላይ ያለው የዋጋ ኢንዴክስ/ጠቋሚ አሃዝ በቀመሩ መሠረት የዋጋ ማስተካከያውን ለማስላት በመነሻነት ይወሰዳል፣

መ/ የዋጋ ማስተካከያው ጥያቄ በንዑስ አንቀጽ ፬፯.፪ ላይ የተገለጸውን ድንጋጌ ተከትሎ በሚቀርብበት ወቅት በተለይ ለግንባታ ሥራ ግዥ የዋጋ ልዩነቱ የሚሰላው በሥራ ላይ ያለውን ወቅታዊ የዋጋ ኢንዴክስ/ ጠቋሚ አሃዝን በመጠቀም በቀመሩ መሠረት ይሆናል፣

49. <u>በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ፤</u>

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ ዋጋ ማስተካከያ ሊያደርጉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፡-

ሀ/ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸው ኤጀንሲው ወይም ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ወቅታዊ የዋጋ መረጃ ለሚሰጥባቸው አቅርቦቶች ብቻ መሆን አለበት።

ለ/ በማዕቀፍ ስምምነት መሠረት ተፈፃሚ ለሚሆን ግዥ የሚቀርብ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ መቅረብ የሚኖርበት ስምምነቱ ስራ ላይ ከዋለ ከ3 ወራት በኋላ ሊሆን ይገባል።

ሐ/ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበትን ዕቃ ወይም አገልግሎት አስመልክቶ ጨረታው በተከፈተበት ዕለት የነበረው ኤጀንሲው ወይም የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሚያወጣው ዋጋ እና የማዕቀፍ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበት ጊዜ በኮንትራት ስምምነቱ ላይ መገለፅ አለበት።

መ/ የመንግስት መ/ቤቱ በውሉ ላይ በተገለፀው እና በጨረታው መክፈቻ ዕለት ተፈፃሚ በነበረው እና አሁን ያለውን ወቅታዊ ዋጋ አስመልክቶ በኤጀንሲው ወይም በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በተሰጠው ዋጋ መካከል ያለውን የዋጋ ልዩነት በማስላት ልዩነቱ በአቅራቢው ዋጋ ላይ እንዲጨመር ወይም እንዲቀነስ በማድረግ የሚቀጥለው የዋጋ ማስተካከያ ጊዜ እስከሚደርስ ድረስ የተስተካከለውን ዋጋ ተፈፃሚ ማድረግ አለበት።

ሠ/ አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሠረት ማቅረብ ሲገባው በወቅቱ ላላቀረባቸው እና ዘግይተው ለቀረቡ አቅርቦቶች የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ የሚቻለው አቅርቦቶቹ መቅረብ በነበረባቸው ወቅት በነበረው ዋጋ መሠረት ብቻ ይሆናል።

50. ለምክር አገልግሎት ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ፤

ሀ/ በምክር አገልግሎት ግዥ የውል አፈጻጸም ወቅት የአማካሪው ስህተት ባልሆነ ምክንያት የውል መፈጸሚያ ጊዜው በመራዘሙ ለአማካሪው የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን መ/ቤቱ ሲያምንበት የዋጋ ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል።

ለ/ በንዑስ አንቀጽ ፭፲ (ሀ) የተገለጸው ቢኖርም ለአማካሪዎች የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ ከአሥራ አምስት ከመቶ (፩፭%) ሊበልጥ አይችልም።

51. ለእቃዎች ወይም አቅርቦቶች የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ

መ/ቤቱ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸው ዕቃዎች ወይም አቅርቦቶች ለተካተቱበት ግዥ በሚያዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ላይ የሚከተሉትን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሁኔታዎች በግልጽ ማመልከት ይኖርበታል፦

ሀ/ የዋጋ ማስተካከያውን ተግባራዊ ለማድረግ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር ማቅረብ ያለባቸውን የመረጃ አይነት፣

ለ/ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄው የሚቀርብባቸውን ሁኔታዎች፣ የአቀራረብ ዘዴውን እና ከዋጋ ማስተካከያ ጥያቄው ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ማስረጃዎችን አይነትና መጠን፣

ሐ/ ሌሎች ለዋጋ ማስተካከያው አፈጻጸም ይጠቅማሉ ተብሎ የሚታመንባቸውን መረጃዎች እና ተጫራቾች ሊከተሉት ይገባል የሚላቸውን አሰራሮች፣

52. የመንግስት መ/ቤቱ በጨረታ ግምገማ ወቅት ተጫራቾች ለዋጋ ማስተካከያ ዓላማ የተቀመጠ ትን ቅድመ ሁኔታዎች መቀበላቸውን እና ያቀረቧቸው ማስረጃዎችም ተቀባይነት ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

53.የመንግስት መ/ቤቱ እና በጨረታ ውድድሩ አሸናፊ የሆነው ተጫራች በሚያደርጉት የውል ስምምነት ላይ የሚከተሉት እና ሌሎች ተገቢ ናቸው ተብሎ የታመነባቸው ሁኔታዎች በግልፅ እንዲካተቱ መደረግ ይኖርበታል:-

ሀ/ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግላቸውን ግብዓቶች በመጠቀም የሚመረቱ ዕቃዎችን ወይም አቅርቦቶችን ዝርዝር እና የማስተካከያውን አፈፃፀም፤

ለ/ ለዋጋ ማስተካከያው አፈጻጸም የመንግስት መ/ቤቱ እና አቅራቢው የተስማሙበት የሰነድ አይነት እና ምንጭ፣

ሐ/ ለዋጋ ማስተካከያ የሚቀርበው ማስረጃ በውሉ ላይ በተገለፀው መሠረት መሆን እንዳለበት እና ከሌላ ምንጭ የሚመጣ መረጃ ተቀባይነት እንደማይኖረው፣

መ/ አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሰረት በወቅቱ ስራውን ወይም አቅርቦቱን ማከናወን ባለመቻሉ የሚፈጠር የዋጋ መናር ማስተካከያ የማይደረግበት ስለመሆኑ፣

54. የዋጋ ማስተካከያ ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ውስጥ በማስተካከያው ምክንያት የተፈጠረው ልዩነት ከግንባታ ሥራው ጠቅላላ የውል ዋጋ ፳፭% (ሃያ አምስት ከመቶ) በሚበልጥበት ጊዜ የዋጋ ለውጡን ተቀብሎ ግዥውን መቀጠሉ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑን ተረድቶ ተገቢውን ውሳኔ መወሰን እንዲችል የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ እንዲያውቀው መደረግ ይኖርበታል፡፡

55. የመንግስት መ/ቤቱ የዋጋ ማስተካከያ ለተፈቀደበት ማንኛውም ግዥ ከአቅራቢው የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ባይቀርብም የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብለት የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግባቸው በውል ስምምነቱ በተፈቀዱ ግብአቶች ላይ የዋጋ መቀነስ መኖር አለመኖሩን የማጣራትና የዋጋ ቅናሽ ካለም አስልቶ ከቀረበው የክፍያ ጥያቄ ላይ ከቀነሰ በኋላ መክፈል ይኖርበታል፡፡

# ክፍል ፩፩

## <u>ሌሎች ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

### ፸፮. *<u>መደበኛ ያልሆኑ የግዥ ጥያቄዎችን መመርመር፣</u>*

፸፮.፩ የመንግስት መ/ቤቶች በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን የግዥ አፈጻጸም ስርዓቶች ሊጠብቅ ያልቻለ ወይም መደበኛ ያልሆነ ግዥ መፈፀም የሚችሉት የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲው ማቋቋሚያ አዋጅ በአንቀጽ ፮ በንዑስ አንቀጽ ፫ በተደነገገው መሠረት ለኤጀንሲው ጥያቄያቸውን አቅርበው ሲፈቅድላቸው ብቻ ነው።

፸፮.፪ መ/ቤቶች ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፸፮.፩ በተገለጸው መሠረት ለሚያቀርቡት የልዩ ፈቃድ ጥያቄ የወሰዱት አማራጭ ከወጪ፣ ከጥራት፣ ከጊዜ እና ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮች ጋር በተያየዘ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ያካተተ መግለጫ አግባብ ካላቸው ደጋፊ ሰነዶች ጋር ለኤጀንሲው ማቅረብ አለባቸው።

### ፸፯. <u>የግዥ ሠነዶች</u>

፸፯.፩ መ/ቤቶች በአዋጁ አንቀፅ ፩፪ ላይ የተዘረዘሩትን እና ሌሎች አስፈላጊ ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን የግዥ ሰነዶች ይዘው ማቆየት ይኖርባቸዋል።

፸፯.፪ የግዥ ሰነዶች በአስተዳደሩ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩፻፪፲፲፪ አንቀፅ ፸፸ ላይ በተገለፀው መሰረት በሚወጣው ደንብ ወይም መመሪያ ላይ ለፋይናንስ ሰነዶች የቆይታ ጊዜ ከሚገለፀው እኩል የቆይታ ጊዜ ይኖራቸዋል።

### ፸፰. የአቅራቢዎች ምዝገባ፣

በማንኛውም የመንግሥት ግዥ ለመሳተፍ በአቅራቢነት መመዝገብ ግዴታ ነው።

ሀ/ በመንግሥት ግዥ መሳተፍ የሚፈልጉ አቅራቢዎች በኤጀንሲው ድረ-ገጽ በተለይ ለአቅራቢዎች ምዝገባ በተዘጋጀው ክፍል በቅድሚያ ራሳቸውን መመዝገብ ይኖርባቸዋል፣

ለ/ ከላይ በፊደል ተራ "ሀ" ላይ የተገለጸው ቢኖርም በሪል ስቴት ያልተሠማሩ የቤት አከራዮች በአቅራቢዎች ዝርዝር ባይመዘገቡም ለቤት ኪራይ በወጣ ጨረታ መሳተፍ ይችላሉ፣

፳፱፥ <u>በአቅራቢነት ለመመዝገብ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች:</u>

ሀ/ አቅራቢው የተሠማራበትን የሥራ ዘርፍ የሚገልፅ የታደሰ ንግድ ፈቃድ፣

ለ/ የምክር አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ አቅራቢ ከሆነ ስለተሰማራበት የሙያ ዘርፍ በሚመለከተው አካል የተሰጠ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ፣

ሐ/ በግንባታ ሥራ ላይ የተሰማራ ከሆነ የሥራ ተቋራጭነት ሥራ እንዲሠራ በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የተሠጠውን ደረጃ የሚገልፅ ማስረጃ፣

መ/ የተሽከርካሪ ጥገና አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሠማራ ከሆነ ከፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን የተሠጠ ደረጃውን የሚገልፅ ማስረጃ፣

ሠ/ መድሐኒት እና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎችን በማቅረብ የተሠማራ ከሆነ ከመድሐኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን የተሠጠውን ማስረጃ፣

# ክፍል ፩፪

# የመንግሥት ግዥ ሥነ-ምግባር

## ፺፲. የግዥ ፈፃሚ ባለሙያ ውይም ኃላፊ የሚጠበቅ ሙያዊ ሥነ - ምግባር

በአዋጁ አንቀጽ ፪፩.፩ ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ከመንግሥት ግዥ አፈጻጸም ጋር ግንኙነት ያለው ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ተግባሩን በተሟላ የሙያ ሥነ-ምግባር መፈጸም ይኖርበታል:: ለዚህም የሚከተሉትን እና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ማከናወን አለበት:-

፺፲.፩ በመንግስት ግዥ ሥራ ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተሰማራ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ከሚሰራው ሥራ ጋር በተገናኘ የሚሰጠው ውሳኔ በማንኛውም መልኩ ራሱን

ወይም ቤተሰቡን ሊጠቅም የሚችል መሆኑን ሲረዳ ከሥራው ጋር የተገናኘ የጥቅም ግጭት መኖሩን በጽሑፍ በማሳወቅ ከግዥ ሂደቱ ሥራ ራሱን ማግለል ይኖርበታል፡፡

፷፲.፪ የመንግሥት መ/ቤቱ በመንግሥት ግዥ ሥራ ላይ የተሳተፈ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ከሚሰራው ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት እንዳለው ከማንኛውም ምንጭ መረጃ ሲደርሰው:-

፷፲.፪.፩ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው በቀረበው የጥቅም ግጭት ጉዳይ ላይ አስተያየቱን በጽሑፍ እንዲሰጥ ያደርጋል፣

፷፲.፪.፪ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፷፲.፪.፩ በተሰጠው የጽሑፍ አስተያየት እና ተገቢ ነው ብሎ ባመነባቸው መንገዶች ተጨማሪ መረጃ በማሰባሰብ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው ከያዘው የግዥ ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት እንዳለው ወይም እንደሌለው ይወስናል፣

፷፲.፪.፫ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፷፲.፪.፪ ላይ በተቀመጠው መሠረት የመንግሥት መ/ቤቱ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው ከሚሰራው የግዥ ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት መኖሩን ሲያረጋግጥ:-

ሀ/ ሠራተኛውን ወይም ኃላፊውን ከሂደቱ እንዲገለል ያደርጋል፡፡

ለ/ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው በሂደቱ ተሳትፎባቸው ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች እንደገና እንዲታዩ ያደርጋል፡፡

ሐ/ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው የጥቅም ግጭቱን ያላሳወቀው ከግንዛቤ ጉድለት ነው ብሎ ካላመነ በስተቀር በሠራተኛው ወይም በኃላፊው ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

፷፲.፫ በመንግሥት ግዥ ሥራ ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚሳተፍ ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም አቅራቢዎች እኩል የመወዳደርና ውል የመፈፀም ዕድል እንዳያገኙ የሚያደርግ ማንኛውንም ተግባር መፈፀም የለበትም፡፡

ለዚህም፡፡

ሀ/ በጨረታ ጥሪ ሁሉም ዕጩ ተወዳዳሪዎች በቂ መረጃ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በጨረታው ለመሳተፍ እና ተመራጭነት ሊያገኝ የሚችል የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት የሚያስችል የተሟላ እና ግልፅ መረጃ መያዙን ማረጋገጥ፣

ለ/ በጨረታ ሰነዱ የተገለጸው ማንኛውም የመወዳደሪያ መስፈርትም ሆነ የፍላጎት መግለጫ ዝርዝር የተወሰነ ዕጩ ተወዳዳሪን ሊጠቅም በሚችል መልኩ አለመዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣

ሐ/ የጨረታው ውጤት ለሁሉም ተሳታፊዎች በእኩል ጊዜ መገለጹን ማረጋገጥ፣

መ/ በውል ሰነድ ዝግጅት ለአቅራቢዎች የሚሰጠው ኃላፊነት ግዴታቸውን ሆነ ብሎ ለማቅለል ወይም ለማክበድ ያላለመ እና እስከተቻለ ድረስ ተመሳሳይ ውል ለሚፈርሙ አቅራቢዎች ተመሳሳይ ይዘት ያለው ውል ሆኖ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣

ሠ/ በውል አፈጻጸም ወቅት ክፍያን፣ ቁጥጥርን፣ የመረጃ ልውውጥን እና የመሳሰሉት ተግባራት በእኩልነት ለሁሉም አቅራቢዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ።

፯፲.፬ በመንግሥት ግዥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ተሳትፎ ያላቸው የመንግሥት መ/ቤት ሠራተኞች እና ኃላፊዎች በግዥ ሥራቸው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ወይም ሊያሳድር የሚችል ምንም ዓይነት ስጦታ ከሦስተኛ ወገን መቀበል የለባቸውም። ለዚህ ንዑስ አንቀፅ አፈፃፀምም የመንግሥት መ/ቤት ሠራተኞች ወይም ኃላፊዎች የሚከተሉትን ያካተተ ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል:-

ከዚህ በታች በፊደል ተራ (ሠ) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ:-

ሀ/ የገንዘብ ዋጋ ያለውን ስጦታ በተለይ ለመንግሥት መ/ቤቱ ከአቅራቢ/ዕጩ አቅራቢ ከሆነ አካል አለመቀበል፣

ለ/ የሥራ ዕድል ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ አለመቀበል፣

ሐ/ በግል በሚደረግ ግዥ ላይ ለመንግሥት መ/ቤቱ አቅራቢ/ዕጩ አቅራቢ ከሆነ አካል የተለየ የዋጋ ቅናሽ ወይም አገልግሎት አለመቀበል፣

መ/ በሥራው ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል የግብዣ ፕሮግራም አለመቀበል፣ ሆኖም ጉዞን ያላካተተ እና ጋባዡ ከመንግሥት መ/ቤቱ ጋር ካለው የሥራ ግንኙነት ጋር የማይገናኝ ግብዣ ሲሆን ሊቀበል ይችላል።

ሠ/ ከላይ በፊደል ተራ (ሀ) ላይ የተቀመጠው ቢኖርም ሠራተኛው ወይም ኃላፊው አቅራቢው/ዕጩ አቅራቢው ለማስታወቂያነት አገልግሎት የሚያዘጋጃቸው

የውስጥ እሴት እንጂ የገበያ ዋጋ የሌላቸው በነጻ የሚታደሉ ስጦታዎችን መቀበል ይችላል፡፡

፮፲.፭ የመንግሥት መ/ቤት ሠራተኛ ወይም ኃላፊ በስራ አጋጣሚ የተመለከታቸውን የተፈጠሩ ወይም ሊፈጠሩ የታሰቡ የሙስና ተግባራትን ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ የሚኖርበት ሲሆን ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸምም:-

ሀ/ የሚያደርገው ጥቆማ በማስረጃ የተደገፈ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ለ/ እራሱን የታሰበውን የሙስና ተግባር ሊደግፍ ከሚችል ማንኛውም ተግባር መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

፮፲.፮ የመንግሥት መ/ቤቱ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ከግዥ ሥራ ጋር በተገናኘ ያወቃቸውን የመንግሥት መ/ቤቱን ወይም የዕጩ ተወዳዳሪውን ወይም የአቅራቢውን ሚስጥራዊ መረጃዎች መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ ለዚህም:-

ሀ/ ውድድርን ሊገድብ የሚችል ወይም ለተወዳዳሪዎች ፍትሐዊ ያልሆነ ጥቅም የሚያስጥ ወይም የመንግሥት መ/ቤቱን ጥቅም ሊጎዳ የሚችል መረጃ በልዩ ሁኔታ በመ/ቤቱ ኃላፊዎች ካልተፈቀደ በስተቀር ለማንኛውም አካል አለመስጠት፣

ለ/ የመንግሥት መ/ቤቱ በውል አፈጻጸም ወቅት ከአቅራቢዎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት የመንግሥት መ/ቤቱን ውሳኔ እና መረጃ መጠበቅ፣

ሐ/ የዕጩ ተወዳዳሪዎችን መረጃ እና የግምገማ ሂደት ውጤቱ በመንግሥት መ/ቤቱ ከመገለጹ በፊት ለማንኛውም አካል አለማሳወቅ፣

## 61. ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚጠበቅ ሥነ - ምግባር

በመንግሥት ግዥ የሚሳተፉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በአዋጁ አንቀጽ ፳፩.፪ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን ዋና ዋና የሥነ-ምግባር መርሆዎች መከተል አለባቸው:-

ሀ/ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም አቅራቢ በመንግሥት ግዥ ሥራ ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ለተሰማራ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ራሱ ወይም በሦስተኛ ወገን በኩል በአዋጁ በአንቀጽ ፳፩ በን/አንቀጽ ፪ ሥር የተጠቀሰውን ስጦታ መስጠት የለበትም፡፡

ለ/ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም አቅራቢ የሚያውቀውንና የመንግሥት መ/ቤቱ በግዥ አፈጻጸም ወይም በውል አስተዳደር ወቅት ለሚሰጠው ውሳኔ ይረዳዋል ብሎ የሚገምተውን መረጃ ለመንግሥት መ/ቤቱ መግለጽ አለበት፡፡

ሐ/ የመንግሥት መ/ቤት በሚያደርገው የግዥ አፈጻጸም በመስኩ ከተሰማራ ሌላ ተወዳዳሪ ጋር በመነጋገር ዋጋ መስጠት፣ መ/ቤቱን ሊጎዳ የሚችል መረጃ መለዋወጥ ወይም በግዥ አፈጻጸሙ ለመሳተፍ የሌላ ተወዳዳሪን ሰነድ ወይም መረጃ መጠቀም የለበትም፡፡

መ/ በመንግሥት ግዥ አፈጻጸም ሊፈፀም የታሰበን የሙስና ተግባር ለሚመለከተው አካል ማሳወቅና የሙስና ተግባሩ ተባባሪ ሆኖ አለመገኘት

# ክፍል ፩፫

# በመንግሥት ግዥ አፈጻጸም ላይ የሚቀርብ አቤቱታ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ቦርድ

## ፯፪. <u>የቦርድ አባላት ስያሜና የስራ ዘመን</u>

ሀ/ ቢሮው ከእጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ከተጫራቾች በመንግስት መስሪያ ቤቶች የግዥ አፈጻጸም ላይ የሚቀርብን አቤቱታ አጣርቶ ውሳኔ የሚሰጥ፣

ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚወከል .................. ሰብሳቢ፣
ከንግድ ምክር ቤት የሚወከል............................................... አንድ አባል፣
ከመንግሥት መ/ቤቶች የሚመረጥ ...................................... ሶስት አባል፣
ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚወከል............................ አንድ አባል፣
ከመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የሚወከል..... አንድ አባል፣

በድምሩ ሰባት የቦርድ አባላትን የሚሰይም ሲሆን ከኤጀንሲው አንድ ባለሙያ ድምፅ የሌለው አባል ሆኖ በፀሐፊነትና በአስረጂነት እንዲሰራ ይመደባል፡፡ የቦርድ አባላት ብዛት እንደ አስፈላጊነቱ እስከ ዘጠኝ አባላት ሊኖሩት ይችላል፣

ለ/ የቦርዱ አባላት በተቻለ መጠን በስምምነት ውሳኔዎችን የሚያሳልፉ ሲሆን አስፈላጊ ሲሆን በድምጽ ብልጫ ውሳኔ ሊተላለፍ ይችላል፡፡ የአባላት ድምጽ እኩል በእኩል በሚሆንበት ጊዜ የቦርዱ ሰብሳቢ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

ሐ/ የቦርድ አባላት የስራ ዘመን ሦስት ዓመት ነው:: ሆኖም የስራ አፈጻጸማቸውና ያላቸው ስነ-ምግባር ታይቶ ለሌላ አንድ ተመሳሳይ የስራ ዘመን እንዲሰሩ ሊራዘምላቸው ይችላል::

መ/ ለቦርድ አባልነት የሚሰየሙት በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር በቂ እውቀትና ልምድ ያካበቱ፣መልካም ባህሪና ስነ-ምግባር ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል::

## ፷፫. <u>የቦርድ ስብሰባ</u>

ሀ/ የቦርድ አባላት ስራቸውን ለማከናወን እንደአስፈላጊነቱ በአስራ አምስት ቀን የሚሰበሰቡ ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተጨማሪ የስብሰባ ቀን ሊወሰኑ ይችላሉ፣

ለ/ ከቦርድ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ ከተገኙ ስብሰባው ሊካሄድ ይችላል፣

ሐ/ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሰብሳቢው በስብሰባው ላይ የማይገኝ ሲሆን፣ ስብሰባውን በጊዜያዊነት የሚመራለት ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል ሊወክል ይችላል::

## 64. <u>ከቦርድ አባልነት መልቀቅ</u>

የቦርድ አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ በማንኛውም ጊዜ ከቦርድ አባልነት መልቀቂያ ማመልከቻ ለቢሮው በማቅረብ ሲፈቀድላቸው መልቀቅ ይችላሉ::

## ፷፭. <u>የቦርድ አባልነት መቋረጥ</u>

ቢሮው ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የቦርድ አባልን በአባልነት መቀጠል ሊያቋርጥ ይችላል:

ሀ/ በአዕምሯዊ ወይም በአካላዊ ጉዳት ኃላፊነቱን መወጣት ካልቻለ፣

ለ/ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ከተረጋገጠ፣

ሐ/ የሥነ-ምግባር ወይም የዲሲፕሊን ጉድለት ከተገኘበት፣

መ/ ያለ በቂ ምክንያት በ፫ /ሶስት/ ተከታታይ የቦርዱ ስብሰባዎች ላይ ካልተገኘ

## ፺፮. የጥቅም ግጭትን ስለመግለጽ

ማንኛውም የቦርዱ አባል ከአቤቱታ አቅራቢ ወይም አቤቱታ ከቀረበበት ግዥ አፈጻጸም ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ግንኙነት ካለው ይህንኑ ለቦርዱ በማሳወቅ ከቦርዱ ስብሰባ ራሱን ማግለል አለበት::

## ፺፯. የቦርዐ ስልጣን

ቦርዱ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ አሸናፊውን ተጫራች ከመምረጥ ወይም ውል ከመፈረም ጋር የተያያዙ ውሳኔዎችን ከማሳለፍ በስተቀር የሚከተሉት ስልጣኖች ይኖሩታል::

ሀ/ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ወይም ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት ህግ ከሚያዘው ውጭ ስለመፈጸሙ ወይም ግዥ በትክክል ስላለማከናወኑ ወይም የግዥውን አመራር በትክክል ስላለመፈጸሙ ወይም የጥቅም ግጭት ወይም የሙስና ተግባር ስለመፈጸሙ አቤቱታ ያቀረበ እንደሆነ ከግዥው ጋር የተያያዙ መረጃዎች፣ ሰነዶች፣ መዝገቦችና መግለጫዎች ከመንግሥት መ/ቤቱ ወይም ከእጩ ተወዳዳሪው እንዲቀርቡለት የማዘዝ፣

ለ/ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የመንግሥት መ/ቤቱ ቀጣይ እንቅስቃሴ እንዳያደርግ የጽሁአ ማስታወቂያ መላክ፣

ሐ/ የቀረበው አቤቱታ በኤጀንሲው ወይም በሌሎች ባለሙያዎች ዝርዝር የቴክኒክ ምርመራ ተደርጎበት ሪፖርት እንዲቀርብለት የማድረግ፣

መ/ ምስክሮችን የመጥራት፣ ምስክሮችና ግዥው የሚመለከታቸው ወገኖች ቃላቸውን በመሃላ እንዲሰጡ የማድረግ፣

ሠ/ የመንግሥት መ/ቤቱ በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሰረት ስራውን እንዲያከናውን ትዕዛዝ የማስተላለፍ፣

ረ/ የመንግሥት መ/ቤቱ ከህግ ውጭ ያከናወነው ተግባር ወይም የሰጠው ውሳኔ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን የማድረግ፣

ሰ/ ተገቢ ሆኖ ካላገኘው የተጫራቹን ወይም የእጩ ተወዳዳሪውን አቤቱታ ውድቅ የማድረግ፣

ሽ/ አቤቱታው ለቦርዱ የቀረበው የመንግሥት መ/ቤቱ ለአቤቱታው ምላሽ ከሰጠ በኋላ ፲፭ የሥራ ቀናት አልፎ ከሆነ ወይም አቤቱታው በመጀመሪያ ለመንግሥት መ/ቤቱ ያልቀረበ ከሆነ አቤቱታውን ውድቅ የማድረግ፣

## ፺፰. የቦርዱ ተግባር

ቦርዱ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

ሀ/ ከዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ከተጫራች አቤቱታን መቀበል፣

ለ/ አቤቱታው ለቦርዱ የቀረበው ዕጩ ተወዳዳሪው ወይም ተጫራቹ ለመንግሥት መ/ቤቱ አቤቱታውን አቅርቦ መልስ በተሰጠው ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ወይም መ/ቤቱ መልሱን አዘግይቶ ከሆነ አቤቱታው ለመ/ቤቱ ከቀረበ ከ1፲ኛው ቀን በኋላ ባሉት ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ መሆኑን ማጣራት፣

ሐ/ አቤቱታው የቀረበው በተገቢው ጊዜና ሁኔታ ከሆነ አቤቱታ ለቀረበበት የመንግሥት መ/ቤት አቤቱታ የቀረበበት መሆኑንና ከግዥው አፈጻጸም ጋር የተያያዙ ሰነዶችንና መግለጫዎች እንዲልክ እና በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ቀጣይ እንቅስቃሴ እንዳያደርግ የጽሁአ ማስታወቂያ መላክ፣

መ/ የጽሑፍ ማስታወቂያ የደረሰው የመንግሥት መ/ቤት የግዥ ሂደት የተከናወነባቸውን ሰነዶች፣ ማስረጃዎችና መግለጫ እንዲልክ መከታተል፣

ሠ/ ከጽ/ቤቱ ተጠናቅረው የቀረቡትን የአቤቱታውን ጭብጦች፣ ከመንግሥት መ/ቤቱ የተሰጠውን ምላሽ፣ ማስረጃዎችን፣ ሰነዶችን እና መግለጫዎችን ከመንግሥት ግዥ ህጉ አኳያ በመመርመር ውሳኔ መስጠት፣

ረ/ ውሳኔው ለሚመለከታቸው አካላት በጽሁአ እንዲደርስ ማድረግ፣

ሰ/ ስለተከናወኑ ተግባራት ለቢሮው ሪፖርት ማቅረብ፣

# ክፍል ፩፬

## ለመንግሥት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ወይም ለቦርድ ጽ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ የሚታይበት ሥርዓት

### 69. የዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች አቤቱታ የማቅረብ መብት

በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 62 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ጨረታውን ያወጣው የመንግስት መ/ቤት በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ የተመለከተውን በአግባቡ ባለመፈጸሙ ምክንያት ጉዳት ወይም ኪሳራ ደርሶብኛል ወይም ሊደርስብኝ ይችላል የሚል ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ጨረታው እንደገና እንዲታይለት ወይም ሂደቱ እንዲጣራለት ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ለቦርድ ጽ/ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

### ፯፲. አቤቱታ ማቅረብ የማይቻልባቸው ሁኔታዎች

ከዚህ በታች በተመለከቱት ምክንያቶች አቤቱታ ማቅረብ አይቻልም፡፡

ሀ/ በግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጁ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ በተወሰነው የግዥ ዘዴ ምርጫ ላይ፣

ለ/ በውስን ጨረታና በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈጸም ግዥ በተከናወነ የተጫራቾች አመራረጥ ወይም በጨረታ ሠነዱ ላይ አስቀድሞ በሰፈረ የተጫራቾች ማወዳደሪያ መስፈርት ላይ፣

ሐ/ በአዋጁ አንቀጽ ፩፬ እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፬፫÷፫ መሠረት ለአገር ውስጥ አቅራቢዎች፣ ምርቶችና እና የግንባታ ዘርፍ ስራዎች በተሰጠ ልዩ አስተያየት ላይ፣

መ/ በአዋጁ አንቀጽ ፩፱ መሰረት ጨረታን፣ የመጫረቻ ሰነድን ወይም የዋጋ ማቅረቢያን ውድቅ ለማድረግ በተሰጠ ውሳኔ ላይ፣

ሠ/ መ/ቤቱ የግምገማውን ውጤት ካሳወቀበት ወይም ለቀረበለት አቤቱታ ውሳኔውን በጽሁፍ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ የሚቆጠር ፭ /አምስት/ የስራ ቀን ካለፈ፡፡

ረ/ አቤቱታው የቀረበው ውል ከተፈረመ እና ውሉ በአዋጁ አንቀጽ ፫፭ ንዑስ አንቀጽ ፫ እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፯፩.፩ ፊደል ተራ "ሀ" የተጠቀሰውን ፯ የሥራ ቀናት የጊዜ ገደብ ጠብቆ የተፈረመ ከሆነ፣

## 71. ለመንግሥት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ የሚቀርብ አቤቱታ የሚጣራበት ሥርዓት

71.፩ <u>የግዥ ውል ከመፈረሙ በፊት፣</u>

ሀ/ ጨረታውን ያወጣው የመንግሥት መ/ቤት የጨረታውን ወይም የአቤቱታውን ውጤት ለተጫራቾች ከገለጸበት ቀን ጀምሮ ተጫራቾች አቤቱታ ካላቸው ማቅረብ እንዲችሉ ፯ የስራ ቀናት ሊጠብቃቸው ይገባል።

ለ/ በግዥ አፈጻጸም ሂደት ጉዳት ወይም በደል ደርሶብኛል የሚል አቅራቢ ወይም ተጫራች ለአቤቱታው መሰረት የሆነውን የመጨረሻ ውሳኔ በይፋ ካወቀበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 5 የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ጨረታውን ላወጣው የመንግሥት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ማቅረብ ይኖርበታል። ከዚህ ጊዜ በኋላ ለመ/ቤቱ የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም፡

ሐ/ አቤቱታ ባቀረበው ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች እና ጨረታውን ባወጣው የመንግስት መ/ቤት በስምምነት ካልተፈታ በስተቀር በአዋጁ አንቀጽ ፺፤ ንኡስ አንቀጽ ፫ በተጠቀሰው መሠረት የመንግስት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ አቤቱታ ከቀረበበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር 1፤ የሥራ ቀናት ውስጥ ለቀረበው አቤቱታው ውሳኔውን በጽሁፍ መስጠት አለበት።

መ/ የመንግሥት መ/ቤቱ ውሳኔውን በሰጠ በ፫ የሥራ ቀናት ውስጥ የውሳኔውን ቅጅ አቤቱታውን ላቀረበው ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች እንዲደርስ ማድረግ አለበት።

71.፪ <u>በሁለት ኤንቬሎፕ የቀረበ ጨረታ፣</u>

በን/አንቀጽ 71.1. የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጫራቾች የቴክኒክና የዋጋ የመጫረቻ ሰነዳቸውን በተለያየ ሁለት ኤንቬሎፕ እንዲያቀርቡ በተደረገበት ጨረታ፣

ሀ/ የቴክኒክ ግምገማ ውጤቱን የመንግሥት መ/ቤቱ ለሁሉም በጨረታው ተሳታፊ ለሆኑ ተጫራቾች በእኩል ጊዜ በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

ለ/ ማንኛውም ተጫራች የቴክኒክ ግምገማው አፈፃፀም የግዥ አዋጁን፣ የአፈፃፀም መመሪያውን እና የጨረታ ሰነዱን መሠረት አድርጎ አልተከናወነም የሚል ቅሬታ ካለው፣ቅሬታውን በ፭ የሥራ ቀን ውስጥ ማቅረብ እንደሚችል የመንግሥት መ/ቤቱ የቴክኒክ ግምገማ ውጤቱን ለተጫራቾች በሚያሳውቅበት ደብዳቤ ላይ ማመልከት ይኖርበታል።

ሐ/ የቴክኒክ ግምገማውን በሚመለከት ለቀረበው አቤቱታ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የተሰጠው ውሳኔ የግዥ አዋጁን፣ መመሪያውን እና የጨረታ ሰነዱን የጠበቀ አለመሆኑን ማረጋገጥ የሚችል ተጫራች የኃላፊውን ውሳኔ ባወቀ በ፫ የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል።

መ/ የመንግሥት መ/ቤቱ የዋጋ መወዳደሪያ ኃሳብ የያዘውን ኤንቨሎፕ ሊከፍት የሚችለው የቴክኒክ ግምገማ ውጤቱን ለተጫራቾቹ ካሳወቀ ከ፫ የሥራ ቀናት በኋላ ይሆናል። ሆኖም የቴክኒክ ግምገማውን በሚመለከት ለቀረበው አቤቱታ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በሰጠው ውሳኔ ባለመስማማት በተገቢው ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ አቤቱታ የቀረበ ከሆነ መ/ቤቱ ቦርዱ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የዋጋ መወዳደሪያ ኃሳብ የያዘውን ኤንቨሎፕ ሳይከፍት እንደታሸገ ማቆየት ይኖርበታል።

፺፩.፫ አቤቱታ የቀረበበት ማናቸውም ግዥ የሚጣራው ለጨረታው የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ፣ አዋጅና መመሪያ መሠረት በማድረግ ብቻ ይሆናል።

## ፸፪. የመንግሥት መ/ቤቶች የግዥ አፈጻጸም ሂደትን ማገድ ስለመቻላቸው

ሀ/ ጨረታውን ያወጣው የመንግስት መ/ቤት አቤቱታው ከዚህ በላይ በአንቀጽ 71 ፊደል ተራ "ሐ" ላይ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የቀረበ መሆኑን ካረጋገጠ አቤቱታው ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ጨረታው ታግዶ እንዲቆይ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ለ/ በመንግስት መ/ቤት የሚተላለፍ ማናቸውም ውሳኔ እንዲሁም የውሳኔው ምክንያቶች እና ሁኔታዎች የግዥውን ስርዓት የሚያሳዩ ሰነዶች አካል ሆነው መያዝ አለባቸው፡፡

## 73. አቤቱታ ለቦርድ ጽ/ ቤት የሚቀርብበትና የሚጣራበት ስርዓት

ሀ/ በአዋጁ አንቀጽ ፯፲ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት የመንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ አቤቱታ ከቀረበበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር አስር የሥራ ቀናት ውስጥ ለአቤቱታው ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ውሳኔ ተሰጥቶ አቤቱታ አቅራቢው በተሰጠው ውሳኔ ያልረካ እንደሆነ የመስሪያ ቤቱ ውሳኔ በጽሁአ ከተገለጸለት ወይም ውሳኔው በወቅቱ ካልተሰጠ ውሳኔው መሰጠት ከነበረበት ቀነ ገደብ ማብቂያ ጀምሮ በሚቆጠር ፭ የሥራ ቀን ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን ለቦርድ ጽ/ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ለቦርድ ጽ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

ለ/ እጩ ተወዳዳሪው ወይም ተጫራቹ አቤቱታውን ለቦርድ ጽ/ቤት ሲያቀርብ ለመሥሪያ ቤቱ ያቀረበውን አቤቱታ የሚያሳይ ደብዳቤ፣ በመንግስት መስሪያ ቤት ለአቤቱታው ውሳኔ ተሰጥቶ ከሆነ የውሳኔውን ቅጂ፣ የአቤቱታውን ጭብጥና፣ ተያያዥ ማስረጃዎችን በአባሪነት ማያያዝ ይኖርበታል፡፡

ሐ/ የቦርዱ ጽ/ቤት አቤቱታው እንደቀረበለት መ/ቤቱ አቤቱታ የቀረበበት መሆኑን፣ በቀረበበት አቤቱ□ ላይ ያለውን ማስረጃና መግለጫ ማስታወቂያው በደረሰው በአምስት የሥራ ቀን ውሰጥ እንዲያቀርብ እንዲሁም ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ቀጣይ የግዥ ሂደት እንቅስቃሴ እንዲያቆም የሚገልጽ ማስታወቂያ ለመንግስት መ/ቤቱ ይልካል፡፡

መ/ አቤቱታ የቀረበበት የመንግስት መ/ቤት እንዲልክ የሚጠየቃቸውን ሠነዶች ማስታወቂያው ከተላከለት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፫ የሥራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሠ/ ቦርዱ አቤቱ□ የቀረበበትን ማናቸውንም ግዥ የሚያጣራው እና ውሳኔ የሚሰጠው መ/ቤቱ ለጨረታው ያዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ፣ የግዥ አዋጅ፣ መመሪያ እንዲሁም

እንደአስፈላጊነቱ የጨረታ ግምገማ ሪፖርቱን፣ ተጫራቹ ያቀረበውን የመጫረቻ እና ሌሎች ሠነዶችን መሠረት በማድረግ ይሆናል።

ረ/ ቦርዱ ከላይ በአንቀፅ ፸፫ ፊደል ተራ "መ" መሠረት የቀረቡለትን ሰነዶች መርምሮ ውሳኔውን በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታ ላቀረበው ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች እና ለመ/ቤቱ በጽሁፍ መስጠት አለበት።

ሰ/ የቦርዱ ጽ/ቤት ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ ግልባጭ ወዲያውኑ አቤቱታውን ላቀረበው አቅራቢ ወይም ተጫራች እና አቤቱታ ለቀረበበት የመንግሥት መ/ቤት እንዲደርስ ማድረግ አለበት።

# ክፍል ፲፰

## ለኤጀንሲው የሚቀርብ የጥፋተኝነት ሪፖርት የሚታይበት ስርዓት

## 74. የጥፋተኝነት ሪፖርት አቀራረብና የማጣራት ሥርዓት አፈፃፀም

ኤጀንሲው በአዋጁ አንቀጽ ፸፪ መሠረት የመንግሥት መ/ቤቶች በተጫራቾች ወይም በአቅራቢዎች ላይ የሚያቀርቡትን የጥፋተኝነት ሪፖርት በሚከተለው ሁኔታ አጣርቶ ውሳኔ ይሰጣል።

፸፬.፩ ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት በመንግሥት ግዥ የተሳተፈ ማንኛውም ተጫራች/ አቅራቢ የተሳተፈበት ግዥ የሚመራበት ሕግ ከሚያዘው ውጭ መፈፀሙን፣ ውል ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆኑን፣ ማጭበርበሩን፣ የሀሰት ሰነድ ማቅረቡን፣ መመሳጠሩን፣ የሙስና ተግባር መፈፀሙን እና/ወይም የገባውን የውል ግዴታ ባለመፈፀሙ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ማረጋገጥ ከቻለ በጥፋት ፈፃሚው ላይ የጥፋተኛነት ሪፖርት ለኤጀንሲው ሊያቀርብ ይችላል።

74.፪ የመንግሥት መ/ቤቱ በተጫራቹ ወይም አቅራቢው ላይ የጥፋተኝነት ሪፖርት ለኤጀንሲው ሲያቀርብ የአቤቱታውን ጭብጥ የሚገልጽ መግለጫ፣ ግዥ የተካሄደባቸውን ሰነዶች ቅጂና ሌሎች ጉዳዩን ለማጣራት የሚረዱ ተያያዥ ማስረጃዎችን አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል።

፯፬.፫ ኤጀንሲው ሪፖርት ለቀረበበት ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የቀረበበትን የጥፋተኝነት ሪፖርት ፍሬ ሀሳብ በመግለጽ በበኩሉ ያለውን ማስረጃ እና ማብራሪያ በ፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ለኤጀንሲው እንዲያቀርብ የጽሑአ ማስታወቂያ መላክና አፈፃፀሙን መከታተል ይኖርበታል፡፡

፯፬.፬ ኤጀንሲው ከመንግሥት መ/ቤቱ እንዲሁም ከተጫራቹ ወይም ከአቅራቢው የቀረቡለትን መግለጫና ማስረጃዎች ከአዋጁ፣ ከዚህ መመሪያ፣ ከጨረታ ሰነዱና ከግዥ ውሉ አኳያ በማጣራት የጥፋተኝነት ሪፖርቱ በቀረበ በ፩፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሁፍ ሪፖርት ላቀረበው የመንግሥት መ/ቤት እና የጥፋተኝነት ሪፖርት ለቀረበበት አቅራቢ ወይም ተጫራች እንዳስፈላጊነቱም ለሌሎች የሚመለከታቸው አካላት መላክ አለበት፡፡

74.፭ በኤጀንሲው የሚሰጠው የቅጣት ውሳኔ የአዋጁን አንቀጽ ፯፪ ን/አንቀጽ 62.፭ የተከተለ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ ፯፬.፭.፩፣ ፯፬.፭.፪ ወይም ፯፬.፭.፫ ላይ ከተመለከቱት መካከል አንዱ ሊሆን ይችላል፡፡

፯፬.፭.፩ ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የግዥውን ግምገማ ውጤት ሆን ብሎ ለማዛባት ወይም ለማስለወጥ በጨረታው ሂደት ወይም በውል አስተዳደር ወቅት ከዚህ በታች የተገለጹትን መፈፀሙ ከተረጋገጠ እንደነገሩ ሁኔታ ከሁለት ዓመት ላላነሰ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት በሚያወጣው የግዥ ጨረታ ላይ እንዳይሳተፍ ለማድረግ ከአቅራቢነት መዝገብ ይሰረዛል፡፡

ሀ/ የሙስና ተግባር ማለትም በግዥ ሙያ ላይ ለተሰማራ ባለሙያ ወይም ኃላፊ ጉቦ ወይም ማባበያ ወይም ማንኛውንም ዋጋ ያለውን ነገር መስጠቱ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣

ለ/ የማጭበርበር ማለትም ሀሰተኛ ወይም ህጋዊ ያልሆነ ሰነድ ማቅረቡ ወይም በኤጀንሲው ታግዶ እያለ የእገዳው ጊዜ ሳይጠናቀቅ በሌላ ጨረታ ላይ ተካፍሎ መገኘቱ ወይም ከውል ውጭ ጥራት የጎደለውን ዕቃ ወይም አግልግሎት ወይም የግንባታ ስራ ወይም የምክር አገልግሎት ዕውነተኛ ወይም ትክክለኛ አስመስሎ ማቅረቡ ሲታወቅ፣

ሐ/ ከሌሎች ተጫራቾች ጋር ተመሳጥሮ ዋጋ በመወሰን ለሌሎች ተጫራቾችና መ/ቤቱ ከነጻ ውድድር ማግኘት የሚችሉትን ጥቅም ማሳጣቱ ሲረጋገጥ፣

መ/ ከመንግስት መ/ቤት ሰራተኞች ወይም ኃላፊዎች ጋር በመመሳጠር ከውሉ ውጭ የሆነ ዕቃ ወይም አገልግሎት ወይም የምክር አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ማቅረቡ ሲረጋገጥ፣

ሠ/ በግዥ ስራ ላይ የተሰማራን ባለሙያ ወይም ኃላፊ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መጉዳቱ ወይም ለመጉዳት ማስፈራራቱ (መዛቱ) ወይም ማስገደዱ ሲረጋገጥ፣

ረ/ ቀደም ሲል በኤጀንሲው የተጣለበትን ቅጣት ከፈጸመ ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር በሁለት ዓመት ውስጥ ሌላ እገዳ የሚያስከትል ጥፋት መፈጸሙ ሲታወቅ፣

፺፬.፭.፪ ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀሙ ሲረጋገጥ፣ እንደ ጥፋቱ ክብደት እየታየ ከስድስት ወር ላለነሰና ከሁለት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ በማንኛውም የመንግሥት ግዥ ጨረታ እንዳይሳተፍ ለማድረግ ከአቅራቢነት መዝገብ ይሰረዛል፡፡

ሀ/ በገባው ውል መሠረት አቅርቦቱን ወይም አገልግሎቱን ወይም የምክር አገልግሎቱን ወይም የግንባታ ሥራውን፣ ባለማጠናቀቁ ወይም አቅርቦቱን ጀምሮ በማቋረጡ ምክንያት በመንግሥት መ/ቤቱ ላይ የገንዘብ ኪሳራ ወይም የሥራ መጓተት ወይም የጥቅም ማጣት ካስከተለ፣

ለ/ በጨረታ ውድድሩ አሸናፊ መሆኑ በጽሁፍ ተገልጾለት ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ባለመሆኑ ምክንያት መ/ቤቱ ግዥውን ከሌላ ተጫራች በመፈጸሙ በመንግሥት መ/ቤቱ ላይ ኪሳራ ወይም የሥራ መጓተት ካስከተለበት፣

ሐ/ ከዚህ ቀደም (ከ፫ ዓመት ወዲህ) ሌላ ጥፋት ፈጽሞ በኤጀንሲው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት የነበረ ሆኖ አሁን የቀረበበት ሪፖርት ሌላ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጥ የግዥ አፈጻጸም ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ፣

፺፬.፭.፫ ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀሙ ሲረጋገጥ፣ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡

ሀ/ ውል ገብቶ አቅርቦቱን ወይም አገልግሎቱን ወይም የምክር አገልግሎቱን ወይም የግንባታ ሥራውን በውሉ በተቀመጠው ጊዜ ሳይሆን ዘግይቶ በማቅረቡ ምክንያት በመ/ቤቱ ሥራ ላይ ችግር መፍጠሩ፣

ለ/ ግዥ ለሚፈጽም ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ፕሮፎርማ እንዲሰጥ ተጠይቆ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆኑ፣

፺፬.፫.፬ ኤጀንሲው ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፺፬..፫.፩፣ ፺፬.፫.፪ መሠረት የሰጠው ውሳኔ ግልባጭ ለሁሉም የፌደራል መ/ቤቶች፣ በክልል ለሚገኙ የፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች፣ ኮሌጆችና፣ ማዕከላት፣ ለክልሎች እና ለከተማ አስተዳደሮች እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡ በኤጀንሲው ድረ-ገጽ ላይም ውሳኔው እንዲሰፍር ይደረጋል፡፡

፺፬.፫.፫ ኤጀንሲው ከላይ በተመለከተው ሁኔታ የሚሰጠው ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት መ/ቤቶች ተጫራቹ ወይም አቅራቢው በፈጠረው ችግር ምክንያት የደረሰባቸውን ኪሣራ በግዥ ውላቸው እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት መጠየቅ ይችላሉ፡፡

## ፺፭. ከአቅም በላይ የሆነ ችግር

፺፭.፩ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ደርሷል የሚባለው አቅራቢው ድንገት ደራሽ በሆነ ሁኔታ የውል ግዴታውን እንዳይፈጽም ከአቅሙ በላይ የሆነ ችግር ባጋጠመው ጊዜ ነው፣

፺፭.፪ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ነው ሊያሰኙ የሚችሉ ምክንያቶች ከሚከተሉት አንዱ ሊሆኑ ይችላሉ፣

ሀ/ ውል እንዳይፈጸም በመንግስት የሚደረግ ክልከላ፣

ለ/ እንደ መሬት መናወጥ፣ መብረቅ፣ ማዕበል፣ እና የመሳሰሉ ፍጥረታዊ መቅሰፍቶች፣

ሐ/ የጠላት፣ የውጭ አገር ወይም የአገር ውስጥ ጦርነት፣

መ/ ውል የገባው ወገን መሞት ወይም ባልታሰበ ሁኔታ የሚደርስበት ከባድ አደጋ ወይም ጽኑ ህመም፣

ሠ/ በፍትሐብሔር ሕግ የተዘረዘሩ ሌሎች ከአቅም በላይ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ፣

፲፰.፫ ግልጽ የሆነ ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በቀር ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ተደርገው ሊቆጠሩ አይችሉም:-

ሀ/ በተዋዋይ ፋብሪካ ወይም ስራውን ከሚያከናውንበት ባንደኛው ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ውስጥ የተደረገ የሠራተኛ አድማ ወይም የመ/ቤት መዘጋት፣

ለ/ ለውሉ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶች ዋጋ መወደድ ወይም መርከስ፣

ሐ/ ተዋዋይ ያለበትን የውል ግዴታ አፈጻጸም ወጪ የሚያከብድበት አዲስ ህግ መውጣት፣

## ፲፱. <u>አቤቱታን በፍርድ ቤት ስለማየት</u>

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፲፭፣ ፲፮ እና ፲፯ መሠረት የመንግሥት መ/ቤቱ፣ ቦርዱ ወይም ኤጀንሲው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ዕጩ ተወዳዳሪ፣ ተጫራች ወይም አቅራቢ ጉዳዩን አግባብ ላለው ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል::

# ክፍል ፲፯

## <u>የተሻሩ መመሪያዎች እና ይህ መመሪያ የሚፀናበት ጊዜ</u>

### ፺፯. <u>የተሻሩ መመሪያዎች፣</u>

በገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ታህሳስ 2003 ዓ.ም. የወጣው የግዥ አፈጻጸም መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

### ፺፰. <u>መመሪያው የሚፀናበት ቀን</u>

ይህ መመሪያ  ሐምሌ ፪ሺ5 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*ድሬዳዋ ሐምሌ ፪ሺ፭ ዓ.ም*

*አስራት ጫላ*
*የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት*
*ቢሮ ኃላፊ*

ቅፅ 1.

# የ_______________ በጀት ዓመት

## የግዢ እቅድ ማጠቃለያ /ከመንግስት ግምጃ ቤት/

**የተቋሙ ስም -------------------------------------**

| ተ.ቁ | የግዢው ምድብ | የተመደበ በጀት | | | ግዥ የሚፈጸምበት ጊዜ | ግዥው የሚፈፀምበት የግዥ ዘዴ | ግዢውን ለመፈፀም የሚወስደው ጊዜ | ጨረታ የሚወጣበት /የሚካሄድበት ጊዜ | ግዢው ተጠናቆ ርክክብ የሚፈፀምበት ጊዜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መደበኛ | ካፒታል | የውስጥ ገቢ | | | | | | |
| 1 | ስቴሽነሪ ግዥ | | | | | | | | | |
| 2 | የፅዳት ዕቃዎች ግዥ | | | | | | | | | |
| 3 | የደንብ ልብስ ግዥ | | | | | | | | | |
| 4 | የህትመት ግዥ | | | | | | | | | |
| 5 | የጥገና ስራዎች ግዥ | | | | | | | | | |
| 6 | የምክር አገልግሎት ግዢ | | | | | | | | | |
| 7 | ቋሚ እቃዎች ግዥ | | | | | | | | | |
| 8 | የግንባታ ሥራዎች ግዢ | | | | | | | | | |

ቅፅ 2.

# የ_______________ በጀት ዓመት
# የግዢ እቅድ ማጠቃለያ /ከብድርና እርዳታ/

**የተቋሙ ስም --------------------------------------**

| ተ.ቁ | የግዢው ምድብ | የተመደበ በጀት | | ግዥ የሚፈፀምበት ጊዜ | ግዥ የሚፈፀምበት ዘዴ | ግዢውን ለመፈፀም የሚወስደው ጊዜ | ጨረታ የሚወጣበት /የሚካሄድበት ጊዜ | ግዢው ተጠናቆ ርክክብ የሚፈፀምበት ጊዜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እርዳታ | ብድር | | | | | | |
| 1 | ስቴሽነሪ ግዥ | | | | | | | | |
| 2 | የፅዳት ዕቃዎች ግዥ | | | | | | | | |
| 3 | የደንብ ልብስ ግዥ | | | | | | | | |
| 4 | የህትመት ግዥ | | | | | | | | |
| 5 | የጥገና ስራዎች ግዥ | | | | | | | | |
| 6 | የምክር አገልግሎት ግዢ | | | | | | | | |
| 7 | ቋሚ እቃዎች ግዥ | | | | | | | | |
| 8 | የግንባታ ሥራዎች ግዢ | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |

ቅፅ.3

# የ_____ በጀት ዓመት በግዥ እቅድ ተይዘው የሚገዙ እቃዎች ዝርዝር

የግዢው ምድብ ________________________________

| ተ/ቁ | የሚገዛው ዕቃ/አገልግሎት/የግንባ ሥራ ዓይነት ዝርዝር | መለኪያ | መጠን | ግምታዊ ነጠላ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

## ፩. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሰብሳቢና ፀሐፊ ዋና ዋና ኃላፊነቶች

### ፩.፩ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኃላፊነቶች

የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሰብሳቢ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚሾም ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል::

፩. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴን የስብሰባ ቀንና ሰዓት ይወስናል ስብሰባ ይመራል::
፪. ከጨረታ ሂደት ጋር የተያያዙ ተግባራት የመንግስት ግዥ አዋጅና መመሪያውን ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን ያረጋግጣል፣

### ፩.፪ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ፀሐፊ ኃላፊነት

የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ፀሐፊ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚመደብ ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል::

፩. ማንኛውንም የአጽዳቂ ኮሚቴ የስብሰባ ቃለ-ጉባዔ ይመዘግባል፣ ኮሚቴው የተሚሉ ሠነዶች እና መዛግብቶች እንዲኖሩት ያደርጋል፣ በጥንቃቄ ይይዛል::
፪. በውሳኔ አሠጣጥ ሂደት ከአቅራቢዎች ጋር የተደረገ ውይይት ካለ ቃለ-ጉባዔ መዝግቦ መያዝ አለበት::
፫. ከኰሚቴው ሰብሳቢ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት አጀንዳ ያዘጋጃል::
፬. በአፅዳቂ ኮሚቴ ስብሰባዎች ድምፅ ይሰጣል::

### ፩.፫ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ የስብሰባ ሥነ-ስርዓት

፩. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሊሰበሰብ የሚችለው ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ሲቆኙ ሲሆን ውሣኔ የሚተላለፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል::
፪. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ በውሳኔ አሰጣጥ ወቅት እኩል ድምጽ በሚኖረው ጊዜ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ተቀባይነት ይኖረዋል::
፫. በድምፅ አሰጣጥ ወቅት በሃሳብ የተለየ አባል ሲኖር የተለየበት ምክንክያት በቃለ ጉባዔው እንዲሰፍር ይደረጋል::

## ፩. ጨረታ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ጊዜ

፩.፩ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 34 ን/አንቀጽ 34.2 በተገለጸው መሠረት ዝቅተኛ የመጫረቻ ሰነድ ማዘጋጃና ማቅረቢያ ጊዜ በሚከተለው አኳኋን ይወሰናል::

ሀ/ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የጨረታ ሰነድ በሚያዘጋጁበት ጊዜ የግዥውን ዓይነት እና የግዥውን የተሳትፎ ሽፋን በተለይም ውስብስብ የሆኑ እና ያልሆኑ ግዥዎችን በመለየት ከዚህ በታች በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት የመጫረቻ ሰነድ የሚቀርብበት የመጨረሻ ቀን መወሰን አለባቸው::

| ተራ ቁጥር | የግዥው ዓይነት | ውስብስብነት (Complexity) | የግዥው የተሳትፎ ሽፋን | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ | ብሔራዊ ግልጽ ጨረታ | ውስን ጨረታ | |
| | | | | | የውጭ አገር ተጫራች የሚሳተፉበት | የአገር ውስጥ ተጫራች ብቻ የሚሳተፉበት |
| 1 | የግንባታ ዘርፍ ሥራ | ውስብስብ | 45 ቀናት | 30 ቀናት | 45 ቀናት | 30 ቀናት |
| | | ውስብስብ ያልሆነ | 35 ቀናት | 21 ቀናት | 35 ቀናት | 21 ቀናት |
| 2 | ዕቃ | ውስብስብ | 45 ቀናት | 30 ቀናት | 45 ቀናት | 30 ቀናት |
| | | ውስብስብ ያልሆነ | 35 ቀናት | 15 ቀናት | 35 ቀናት | 15 ቀናት |
| 3 | ሌሎች አገልግሎቶች | ውስብስብ | 45 ቀናት | 30 ቀናት | 45 ቀናት | 30 ቀናት |
| | | ውስብስብ ያልሆነ | 35 ቀናት | 15 ቀናት | 35 ቀናት | 15 ቀናት |
| 4 | የምክር አገልግሎት<br>• ፍላጎት መግለጫ (EOI) | ውስብስብ | 14 ቀናት | 10 ቀናት | - | - |
| | | ውስብስብ ያልሆነ | 10 ቀናት | 7 ቀናት | - | - |
| | • የመወዳደሪያ ሐሳብ ማቅረቢያ | ውስብስብ | 45 ቀናት | 30 ቀናት | 35 ቀናት | 30 ቀናት |
| | | ውስብስብ ያልሆነ | 35 ቀናት | 15 ቀናት | 21 ቀናት | 15 ቀናት |

ለ/ ውስብስብ ያልሆነ የዕቃ እና የአገልግሎት ግዥ የሚባለው በዚህ አባሪ ተራ ቁጥር ፩.፪ የተመለከተው ዓይነት ግዥ ነው::

ሐ/ ከአንድ አቅራቢ እንዲሁም በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ በሚፈፀም ግዥ የመጫረቻ ሰነድ የማቅረቢያው ጊዜ የግዥውን ዓይነት፣ አስቸኳይነት፣ ውስብስብነት፣ የአቅራቢዎቹን የተሳትፎ ሽፋን እና የመሳሰሉ ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ በመንግስት መሥሪያቤቶች ይወሰናል::

መ/ ግዥው የሚፈፀመው የሁለት ደረጃ ጨረታ የግዥ ዘዴን መሠረት በማድረግ በሚሆንበት ጊዜ፣

i) በመጀመሪያ ደረጃ እንደግዥው ዓይነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሀ) በተመለከተው መሠረት በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ወይም በአገር ውስጥ ግልጽ ጨረታ ለሚፈፀም ውስብስብ ግዥ የተፈቀደው ዝቅተኛ የጨረታ መቆያ ወይም የመጫረቻ ሰነድ የሚቀርብበት የመጨረሻ ጊዜ ተፈጻሚ ይደረጋል።

ii) በሁለተኛው ደረጃ በመንግስት መሥሪያቤቱ በውድድር ተሳታፊ እንዲሆኑ የተመረጡት የተወሰኑ የአገር ውስጥ ወይም የውጭ አገር ተጫራቾች ለሚሳተፉበት የውስን ጨረታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሀ) ለውስን ጨረታ የተፈቀደው ዝቅተኛ ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናል።

ሠ/ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር ፩.፩ (ሀ) ላይ የተገለጸው ዝቅተኛ የመጫረቻ ሰነድ ማዘጋጃና ማቅረቢያ ጊዜ መሆኑን በመረዳት እንደግዥው ዓይነት እና የገበያው ሁኔታ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች እንደአስፈላጊነቱ ተመጣጣኝ የሆኑ ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጡ ይችላሉ።

## አባሪ ፬

**<u>፩.፪ በዚህ አባሪ ተራ ቁጥር ፩.፩ (ለ) መሠረት ውስብስብ ያልሆኑ ግዥዎች ዝርዝር</u>**

| ዕቃዎች | የግንባታ ሥራዎች | የምክር አገልግሎት | ሌሎች አገልግሎቶች |
|---|---|---|---|
| ▪ ለገበያ የተዘጋጁ የጽህፈት መሣሪያ ዎች<br>▪ ለገበያ የተዘጋጁ የዕዳት ዕቃዎች | ▪ የህንፃ ዕድሳት<br>▪ የቀለም ቅብ ሥራ | ▪ ዝርዝር የጥናት አካሔድ ( Methodology) | ▪ የህትመት<br>▪ የተሽከርካሪ ጥገና<br>▪ የመሳሪያዎችና ዕቃዎች |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ▪ ለገበያ የተዘጋጁ ኮምፒዩተሮች እና ተጓዳኝ ዕቃዎች<br>▪ ለገበያ የተዘጋጁ ፕሪንተሮች<br>▪ ለገበያ የተዘጋጁ የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች<br>▪ የመኪና ጎማ<br>▪ ለገበያ የተዘጋጁ ልዩ ልዩ መለዋወ ጫዎች (ለምሳሌ የተሽከርካሪ፣ የቢሮ መገልገያ ማሽኖች)<br>▪ ለገበያ የተዘጋጁ የኤሌክትሪክ፣ ኢሌክትሮኒክስና ኢሌክትሮ ሜካኒካል ዕቃዎች<br>▪ ለገበያ የተዘጋጁ የቢሮ መገልገያ ማሽኖች (ለምሳሌ ፋክስ፣ ፎቶ ኮፒ፣ መጠረዣ ማሽን)<br>▪ የግንባታ ዕቃዎቸ (ለምሳሌ ሲሚንቶ፣ ብረት፣ አሸዋ፣ ቧንቧ፣ ቀለም፣ እንጨት፣ ምስማር)<br>▪ የምግብ ጥሬ ዕቃ እና የተዘጋጀ ምግብ<br>▪ ነዳጅና ልዩ ልዩ ቅባቶች<br>▪ ለገበያ የተዘጋጁ ልብሶች፣ ጨርቆች እና ጫማዎች<br>▪ ለገበያ የተዘጋጁ መድሐኒቶች እና የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች<br>▪ ኬሚካሎች እና ሬኤጀንቶች<br>▪ መፃሕፍት እና ጆርናሎች | ▪ የጊዜያዊ ቤቶች ስራ<br>▪ የአጥር ስራ<br>▪ የቢሮ መከፋፈል (ፓርትሽን) ስራ | ማቅረብ የማይጠይቁ አገልግሎት ግዥዎች፣ | ኪራይ<br>▪ የቢሮ ዕቃዎችና የቢሮ ማሽኖች ጥገና<br>▪ የትራንስፖርት ኪራይ<br>▪ የሆቴልና መስተንግዶ<br>▪ የቧንቧ እና የኤሊክትሪክ ጥገና<br>▪ የስልጠና<br>▪ የኦዲት አገልግሎት<br>▪ የጥበቃ እና የፅዳት<br>▪ የግዥ አገልግሎት<br>▪ የግቢ ማስዋብና ማስተካከል<br>▪ የቢሮ ማስዋብ<br>▪ የቢሮ ኪራይ |

- «ለገበያ የተዘጋጁ» ማለት ለተጠቃሚው ሕዝብ ፍላጎት ተብለው የሚመረቱ ስታንዳርድ የገበያ ዕቃዎቸ ሲሆኑ ለግዥ ፈፃሚ መ/ቤቱ በተለየ ሁኔታ የሚመረቱትን አይጨምርም፡፡
- ግዥ ፈፃሚው አካል ዝርዝር የጥናት አካሔድ የማያስፈልጋቸውን ውስብስብ ያልሆኑ የምክር አገልግሎቶች ዓይነት የሚፈለገውን የምክር አገልግሎት የሚኖረውን የጥናት ባሕርይ በማየት ይወስናል፡፡

## በዚህ መመሪያ በን/አንቀጽ 43.9 በን/ን/አንቀጽ 43.9.5 /መ/ በቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ለመንገድ ሥራ እና ለሕንጻ ግንባታ የሚገዙት ማሽነሪዎች ዝርዝር

| ተራ ቁጥር | ለመንገድ ሥራ ተቋራጭ የተፈቀዱ ማሽነሪዎች | ለሕንጻ ሥራ ተቋራጭ የተፈቀዱ ማሽነሪዎች |
|---|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| 1 | ቡል ዶዘር | አክስካቫተር |
| 2 | ፍሮንት ኢንድ ሎደር | ሃይድሮሊክ ብሬከር |
| 3 | ሞቶር ግሬደር | ክሬን |
| 4 | ትሬንች አክስካቫተር | ታወር ክሬን |
| 5 | ባክሆይ | ዶዘር |
| 6 | ግሪድ ሮለር | ትራክ ሚክስር |
| 7 | ቫይብራቶሪ ሮለር | ሎደር |
| 8 | ወተር ቦውሰር | ዳምፕ ትራክ |
| 9 | ዳምፕ ትራክስ | ስካፎልዲንግ |
| 10 | ትራክ ዊዝ ትሬለር | ሮርምወርክ |
| 11 | ሎቤድ ሀኡሊንግ ትራክ | ፍሮንት ኤንድ ዳምፐር |
| 12 | ቢቱመን ዲስትሪቢውተር | ኮምጠክተር/ሮለር |
| 13 | ስቴሽነሪ ሂተር | ባክሆ |
| 14 | ፔቨር ፎር ቤዝ ኮርስ | ክሬሸር |
| 15 | አስጠልት ፔቨር | ጀኔሬተር |
| 16 | ሰልፍ ፕሮፒልድ ቺፕ ስፒረደር | ትራክ ዊዝ ትሬለር |
| 17 | ሜካኒካል ብሩም | |

| ተራ ቁጥር | ለመንገድ ሥራ ተቋራጭ የተፈቀዱ ማሽነሪዎች | ለሕንጻ ሥራ ተቋራጭ የተፈቀዱ ማሽነሪዎች |
|---|---|---|

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 18 | ታንደም ሮለር | |
| | 19 | ቫይብሬቲንግ ሮለር | |
| | 20 | ፖድ ፉት ሮለር | |
| | 21 | ፕኒውማቲክ ታየር ሮለር | |
| | 22 | አስጠልት ፕላንት | |
| | 23 | ክራሺንግ እና ስክሪኒንግ ፕላንት | |
| 7 | 24 | ዋጎን ድሪል | |
| | 25 | ኮምፕሬስር | |
| | 26 | ክሬን | |
| | 27 | ኮንክሪት ሚክሰር | |
| | 28 | ጀነሬተር | |
| | 29 | የኮንሰልታንቶች መቆጣጠሪያ ተሽከርካሪ | |

አባሪ ፳

## በግዥ አፈጻጸም መመሪያ ንዑስ አንቀጽ ፫፮ (፭) መሠረት በተጫራቾች የሚሞላ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና

□ፅ□ መለ□ ቁዓር _________ (የጨረታ መለያ ቁጥር አስገባ)

ለ____________________(የግዥ ፈጻሚውን መ/ቤት ሙሉ ስም አስገባ)

/የተጫራች ሙሉ ስም አስገባ/ ከአሁን በኋላ «ተጫራች» □□ተባለ □ሚ□ራ □ፅ□ መለ□ ቁዓር_________/ □ፅ□ መለ□ ቁዓር እና የዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶችን ____________ **(አጭር መግለጫ አስገባ)** ካሁን በኋላ ጨረታው እየተባለ የሚጠራውን ለማቅረብ በ___________/ **□ፌ ረታ ማስረከቢያ ቀን _________ / ቀን __ወርና__ □ም____** አስገባ/ የተፃፈውን ጨረ□ □ሰቶፃን ስለሆነ እኔ__________________ ____________/ የድርጅቱን ስም እና ባለቤት ወይም የመፈረም ሥልጣን ያለው ኃላፊ ስም አስገባ/ ከዚህ በታች የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ የተጠቀሰውን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና /□ፌ ረታ **ዋስትናውን መጠንና** የገንዘቡን ዓይነት በቃላትና በቁጥር **ፅለ□/** ሙሉ ኃላፊነት ድርጅቱ የሚወስድ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የዋስትና ሰጪው የተለመደ ማህተም ተደርጐበት/ዋስትናው የሚቆይበት **የቀን ብዛት በቁጥር፣ በወር ወይም በዓመት** መሆኑ ተለይቶ ይገለፅ/ ጁታሽ□ል፡፡

የሚከተሉትን ፅጻ ታዎች በመረዳት ተፈጻሚ ለማድረግ ተስማምቻለሁ፡፡

ሀ/ በጨረታ ሠነዱ ላይ የተገለጸው የመጫረቻ ሠነድ ማቅረቢያ የመጨረሻ ጊዜ ካለፈ በኋላ ወይም በመጫረቻ ሠነዱ የተገለጸው የጨረታ ዋጋ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ከጨረታው ራሴን ላለማግለል ፣ወይም

ለ/ በመጫረቻ ሠነዱ የተገለጸው የጨረታ ዋጋ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የግዥ ውል እንድፈርም ከመ/ቤቱ የቀረበልኝን የጽሑፍ ጥያቄ በመቀበል ውል ለመፈረም ፈቀደኛ ለመሆን፣ወይም

ሐ/ በጨረታው ውድድር አሸናፊ በመሆኔ ውል እንድፈርም እና የውል ማስከበሪያ እንዳስይዝ ስጠየቅ፣ የውል ማስከበሪያውን ለማስያዝ ፈቃደኛ ለመሆን፣ እና ከላይ በፊደል ተራ ሀ - ሐ እና በጨረታ ሠነዱ የተገለጹትን ሌሎች ተግባራት፣ባልፈጽም የግዥ □□ሚው መ/ቤት በሚያቀርበው □□ሑአ ዓ□ቴ ከላይ የተገለጸውን የጨረታ ማስከበሪያ የገንዘብ መጠን ለመ/ቤቱ በአምስት ቀን ጊዜ ውስጥ ለመክፈል ተስማምቻለሁ::

ጀህ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ጨረታው ፀንቶ ከሚቆይበት ጊዜ በተጨማሪ ለ፪፰ ቀናት በሕግ ፊት ፀንቶ ይቆያል:: ይህን ዋስትና በተመለከተ ከተጠቀሰው ጊዜ ዘግይቶ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም::

ስም ________ /**ፊ ረታውን የሚፈርመው ሰው ሙሉ ስምና ሕ□ዊ ስልጣኑን** አስገባ/

**□ርማ/______________ስምና ማዕረጉ ከላይ የተጠቀሰውን ሰው ፊርማ አስገባ/**

ወይም ወኪል ከሆነ ፊ ረታውን ለመፈረም ሕጋዊ ስልጣን የተሰጠው /ሰው **ሙሉ ስም** እና ፊርማ **አስገባ/**

ቀን-------------------- /የተፈረመበትን **ቀን**፣ወር እና ዓ.ም. **አስገባ/**